7/10

— MANKIND AND ITS 4 GODS —



ZE'AB ZEMICHAEL

ስለ እኔ---------- 3

Will ምንድን ነው---------- 7

የሰው ልጅ---------- 10

እንስሳ---------- 13

ሰው---------- 23

ታልቁ ሰው---------- 30

ከታላቁ ሰው በላይ---------- 40

የመኖር ፍላጎት---------- 43

የኃይል ፍላጎት---------- 54

የፍቅር ፍላጎት---------- 69

የደስታ ፍላጎት---------- 77

ማጠቃለያ---------- 91

ስለ እኔ

ሰላም ዘአብ ዘሚካኤል እባላለሁ ። በ"ዘ" ፊደል የሚጀምረው ስሜ ለብዙዎች እንግዳ ሊሆን ቢችልም፣ በቤተሰባችን ውስጥ ግን ይህ የተለመደ መለያችን ነው የሁላችንም ስም የሚጀምረው በ"ዘ" ነውና። ወደ ዋናው ርእስ ከመሻገሬ በፊት፣ስለ ራሴ የተወሰነ ነገር ልበላችሁ ።

እ.ኢ.አ በ2013 ዓ.ም የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ በገባበት ወቅት ነበረ፣ያኔ ገና የጉርምስና ዕድሜዬን "ሀ" ብዬ የጀመርኩ ታዳጊ ነበርኩ። በወቅቱ ከመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል ተነስተን ወደ ትግራይ መቐለ ከተማ የተዘዋወርንበት አጋጣሚ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ፣ በዚያው ዓመት ነበር የእርስ በርስ ጦርነቱ የጀመረው ።

ጦርነትን በአካል እንዳለፈ ሰው እንዲህ እገልጸዋለሁ “ጦርነት ማለት በምድር ላይ ያሉትን ክፉ ነገሮች በጠቅላላ በአንድ ላይ ሰብስቦ የያዘ ” በሚል ። በአንድ ወቅት በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ “ለ24 ሰዓታት ያህል ምንም ዓይነት ሕግ ባይኖር ምን ታደርጉ ነበር?” የሚል መነጋገሪያ ርዕስ አይቼ ነበር። የብዙዎች ምላሽ በውስጣቸው ያለውን ጥልቅ የወንጀል ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ነበር። ታዲያ ሕግ በሌለበት ዓለም ውስጥ ለ24 ሰዓት እንኳ ያን ያህል ወንጀል ለመፈጸም የተዘጋጀ ሰው ባለበት ምድር ላይ፣ ለሁለት ዓመታት ሕግ ባይኖር ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በነዚያ የጦርነት ዓመታት የመኖር ፍላጎቴ በእጅጉ ጠፍቶ ነበር። ነገን ለማየት የምጓጓበት ምንም ምክንያት አልነበረኝም። "ነገ" እና "ዛሬ" ለእኔ አንድ ነበሩ። ነገ ምን ሊመስል እንደሚችል ቀድሜ አውቃለዋ ልክ እንደ ዛሬው ሁሉ ድብርትን፣ ተስፋ ቢስነትንና አስጠሊታ ድባብን ይዞ የሚመጣ በመሆኑ ነገ ለእኔ ምንም ትርጉም አልነበረውም።

እንግዳ ሀገር፣ እንግዳ ቋንቋ፣ እንግዳ ሰዎች...በዛ ላይ ትምህርት የለም፣ ኢንተርኔት የለም፣ሌላው ቢቀር የምደበርበት ስማርት ስልክ (Smart Phone) እንኳን አልነበረኝም።

ቀስበቀስም ስሜቶቼ እየደበዘዙ እየደበዘዙ መጡ መናደድ፣መደንገጥ ማዘን ፣መደሰት ፣መጓጓት ፣የመሳሰሉት ደበዘዙ ከሰው ይልቅ ወደ ሮቦትነት እየተጠጋሁ መጣሁ የነዚህ ሁሉ እንግዳና አስጨናቂ ነገሮች መደራረብ ሁኔታውን ይበልጥ ከባድ አደረገው፤ ይህንን ዝቅተኛውንና ጨለማውን የሕይወቴን ክፍል ለሁለት ተከታታይ ዓመታት አሳለፍኩት።

በዚህ ተስፋ ቢስ የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ እያለሁ ግን፣ በአንድ ወቅት በNBC ETHIOPIA የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ የቀረበ አንድ ፕሮግራም ተመለከትኩ "የNBC ዶክመንተሪ በግሩም ተበጀ"። ይህ ፕሮግራም ለእኔ ጨዋታ ቀያሪ (Game Changer) ነበር።

በፕሮግራሙ እጅግ ከመማረኬ የተነሳ፣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የደስታ ስሜት በውስጤ ያቆጠቁጥ ጀመር። ሁልጊዜ ማታ 1:30 ሆኖ ጋዜጠኛ ግሩም ተበጀ የሚመጣበትን ቀን በጉጉት መናፈቅ ጀመርኩ። አሁን ለእኔ "ነገ" አዲስ ትርጉም አለው፤ ምሽጽ 1:30 ላይ ከዚህ ቀደም የማላውቀውን አዲስና ውብ ዓለም ይዞልኝ ይመጣል። በዚያ በጦርነት ውስጥ ነገን የማየት ፍላጎቴ እየተመለሰ መጣ።

ግሩም ተበጀ ማለት እንደ BBC, NETFLIX, CGTN እና በመሳሰሉት ትላልቅ የዓለም አቀፍ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የተዘጋጁ የዶክመንተሪ ፊልሞችን በአማርኛ ተርጉሞ የሚያቀርብ ባለሙያ ነው። ስለ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ የዱር እንስሳት፣ ተፈጥሮና ስለ <u>ሰው ልጅ</u> ያቀርብ ነበር። እነዚህ ጉዳዮች፣ በተለይም በዚያ በጦርነት ጨለማ በተዋጠ ወቅት፣ እንደዚያ ተከሽነው ሲቀርቡ ትልቅ

የአእምሮ እረፍት ሆነኝ ። እሱን ከመውደዴ የተነሳ የእሱን የአነጋገር ዜማና ቃላት ለመጠቀም ሁላ እሞክር ነበር።

ከቀረቡት ዶክመንተሪዎች መካከል ከሁሉም በላይ ትኩረቴን የሳቡት በሰው ልጅ ዙሪያ የሚሰሩት ነበሩ። የሰው ልጅ ምን ያህል አደገኛና ምስጢራዊ፣ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ምን ያህል አስገራሚ ፍጡር እንደሆነ ተረዳሁ። ስለ ሰው ልጅ ማንነትና ስለ አደገኝነታችን በጥልቀት የማወቅ ፍላጎት አደረብኝ፤ በዚህም የሰው ልጅ ከምንም በላይ የምወደውና ይበልጥ ማወቅ የምፈልው ፍጡር ሆነ።

ጊዜያት አልፈው በሁለቱ ኃይሎች ስምምነት ጦርነቱ ሲያበቃ፣ ነገሮች ወደ መረጋጋት ማምራት ጀመሩ። ከጦርነቱ አሰቃቂ ትውስታ (Trauma) እንድወጣ የረዱኝ፣ እንደ ሕክምና (Therapy) የሆኑልኝ አራት ዋና ዋና ነገሮች ነበሩ። በጊዜ ቅደም ተከተል ሳስቀምጣቸው፦

1. ግሩም ተበጀ
2. Bleach (የጃፓን አኒሜሽን)
3. ፋሩቅ ወህቢ ዑመር (Farouk Almeghribi)
4. ማጎሌት ዘቅዱስ ያሬድ

ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነውን የፋሩቅ አልመግሪቢን ሥራዎች አገኘሁ። ፋሩቅ በአንድ ወቅት ባደረገው የፖ ድካስት (Podcast) ላይ ስለ ፍላጎት ፍልስፍና ("The Will Philosophy") የተወሰነ ነገር ጠቅሶ ያልፏል (ፋሩቅ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነና ምን እንደሚሠራ መግለጽ ስለሚከብድ ዝም ብዬ አልፈዋለሁ)። ይህ አባባሉ ትኩረቴን በእጅጉ ስለሳበው "ምንድን ነው?" ብዬ በራሴ መፈለግና መመርመር ጀመርኩ።

እሱ የጠቀሳቸውን መነሻዎች መሠረት በማድረግ፣ በራሴ ሕይወት ትክክለኛነቱን መረመርኩ፤ ተረዳሁትም። ስረዳው ግን ነገሩ ሌላ ታሪክ ሆኖ አገኘሁት! የሰው ልጅን ማንነት አብጠርጥሮ የሚያስረዳ ጥልቅ የፍልስፍና ውጤት ነው።

የሰው ልጅ ምን እንደሆነ አወቅሁ፤ "Will"ን (ፍላጎትን) ስትረዳ፣ አንድ ሰው ገና የሚተነፍሰውን ትንፋሽና የልቡን ትርታ በማዳመጥ ብቻ፣ ያንን ድርጊት ለምን እንዳደረገው ወይም እንደሚያደርገው አስቀድመህ ማወቅ ትችላለህ።

በአሁኑ ጊዜ የጦርነቱ ተፅዕኖ በግል ሕይወቴ ላይ አሉታዊ ጫና የሚያደርስበት ደረጃ ላይ አይደለም። መጀመሪያ አካባቢ ያንን ጊዜ ሳስበው በጣም ያመኝና እጠላው ነበር። አሁን ግን ማለፍ የነበረብኝ ወሳኝ የሕይወት ምዕራፍ መሆኑን ተረድቻለሁ። አሁን ያንን ጊዜ አልጠላውም፤ አጠንክሮኛል። አብዛኛው ሰው ማለፍ የሚከብደውን የልጅነት (Teenage) ዕድሜ እንድሻገር ረድቶኛል። አሁን ራሴን በራሴ አክሜ ጤናዬን አግኝቻለሁ። እኔ አሁን መኖርን በጣም የምወድ፣ ሕይወትን የማጣጥም እና ይህችን ውብ ዓለም የማፈቅር የ21 ዓመት ወጣት ነኝ።

ለአርተር ሾፐንሃወር (Arthur Schopenhauer) እና ለፍሬድሪክ ኒቻ (Friedrich Nietzsche) ክብር ይሁንና፣ ቀጥሎ ስለ ፍላጎት ፍልስፍና (The Will Philosophy) ማብራሪያዬን እጀምራለሁ።

ማሳሰቢያ፦ ከዚህ በመቀጠል የምሰጠው ማብራሪያ እኔ በግሌ የ "Will"ን ትክክለኛነት ያረጋገጥኩበት መንገድ ነው እንጂ፣ በቀጥታ የሾፐንሃወርም ሆነ የኒቻ ማብራሪያ አይደለም።

Will ምንድነው

የሰው ልጅ የውስጥ ሞተር፡ ፍላጎት "Will" የሚለውን ቃል ቀጥተኛ ወደ አማርኛ ስንመልሰው "ፍላጎት" ወይም "ፈቃድ" የሚል ትርጉም ይሰጠናል። ነገር ግን ከተራ፣ ጊዜያዊና ዕለታዊ ፍላጎት ሰፋ ባለ መልኩ "ውስጣዊ የገፊ ኃይል" (Inner Driving Force) ልንለው እንችላለን።

በቀላል አማርኛ፣ በሰው ልጅም ሆነ በሌሎች ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ውስጥ የተጫነ ተፈጥሯዊ "የሶፍትዌር መተግበሪያ" (Software Application) እንደማለት ነው።

እያንዳንዱ የ"Will" መተግበሪያ የየራሱ የሆነ ልዩ ተግባር ያለውና እኛን ከውስጥ ሆኖ አንድን ነገር እንድናደርግ የሚገፋፋ የተፈጥሮ ኃይል ነው።

የዚህ ኃይል ዋና ተግባር እኛ ስንፈጠር ጀምሮ የጎደለንን ወይም የእኛ ያልሆነውን ነገር ለመሙላትና ያንን ጎደሎ ነገር ለመሙላት በምናደርገው ጉዞ ውስጥ እኛን በ ሕይወት ለማቆየት ፕሮግራም የተደረገ Software ነው።

ይህንን ውስጣዊ ገፊ ኃይል በዋናነት በአራት ታላላቅ ምድቦች ከፍለን እናያቸዋለን፦

1. የመኖር ፍላጎት (The Will to Live) በአርተር ሾፕንሃወር
2. የኃይል ፍላጎት (The Will to Power) በፍሬድሪክ ኒቻ
3. የፍቅር ፍላጎት (The Will to Love) በፋሩቅ አልመግሪቢ
4. የደስታ ፍላጎት (The Will to Happiness) በዘአብ ዘሚካኤል

የኛ የሰው ልጆች ድንቅ ባህርይ ከምለው ውስጥ ከትንሽ እና ከተራ ነገር ተነስተን፣ ያችን ቀላል የምትመስልን ጽንሰ-ሃሳብ ወደ ታላቅ

ተአምር የመቀየር ጥበባችን ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ውጫዊውን የተፈጥሮ የስበትን ህግ (Gravity) የተረዳንበት መንገድ ነው።

የውጪውን ዓለም ህግ፣ በተለይም የመሬት ስበትን (Gravity) ምንነት ከተረዳን በኋላ በዚያው አላበቃም። ይልቁኑ ያንን የመሬት ስበት ህግ እንዴት ማቀናበርና መላመድ ለራስ ጥቅም ማዋል (Manipulate ማድረግ) እንደምንችል አጠናን። በውጤቱም፣ የመሬት ስበትን ተቋቁሞና አሸንፎ በሰማይ ላይ እንደ ወፍ መብረር ቻልን፤ የኤሮዳይናሚክስን ህግ በመጠቀም ግዙፍ አውሮፕላኖችንና መንኮራኩሮችን ሰራን።

ከግራቪቲ በተጨማሪ፣ ሌሎች በርካታ የተፈጥሮ ህጎችን መርምረን ለራሳችን ጥቅም አውለናል፦

- የብርሃንና የኤሌክትሮማግኔቲክ ህጎችን በማጥናት ጨለማን በብርሃን ቀየረናል፤ ዓለምን በኮሙዩኒኬሽን መረብ አገናኝተናል።

- የቴርሞዳይናሚክስ (የሙቀት) ህግን በመረዳት የኢንዱስትሪ አብዮትን ፈጠረናል፤ ሞተሮችን አንቀሳቅሰናለ።

- የኳንተም ፊዚክስና የአቶም ህጎችን በመበዝበዝ ማይክሮ-ቺፖችንና የሱፐር ኮምፒውተር ቴክኖሎጂዎችን እውን አደረገናል።

እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ትልቁ ጥያቄ የሚፈጠረው። የሰው ልጅ ውጫዊ የሆነውን የተፈጥሮ ህግ ተረድቶ፣ ተፈጥሮ የጣለችበትን ገደብ ጥሶ እዚህ ደረጃ ድረስ ከተራቀቀና ተአምራትን ከሰራ ለመሆኑ ውስጣዊ የሆነውን ራሱን (ፍላጎት Will እና ማንነት) ጠንቅቆ ሲያውቅ ምን ዓይነት ተአምር ይፈጥር ይሆን?

ውጫዊውን ዓለም በመግራት ምድርን የቀየረው የሰው ልጅ፣ ወደ ውስጥ ተመልሶ የገዛ እራሱን የአዕምሮና የነፍስ ህግጋት ሙሉ በሙሉ ማስተዳደር ቢችል የሚኖረውን የዕድገትና የንቃት ደረጃ ማሰብ በአውነትም ያስደንቃል።

ይህንን ፅሁፍ እንድፅፍና እነዚህን አራት የ"Will" አይነቶች እንድዳስስ ዋነኛ መነሻ (Inspiration) የሆነኝም፣ ይኸው የሰው ልጅ ውስጣዊ አቅሙንና ፍላጎቱን ተረድቶ ወደ የትኛው የላቀ የንቃት ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል ካለኝ ጥልቅ ጉጉትና መደነቅ የተነሳ ነው።

የሰው ልጅ

ከፈረሱ ጋሪው እንዳይቀድምብን መጀመሪያ ራሱ የሰውልጅ ማነው ? እኛ እነማን ነን ምንድነን ? “የሰው ልጅ ማነው?” የሚለው ጥያቄ በታሪክ ውስጥ ታላላቅ ፈላስፋዎችን፣ ሳይንቲስቶችን፣ የሃይማኖት አባቶችንና ባለቅኔዎችን ሲያነጋግር የኖረ፣ ዛሬም ድረስ ምላሹ ያላለቀለት ጥልቅ ጥያቄ ነው። የሰው ልጅ ይህንን ማንነቱን ለመፈለግ ያደረገውን ዘመናትን የተሻገረ ጉዞ እና የደረሰበትን መደምደሚያዎች በጥቂቱ እንመልከት

1. <u>ማንነትን የመፈለግ ታሪካዊ ጉዞ (The Historical Journey)</u>

የሰው ልጅ ራሱን የመፈለግ ጉዞ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች ውስጥ አልፏል፦

ሀ. የኮስሞሎጂ እና የተፈጥሮ ምዕራፍ (ቀደምት ስልጣኔዎች) በጥንታዊው ዓለም (በግብፅ፣ በባቢሎን፣ በግሪክ) መጀመሪያ ላይ የሰው ልጅ ማንነቱን የፈለገው ከተፈጥሮና ከኮስሞስ (ከጽንፈ ዓለም) አንጻር ነበር። “እኔ ከፀሐይ፣ ከከዋክብትና ከምድር ጋር ያለኝ ግንኙነት ምንድነው?” ብሎ ጠየቀ። የሰው ልጅ እራሱን የታላቁ ተፈጥሮ አንድ አካል አድርጎ ያይ ነበር።

ለ. የሃይማኖትና የመለኮት ምዕራፍ (The Theological Era) ከዚያም የሰው ልጅ ማንነቱን ከመለኮታዊ ኃይል ጋር አገናኘው። በሁሉም ታላላቅ ሃይማኖቶች (በተለይም በአብርሃማዊ ሃይማኖቶች) የሰው ልጅ ትርጉም ያገኘው ከፈጣሪው ጋር ባለው ግንኙነት ነው። “የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ፣ ምድርን እንዲገዛ የተሾመ፣ ከስጋ ባሻገር የማይሞት ነፍስ ያለው ፍጡር ነው” የሚለው መደምደሚያ የዘመናት መሰረት ሆነ

ሐ. የፍልስፍና እና የዲካርት አብዮት (The Philosophical Era) በ17ኛው ክፍለ ዘመን ሬኔ ዲካርት (René Descartes) "Cogito, ergo sum" "አስባለሁ፣ ስለዚህ አለሁ" በማለት አዲስ የፍልስፍና በር ከፈተ። የሰው ልጅ ማንነቱ የተገነባው በማሰብ ችሎታው (Rationality) ላይ እንደሆነ ተደመደመ። የሰው ልጅ "አስተዋዩ ፍጡር" (The Rational Animal) ተብሎ ተለየ።

መ. የሳይንስና የባዮሎጂ አብዮት (The Scientific Era) ቻርለስ ዳርዊን የዝግመተ-ለውጥ (Evolution) ቲዎሪን ይዞ ሲመጣ የሰው ልጅ ማንነት ፍለጋ ወደ ቁስ እና ወደ ተፈጥሮ ላብራቶሪ ወረደ። ሳይንስ ሰውን ከሌሎች እንስሳት ተለይቶ የዳበረ አዕምሮና የዲ.ኤን.ኤ (DNA) መዋቅር እንዳለው፣ ነገር ግን አሁንም የባዮሎጂ ህግ የሚገዛው ፍጡር እንደሆነ አረጋገጠ።

የሰው ልጅ ማንነት ላይ የተደረሱ ታላላቅ መደምደሚያዎች ከተለያዩ የጥናት መስኮች አንጻር የሰው ልጅ ማንነት በሚከተሉት ዋና ዋና መደምደሚያዎች ላይ ያርፋል፦

1.የፍልስፍና መደምደሚያ (Existentialism)

በተለይም እንደ ዣን ፖል ሳርተር እና አልቤር ካሙ ያሉ የኤግዚስቴንሻሊዝም ፈላስፋዎች የደረሱበት መደምደሚያ አስገራሚ ነው፦
“Existence precedes essence” (ህልውና ከባህርይ ይቀድማል) ።ትርጉሙም፡ የሰው ልጅ ሲወለድ አስቀድሞ የተሰጠው የተዘጋጀ “ማንነት” የለውም። ሰው መጀመሪያ ወደ ምድር ይመጣል (ይኖራል)፤ ከዚያ በኋላ በምርጫው፣ በድርጊቱና በሚያልፍበት ህይወት የራሱን ማንነት ራሱ ይስላል። ስለዚህ የሰው ልጅ የራሱ ማንነት ጠራቢ ነው።

2/ የስነ-ልቦና መደምደሚያ (Psychological Conclusion)

ሲግመንድ ፍሮይድ እና ካርል ዩንግ የሰውን ልጅ ማንነት ወደ ውስጥ (ንዑስ አዕምሮ ወይም Unconscious Mind) ወርደው ፈተሹት። የደረሱበት መደምደሚያ፡ የሰው ልጅ ማንነት ማለት በውስጡ ባሉ ተቃራኒ ስሜቶች (በእንስሳዊ ፍላጎቱ፣ በባህላዊ እሴቶቹ፣ እና በንቃት ደረጃው) መካከለኛ ሆኖ የሚኖር የስሜቶች ጦር ሜዳ ነው።

3/ የባዮሎጂ እና የነርቭ ሳይንስ (Neuroscience) መደምደሚያ

የዘመናችን ሳይንስ የሰው ልጅ ማንነት በቢሊዮን የሚቆጠሩ የነርቭ ሴሎች (Neurons) ትስስር ውጤት እንደሆነ ይናገራል። የሰው ልጅ ማንነቱ ያለው አዕምሮው ውስጥ ነው። ትውስታው፣ ስብዕናውና ስሜቱ በሙሉ የአዕምሮው ኬሚካላዊ ስራዎች ናቸው። ነገር ግን ሳይንስ አሁንም "የሰው ልጅ ንቃት (Consciousness) እንዴት ሊፈጠር ቻለ?" የሚለውን ሙሉ በሙሉ መመለስ አልቻለም።

<u>የሰውን ልጅ ባህርይ እንዴት አየዋለሁ</u>

ከላይ በገለፅኩት መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ላይ የነበሩ ድንቅ ድንቅ ምልከታዎችን አይተናል እስኪ አሁን የግል ምልከታዬን ላስቃኛችሁ ። የሰው ልጅ ባህሪ የማይለወጥ ቋሚ ማንነት ሳይሆን፣ ቀጣይነት ያለው የሽግግርና የለውጥ ሂደት እንደሆነ እና ይህንንም እድገት በአራት ተከታታይ ግን እርስ በእርስ በሚደራረቡ ደረጃዎች ላይ እከፍለዋለሁ ። እነሱም፦

1, **እንስሳ** (The Animal)

2, **ሰው** (The Human)

3, **ታላቁ ሰው** (The Overman/Übermensch)

4, **ከታላቁ ሰው በላይ/ባሻገር** (Beyond the Overman)

በሚል ስከፍላቸው ሁላችንም ሰንፈጠር ከ4ቱ በ 1ዱ ደረጃ ላይ ሆነን ሲሆን የኛ ሃላፊነት የሚሆነው ካለንበት ደረጃ ወደ ላይ መውጣትና መሸጋገር ይሆናል

ደረጃ1 እንስሳ

ይህኛው ብዙውን ጊዜ የምንጠቀምበት ከጭካኔ ጋር በተያያዘ ነው ምንም እንኳ ትክክል ቢሆንም በዚህ ብቻ የተገደበ ግን አይደለም የተለያዩ እና ሰፋ ያሉ ባህርያቶች አሉት ። እኔ ይህንን ደረጃ የሁሉም ነገር መነሻ ነጥብ ብዬ እጠራዋለሁ ፤ አብዛኛው የአለም ሕዝብያለበት ደረጃ ነው ።

ባህሪ 1፦ ደመነፍስ

እዚህ ሁሉንም ነገር የሚመራው ደመነፍስ ነው ። ደመነፍስ (Instinct) ማለት አንድ ሕያው ፍጡር ሳይማረው፣ ማንም ሳያሳየው ወይም አስቦበት ሳይሆን ከተፈጥሮው ይዞት የሚመጣውና በውስጡ የተቀረጸ ድንገተኛ፣ ፈጣንና አውቶማቲክ የባህሪ ምላሽ ነው። በቀላል አነጋገር፣ አእምሮ “ምን ላድርግ?” ብሎ ሳይመራመርና ሳይወስን፣ አካል ወይም ሕሊና ራሱንና ሕይወቱን ለማዳን ወይም ፍላጎቱን ለማሟላት በራሱ ጊዜ የሚወስደው ቅጽበታዊ እርምጃ ነው ፣
ይህ ተፈጥሯዊ ጥበብ በሰዎችም ሆነ በእንስሳት ሕይወት ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ የሚሠራ ሲሆን፣ ለዚህም በርካታ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል፦
1ኛ አንዲት ወፍ ከእንቁላል ወጥታ ብቻዋን ብታድግና ሌላ ወፍ ጎጆ ስትሠራ ባታይም እንኳ፣ ዕድሜዋ ሲደርስ ጭድና ቅጠል አሰባስባ የሚገርም የሕንፃ ጥበብ የተሞላበት ጎጆ ትሠራለች፤ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሕፃን ገና እንደተወለደ ሳይማርና ሳይለማመድ በራሱ

ጊዜ የእናቱን ጡት መጥባት ይጀምራል። እንስሳት አደጋ ሲገጥማቸው ወይም ድመት ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ስትወልድ ግልገሎቿን እንዴት እንደምትጠብቅና እንደምትከባከብ በደመ ነፍስ እንደምታውቀው ሁሉ፣ አንድ ሰውም መንገድ ላይ በድንገት እባብ ሲያይ አእምሮው “ይህ እባብ ይነድፋል ወይስ አይነድፍም? መርዛማ ነው ወይስ ኤዴሌም?” ብሎ እስኪያሰላስል አይጠብቅም ሳያስበውና ሳይመራመር ወዲያው ወደ ኋላ የሚዘልበትና ልቡ በፍጥነት የሚመታበት "ራስን የማዳን" (Fight or Flight) ተፈጥሯዊ ምላሽ አለው።

የተወሰኑ የወፍ ዝርያዎች ኮምፓስ ወይም ጂፒኤስ ሳይኖራቸው የቅዝቃዜ ወራት ሲመጣ በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው ወደ ሞቃት አገር የሚበሩበት ደመ ነፍስ እንደ ኮምፓስ ስለሆነላቸው ነው ፣ በሰውም ላይ አንድ ነገር በድንገት ወደ ዓይን ሲቃረብ አእምሮ ሳይወስን የዓይን ሽፋሽፍት በራሱ ጊዜ ተዘግቶ ዓይንን ከአደጋ የመጠበቅ ተመሳሳይ መካኒዝም ይሠራል።

ይህ ባህሪ ከአካባቢ፣ ከትምህርትና ከልምምድ በሚገኘውና በማሰላሰል የሚመጣው የዕውቀት ባህሪ (ለምሳሌ መኪና መንዳት ወይም በኮምፒውተር መጻፍ) የሚለይ ሲሆን፣ ሙሉ በሙሉ ከተፈጥሮ የተወረሰ፣ ማንም ማስተማር የማይፈልገውና ያለ ምንም ልምምድ በቅጽበት የሚከወን የሕልውና መከላከያ መሠረት ነው።

ይህም ለሒወታችን ሙሉ ሃላፊነት እኛ ላይ እንዳይሆን እና በስንፍናችን የተነሳ ሕይወታችንን እንዳናጣ የሕይወት ማኔጀር ብዬ የምጠራው አንዱነው ለምሳሌ ምግብ መብላት ሙሉ ለሙሉ የኛ ኃላፊነት ቢሆን ኖሮ እና በስንፍናችን ምክንያት ምግብ የማንበላበት ሁኔታ ሲፈጠር ቀስ በቀስ እየተመናመንን ወደ ሞት ደረጃ ያደርሰናል ለዚህም የረሃብን ህመም በደመነብስ ውስጥ እንይዛለን ይህም ምግብ እንድንበላ ያስገድደናል ውጤቱም በህይወት እንድንቆይ ያደርገናል ማለት ነው [ይህንን በሰፊው በ የመኖር ፍላጎት (Will to Live) ላይ እናየዋለን]

ይህም እስከ 4ኛው ደረጃ ድረስ የተዘረጋ ነው ወይም 4ቱም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች እንደየ መጠናቸው እንስሳዊ ባህርያት አሉባቸው

ባህሪ 2፦ ሰዎችን እንደ ቁም ነገር

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው መለኪያ እግዚአብሔር፣ ሰፊው አጽናፈ ሰማይ ወይም የውስጥ ስብዕና ሳይሆን “ሰው” ብቻ ነው። መኖሩም፣ መታገሉም፣ ማሸብረቁም ለሰዎች ነው።

የሰዎች አስተሳሰብ መሰረት “ሰው” ብቻ ሲሆን በዚህ ደረጃ ያሉ ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ሁሉ መልካምም ሆነ ክፉ መነሻው ሰው ነው። ራሳቸውን ችለው መቆም ስለማይችሉ፣ ልክ እንደ እንስሳት መንጋ ሁሌም አይናቸው ሌላው ሰው ላይ ነው።

ሊቃውንትና አዋቂዎቻቸው ራሱ የሚራቀቁት ስለ ሰው ነው በዚህ ደረጃ ያሉ የህብረተሰብ "አዋቂዎች" ወይም "ሊቃውንት" የሚባሉትን እንኳን ብንመለከት፣ ጥበባቸውና ፍልስፍናቸው ሰው ተኮር ነው። ለምሳሌ፦ "ሰው እንዳይንቅህ እንዲህ አድርግ"፣ "አንድ አንድ ሰዎች..." የሚሉ ምክሮች።

የህይወት ስኬት መለኪያቸውም ሰው ነው አንድ ነገር የሚገዙት፣ የሚማሩት ወይም የሚለብሱት ለራሳቸው ደስታ ሳይሆን "ሰው እንዲያይላቸው" ነው። ጎረቤት ወይም ጓደኛ የገዛውን አይተው ካልገዙ ህይወታቸው ትርጉም ያጣ ይመስላቸዋል። ህይወታቸው ሙሉ በሙሉ "ሰዎች ምን ይሉኛል?" በሚል ፍርሃት የታጠረ ነው።

የተገላቢጦሽ ስነ-ልቦና (Reverse Psychology) "እኔ ከሰው ምን አለኝ? ግድ የለኝም!" የሚል ትምክህት ያሳያሉ። ነገር ግን ይህ ንግግራቸው ራሱ ሰው ተኮር ነው። እውነተኛ ግድ የሌለው ሰው "ግድ የለኝም" ብሎ ለመናገር ራሱ አያስፈልገውም።

ባህሪ 3፦ መንጋነት

እንስሳት (ለምሳሌ በጎች፣ የዱር በሬዎች ወይም አንበሶች) ለደህንነታቸው ሲሉ በጅምላ ወይም በመንጋ ይጓዛሉ። አንደኛው ሲሮጥ ሌላው ለምን እንደሚሮጥ ሳያውቅ አብሮ ይሮጣል። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰውም የራሱ የሆነ ነጻ አእምሮና ማስተዋል የለውም፤ ህይወቱን የሚመራው በጅምላ እምነትና ስሜት ብቻ ነው።

በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ትክክለኛነታቸውን የሚመዝኑት በሰዎች ብዛት ነው። "ብዙ ሰው ካደረገው ትክክል ነው፣ ጥቂት ሰው ካደረገው ደግሞ ስህተት ነው" ብለው ያምናሉ። የራሳቸውን እውነት ፈልገው ከመቆም ይልቅ፣ በመንጋው ውስጥ ተደብቆ መጓዝ ሰላምና ደህንነት ይሰጣቸዋል። በትንሹ ምሳሌ ብናየው social media ላይ አንድ አዝናኝ video መጥቶልህ አይተከው ተዝናንተህ ላይክ ልታደርገው ስትል ምንም ላይክ ከሌለው ወይም ዝቅተኛ ከሆነ ኮስተር ብለህ ምንም እንዳልተፈጠረ ታልፈዋለህ ።

አንድ ሃሳብ እውነት መሆኑን የሚያረጋግጡት በምክንያት ሳይሆን "ስንት ሰው ደገፈው?" በሚለው ነው። ለምሳሌ፦ በማህበራዊ ሚዲያ (Social Media) ላይ በአንድ ሰው ላይ የሀሰት ስም ማጥፋት ቢነሳ፣ እውነቱን ሳያጣሩ ብዙ ሰው ስለሰደበው ብቻ አብረው ይሰድባሉ። ምክንያቱም ብቻቸውን ቆመው "እውነቱ ምንድነው?" ቢሉ ከመንጋው ተለይተው እንደሚጠቁ ስለሚፈሩ ነው።

በመንጋነት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ከውጭ ሲታዩ በጣም የሚዋደዱ፣ የሚደጋገፉ እና የአንድ ወገን አባላት ይመስላሉ። ነገር ግን ይህ አንድነታቸው ፍቅር ሳይሆን "የፍርሃት ጥምረት" ነው። ምሳሌ በአንድ ሃይማኖት፣ ብሄር ወይም የፖለቲካ ቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች ውጭ ላይ ሲታዩ እጅግ በጣም የሚዋደዱ እና ለወገናቸው የሚሞቱ ይመስላሉ። ነገር ግን ከውስጣቸው አንዱ ሰው ወጣ ያለ ጥያቄ ቢጠይቅ ወይም "ይህ የምናደርገው ስህተት ነው" ቢል፣

መጀመሪያ ተረባርበው የሚያጠቁትና የሚያገሉት እራሱ መንጋዎቹ ናቸው። **ምክንያቱ**ም የእነሱ ውጫዊ አንድነት ሌላውን ወገን ለማጥቂያ ወይም ራሳቸውን ለመከላከያ የፈጠሩት እንስሳዊ ስብስብ ስለሆነ፣ የውስጥ ነጻነትን በፍጹም አይፈቅዱም።

ባህሪ 4፦ ሞራል አልባነት

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው "ሞራል" ወይም "ቅንነት" የሚባሉትን እሴቶች የሚያውቃቸው በፅንሰ-ሃሳብ ደረጃ ብቻ ነው። ዋናው ግቡ የራሱን ፍላጎት ማርካት እስከሆነ ድረስ፣ ህግንና ስነ-ምግባርን መጣስ ለእሱ የብልጥነት እንጂ የስህተት ጉዳይ አይደለም።

ይህ ሰው በአንድ ወቅት የረዱትን፣ ያሳደጉትን ወይም የሰጡትን ሰዎች ጥቅሙ ሲያልቅ መርገጥና መክደት እንደ "ስትራቴጂ" እንጂ እንደ ነውር አይታየውም። በንግዱም ሆነ በማህበራዊ ህይወቱ ሰውን አታልሎ ሲያተርፍ "እንዴት አታለልኩት?" ብሎ ህሊናው አይወቅሰውም፤ ይልቁንም "የዋህ ስለሆነ ነው፣ "መቼም ቢሆን አይነቃም" ብሎ በራሱ ብልጥነት ይደሰታል።

ለጥቅም ሃይማኖትንና እሴትን መጠቀም፦ ለሰዎች ሲናገር ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ሀገር በከፍተኛ ስሜት ሊሰብክ ይችላል። ነገር ግን ያንን የሚያደርገው ሰዎችን ለማደንዘዝ እና ከጀርባ የራሱን ድብቅ ጥቅም (ገንዘብ፣ ወሲብ፣ ስልጣን) ለማግኘት ነው። ጥቅሙ እስከተገኘ ድረስ የትኛውንም የተቀደሰ እሴት ለማርከስ ወደኋላ አይልም።

ባህሪ 5፦ ካልደረሰባቸው በስተቀር መረዳት አለመቻል

ይህ ባህሪ የሰው ልጅ ገና በመጀመሪያው የእንስሳነት ደረጃ ላይ መሆኑን ያሳያል። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ፣ ረሃብ፣ ስደት ወይም ስብራት በምክንያትና

በዕውቀት መረዳት በፍጹም አይችልም። እሱን መረዳት የሚችለው ደመነብስ ፈቅዶ እራሱ ያንን መከራ ሲቀምሰው ብቻ ነው።

ልክ አንድን ጌም ስንጫወት ሌቭል 1ን ሳንጨርስ ዘለን ሌቭል 10 ላይ መጫወት እንደማንችለው ሁሉ፣ በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው አእምሮም ሌላውን ለመረዳት የሚያስችለው "ሌቭል" ገና አልተከፈተለትም።

ደመነብስ ነገሮችን የሚያበራበት የራሱ የጊዜ ሰንጠረዥ አለው። ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ገና ሀብታም እና ጤነኛ እያለ፣ የድሆች መራብ ወይም የበሽተኞች ስቃይ በቲቪ ሲያይ ምንም አይሰማውም። "ሰነፍ ስለሆኑ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ስለቀጣቸው ነው" ሊል ይችላል። ይህ የሚሆነው ክፉ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣አእምሮው ያንን የመረዳት አቅም (Capacity) ገና ስላልከፈተለት "Unlock" ስላላደረገለት ነው።

ከውጭ ሲታይ ሰውየው ጨካኝ፣ ልበ-ደንዳና ወይም ግትር ይመስላል። ሰዎች "ይህ ሰው እንዴት አይራራም? እንዴት አይገባውም?" ብለው ይበሳጨበታል። እውነታው ግን የመረዳት "ሶፍትዌር" (Software) በውስጡ ገና አልተከፈተም። ደመነፍሱ ያንን ክፍል አሽጎታል። ይህ ሰው የሌላውን ህመም እንዲረዳ የግድ እራሱ መታመም፣ እራሱ መደኸየት፣ ወይም የራሱን ልጅ ማጣት አለበት። ልክ መከራው በራሱ ላይ ሲደርስ፣ ደመነፍሱ የ"መረዳት" ሌቭልን ይከፍትለታል (Unlock ያደርገዋል)። ያኔ ብቻ "አሁን ገባኝ!" ይላል።

<u>ባህሪ 6፦ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት</u> (Extreme/Hyper Egoism)

በተፈጥሮ ህግ ውስጥ አንድ እንስሳ ለአንድ አፍታ እንኳን ቢሆን ስለ ሌላው እንስሳ ህልውና አያስብም። ከአንበሳ አፍ ላይ ምግብ የሚቀማው ጅብ፣ አንበሳው እንደሚርበው አያስብም፤ ፍላጎቱ

የራሱን ሆድ መሙላት ብቻ ነው። በዚህ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ያለ የሰው ልጅም ራስ ወዳድነቱ "**እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል** " የሚል እጅግ ጥሬ እና እንስሳዊ ነው። ይህ ባህሪ የሰው ልጅ አእምሮ ከራሱ ስጋ፣ ደምና ፍላጎት ውጭ ያለውን ዓለም ማየት የማይችልበት የመጨረሻው የእንስሳዊነት መገለጫ ነው። በእሱ እይታ እሱ የአጽናፈ ሰማይ ማዕከል ነው፤ የቀረው ሰው ሁሉ ለእሱ ፍላጎት ማርኪያ የተፈጠረ "ዕቃ" ወይም "መሣሪያ" ብቻ ነው።

ይህ ሰው መጋዘኑን እህል ሞልቶ፣ ጎረቤቶቹ በርሃብ እያለቁ ቢመለከት ቅንጣት ታህል አይሰማውም። እንዲያውም የሰዎች መራብ ለእሱ እህሉን በውድ ዋጋ የሚሸጥበት "ዕድል" ነው የሚሆነው። የሌሎች ሰዎች ስቃይ ለእሱ የጥቅም ምንጭ ነው። በትዳርም ሆነ በጓደኝነት ውስጥ የራሱ ምኞት፣ የራሱ ክብር እና የራሱ ስሜት ብቻ ነው ቦታ ያለው። አጋሩ ብትታምም፣ ብትሰበር ወይም ብታዝን ግድ የለውም፤ እሱ የፈለገውን እንክብካቤ እና ጥቅም እስካገኘ ድረስ የሌላው ሰው ስብራት አይታየውም። ልክ ጥቅም ማግኘት ሲያቆም ያለምንም ማመንታት ጥሏቸው ይሄዳል።

ልክ እንስሳት ሽንታቸውን አፍስሰው "ይህ የእኔ ክልል ነው፣ ማንም እንዳይደርስ" ብለው ወሰን እንደሚከልሉ ሁሉ፣ በዚህ ደረጃ ያለ ሰውም የራሱን ንብረት፣ የራሱን ስልጣን ወይም የራሱን ሰዎች እንደ ግል ንብረቱ ያያል። ማንም ሰው በእሱ "ግዛት" ውስጥ ገብቶ እንዲበልጠው ወይም እንዲያዝዘው አይፈልግም።

ሁልጊዜ በውስጡ "ሌላው ሰው ሊበላኝ/ሊቀማኝ መጣ" የሚል እንስሳዊ ፍርሃት ስላለበት፣ አስቀድሞ ሰዎችን ማጥቃትና የራሱን ክምችት ማብዛት ይፈልጋል። ይህ ሰው ህይወትን የሚያየው "እኔ ለማሸነፍ ሌላው የግድ መሸነፍ አለበት" በሚል ስሌት ነው። ሁሉም ሰው እኩል የሚበላበትና የሚደሰትበት ዓለም ለእሱ ትርጉም የለውም። እሱ የበላይ ሆኖ ሌላው ሲንበረከክ፣ እሱ ጠግቦ ሌላው ሲራብ ማየት ነው የራሱን ትልቅነት የሚያረጋግጥለት።

ባህሪ 7፦ ኃያልነትን እንደ ጨቋኝነት

በተፈጥሮ ወይም በጫካ ህግ ውስጥ ኃያልነት (Power) ማለት ሌላውን እንስሳ ማስደንገጥ፣ ማሸበር፣ ማሸነፍና መጫን ማለት ነው። አንበሳ ኃያል የሚባለው ደካማውን እንስሳ አድኖ ስለሚበላና ሌሎችን ስለሚያስፈራ ነው። በዚህ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ያለ ሰውም "ኃያልነትን" ከ"ጨቋኝነት" ጋር ያምታታዋል። ለእሱ መሪ ወይም ኃያል መሆን ማለት ሰዎችን በእግር ስር ማሸብለልና ማስጨነቅ እንጂ ሰዎችን ማሳደግ አይደለም። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው አእምሮ "ተፅዕኖ መፍጠርን" እና "ማስፈራራትን" መለየት አይችልም። ኃያልነቱን የሚያረጋግጠው በዙሪያው ያሉ ሰዎችን በማስጨነቅ፣ ነጻነታቸውን በመንፈግ እና በእሱ ጥላ ስር እንዲንቀጠቀጡ በማድረግ ብቻ ነው።

ለምሳሌ፦ አንድ ሰው በስራ ቦታ ላይ ትንሽ ስልጣን ሲያገኝ፣ ሰራተኞቹን በዕውቀትና በቅንነት ከመምራት ይልቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ፣ ሁልጊዜ በማስፈራራት (ከስራ አባርርሃለሁ፣ እቀጣሃለሁ በማለት) የስልጣን ጥሙን ያረካል። ሰራተኞቹ እሱን ፈርተው ሲንቀጠቀጡ እሱ በውስጡ "እኔ እኮ ኃያል ሰው ነኝ" የሚል የእንስሳዊ ኩራት ይሰማዋል።

በቤት ውስጥ እሱ ሲገባ ጭጭ የሚል፣ ልጆቹና ባለቤቱ የሚደነግጡበት አይነት አባት ወይም እናት። ይህ ሰው ቤተሰቡ እሱን በማክበሩ ሳይሆን በመፍራቱ የሚደሰት ሲሆን፣ ይህንን ፍርሃት እንደ ትልቅ ክብርና ኃያልነት ይቆጥረዋል።

ልክ የዱር እንስሳት መንጋ ውስጥ "አልፋ" (Alpha) የሚባለው ጠንካራው እንስሳ ሌሎቹን በጉልበት እያጠቃ የበላይነቱን እንደሚያረጋግጠው ሁሉ፣ በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰውም ማህበራዊ ህይወትን እንደ ጫካ ነው የሚያየው። ለእሱ ምርጫው ሁለት ብቻ ነው፦ **"ጨቋኝ መሆን፣ አሊያም ተጨቋኝ መሆን"**። በመሃል ያለውን

ሰብአዊ፣ ፍቅራዊ እና እኩልነት የተሞላበትን ግንኙነት አእምሮው ሊቀበለው አይችልም። ስለዚህ ተጨቋኝ ከመሆን ለመዳን የግድ ጨቋኝ እና አውሬ መሆን እንዳለበት ያምናል።

ይህ ሰው ሌሎችን የሚጨቁነው ውስጡ ካለው ጥልቅ "የመበለጥ ስጋት እና ፍርሃት" የተነሳ ነው። ሌላው ሰው ነጻነት ካገኘ እሱን የሚቀማው ወይም የሚንቀው ስለሚመስለው፣ የሰዎችን ክንፍ ቀድሞ መስበር የህልውናው ጉዳይ እንደሆነ ያስባል። ሰዎችን ማዳከም ለእሱ እራሱን ማጠናከሪያ ብቸኛው መንገድ ነው።

ባህሪ 8፦ ፈራጅነት

በጫካ ህግ ውስጥ ነገሮች ሁሉ ጥቁር ወይም ነጭ ናቸው። አንድ እንስሳ ሌላውን ፍጡር ሲያይ የሚመዝነው በሁለት መንገድ ብቻ ነው፦ **"ይህ ፍጡር ምግቤ ነው? ወይስ ጠላቴ?"**። በመሃል ያለውን ውስብስብ ማንነት መርምሮ የመረዳት አቅም የለውም። በዚህ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ያለ የሰውም ሰዎችን እና ሁኔታዎችን ያለምንም ጥልቀት፣ በደመነፍስ ተገፋፍቶ ወዲያውኑ ይፈርዳል። እሱ ራሱ "ፍጹም ዳኛ" እንደሆነ ያስባል።

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው አእምሮ የአንድን ሰው ስህተት ወይም ሁኔታ በምክንያት አውጥቶ አውርዶ፣ የሰውን ልጅ ድክመት ተረድቶ ይቅር ለማለት የሚችልበት "ሶፍትዌር" የለውም። ለእሱ ሰዎችን ማውገዝ፣ በምላስ መግደል እና ስም መስጠት የመኖሩ እና የበላይነቱን ማረጋገጫ ዋነኛ መሣሪያው ነው።

አንድ ሰው ስህተት ሲሰራ ቢመለከት፣ የዛን ሰው ሁኔታ ወይም የደረሰበትን ችግር ለማወቅ ከመሞከር ይልቅ ቀድሞ ድንጋይ የሚያነሳው እሱ ነው። ሰዎችን "ሌባ"፣ "አመንዝራ"፣ "ክፉ" እያለ ሲፈርጅ እና ሲያወግዝ በውስጡ ትልቅ እርካታ ያገኛል። ምክንያቱም ሌላውን ዝቅ አድርጎ ሲረግጥ፣ እራሱን በምናቡ "ቅዱስ እና ንጹህ" አድርጎ ስለሚስል ነው።

የሰው ልጅ ህይወት በብዙ ውጣ ውረድ የተሞላ መሆኑን ማየት አይችልም። ለእሱ አንድ ሰው አንዴ ከተሳሳተ ፍፁም ሰይጣን ነው፤ አንዴ ካለፈለት ደግሞ ፍፁም መልአክ ነው። ሰዎችን እንደየባህሪያቸው መመዘን አይችልም፤ በአንድ ድርጊት ብቻ ሙሉ ማንነታቸውን ይፈርዳል።

ልክ አንድ ውሻ የማያውቀው ሰው ሲመጣ "ጠላት ነው" ብሎ ወዲያውኑ እንደሚጮኸው ሁሉ፣ በዚህ ደረጃ ያለ ሰውም ከእሱ የተለየ ሃሳብ፣ የተለየ ባህል ወይም የተለየ እምነት ያለውን ሰው ሲያይ ወዲያውኑ ያወግዘዋል። ይህ ፈራጅነቱ ከእውቀት የመነጨ ሳይሆን፣ ከእሱ የተለየውን ነገር ሁሉ እንደ ህልውና ስጋት (Threat) ስለሚያየው ራሱን ለመከላከል ቀድሞ የሚወረውረው የጥላቻ ፍላጻ ነው።

የመጀመሪያውን የሰው ልጅ ደረጃ **"እንስሳዊውን ማንነታችንን"** በእነዚህ ስምንት ምልክቶች ስንመረምረው፣ የዚህ ደረጃ ዋናው መጋቢ እና አንቀሳቃሽ ኃይል **"ደመነፍስ እና ፍርሃት"** (Instinct and Fear) መሆኑን እንረዳለን።

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ምንም እንኳን የሰው ቅርፅ ቢኖረውም፣ አእምሮው ግን ገና ከጫካው ህግና ከህልውና ለማምለጥ ከሚደረግ ትግል (Survival Mode) አልተላቀቀም።

- **ስለ ሰዎች መጨነቁ፦** ከፍቅር ሳይሆን በቡድን የመታቀፍ ፍላጎት ነው።
- **መንጋነቱ፦** ብቻውን ቆሞ እውነትን የመጋፈጥ አቅም ስለሌለው ነው።
- **ሞራል አልባነቱ እና ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነቱ፦** ህይወትን እንደ "እኔ ካልበላሁ እበላለሁ" ስሌት ስለሚያያት ነው።
- **አለመረዳቱ፣ ጨቋኝነቱ እና ፈራጅነቱ፦** የንቃተ-ህሊናው ደረጃዎች (Levels) ገና "Locked" ስለሆኑና ውስጡ ባለው ጥልቅ ፍርሃት ስለሚመራ ነው። ባጭሩ ይህ ደረጃ የሰው ልጅ ገና የሰውነት

(የሰብአዊነት) ክብር ሳይሰማው፣ በስጋዊ ፍላጎቱና በደመነፍሱ ብቻ ተገዝቶ የሚኖርበት ጥሬና መሠረታዊው ማንነቱ ነው።

ደረጃ2 ሰው

የሰው ልጅ ባህሪን ወደ ሁለተኛው ደረጃ ስናሸጋግር፣ ከእንስሳዊው ደመነፍስ ወጥተን ወደ "**ሰብአዊው ህሊና**" (The Human Consciousness) እንገባለን። ይህ ደረጃ የሰው ልጅ ራሱን፣ ማህበረሰቡን እና የህይወትን ትርጉም በበሰለ መንገድ መመልከት የሚጀምርበት ክፍል ነው።

ባህሪ 1፦ ሞራላዊነት (Morality)

በዚህ በሁለተኛው ደረጃ ላይ የመጀመሪያው እና ዋናው ባህሪ "**ሞራላዊነት**" (Morality / Ethical Living) ነው።
በአንደኛው ደረጃ ላይ የነበረው "ሞራል አልባነት" ተሰብሮ፣ ሰውየው ህይወትን በጥቅም ብቻ ሳይሆን **በትክክለኛነት፣ በፍትሃዊነት እና በህሊና ሚዛን** መምራት ይጀምራል።

ይህ ሁላችንም ከመሞታችን በፊት ልንደርስበት የሚገባው ውቡ እና ትክክለኛው ማንነታችን ነው ሰው መሆን የሚቻለው በጥረት ነው በተፈጥሮ ብቻ አይደለም እኔ በግሌ ካሉት ከ 4ቱ ደረጃዎች አስበልጬ የምወደው እና ልደርስበት የምፈልገው ደረጃ ነው ሰው ማለት

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው "ይህ ለእኔ ምን ጥቅም አለው?" ብሎ ከመጠየቁ በፊት "**ይህ የምናገረው ወይም የማደርገው ነገር ትክክል ነው ወይስ ስህተት?**" ብሎ ራሱን ይጠይቃል። ሞራል ለእሱ ከውጭ የመጣ የማስገደጃ ህግ ሳይሆን፣ ከውስጡ የሚፈልቅ የህሊና ድምፅ ነው።

በአንደኛው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ሰው ሲያየው ብቻ ነበረ መልካም የሚሆነው። በዚህ በሁለተኛው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ግን ማንም ሰው እንደማያየው እያወቀ፣ ህግ እንደማይደርስበት እያረጋገጠ እንኳን ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል።

ይህ ሰው ሌሎችን ሰዎች እንደ ራሱ እኩል ፍጡር አድርጎ ይመለከታል። "እኔ እንዲደረግልኝ የማልፈልገውን ነገር በሌላው ላይ አላደርግም" የሚለውን ወርቃማ ህግ (Golden Rule) በተግባር ይኖረዋል።

በንግድም ሆነ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ "እኔም ልኑር፣ ሌላውም ይኑር" (Win-Win) የሚል መርህ አለው። በአንደኛው ደረጃ እንደነበረው የሰዎችን ድካም መበዝበዝ ሳይሆን፣ ሰዎችን በደመወዛቸውና በላባቸው ልክ በአክብሮት መክፈልና መያዝ የሞራል ግዴታው እንደሆነ ያምናል።

በእንስሳዊው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ጥፋት ሲያጠፋ ራሱን ለመከላከል ይጮኻል ወይም በሌሎች ላይ ያሳብባል። በሞራላዊው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ግን ስህተት ሲሰራ ውስጣዊ ፀፀት (Guilt) ይሰማዋል። ያለ ምንም እብሪት "አጥፍቻለሁ፣ ይቅርታ" ብሎ ጥፋቱን ያምናል፤ የተበላሸውን ነገር ለመካስና ሰዎችን ለመጠገን በቅንነት ይንቀሳቀሳል። ይህ የፀፀት አቅም የሰው ልጅ ትልቅ የሞራል ደረጃ ላይ መድረሱን ማረጋገጫ ነው።

የሌሎችን ስሜት መረዳት ይህ ባህሪ በአንደኛው ደረጃ ላይ የነበረውን "በራሱ ላይ ካልደረሰ መረዳት አለመቻልን" (የተቆለፈውን አእምሮ) ሙሉ በሙሉ ሰብሮ የሚወጣ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ የሰው ልጅ አእምሮ ከራሱ ስጋና ፍላጎት ወጥቶ፣ በምናቡ (imagination) የሌላውን ሰው ጫማ ተጫምቶ መጓዝ ይጀምራል። የሌላው ሰው ህመም፣ ደስታ፣ ፍርሃትና ስብራት ልክ በራሱ ላይ እንደደረሰ አድርጎ የማስተዋል ጥልቅ ሰብአዊ አቅም አለው።

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው የሰዎችን ሁኔታ ለመረዳት የግድ ያ መከራ እራሱ ቤት እስኪኳኳ ድረስ አይጠብቅም። የሌላውን ሰው እንባ ሲያይ እንባው ይተናነቀዋል፤ የሌላውን ስብራት ሲመለከት ውስጡ ያዝናል፤ ያንን ሰው ለመርዳትና ስሜቱን ለመጋራት ይንቀሳቀሳል።

በአንደኛው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ድሆችን "ሰነፍ ስለሆኑ ነው" ብሎ ሲንቅ፣ በዚህ በሁለተኛው ደረጃ ላይ ያለ ሰው ግን ያ ሰው ያሳለፈውን ከባድ ህይወት፣ የገጠመውን ፅድል እና የውስጥ ስብራት ለማሰብ ይሞክራል። "እኔስ በሱ ቦታ ብሆን ኖሮ?" ብሎ ራሱን ይጠይቃል። ይህ አስተሳሰብ ከጭካኔ ይልቅ ርህራሄን፣ ከፍርድ ይልቅ መደገፍን በውስጡ ይወልዳል።

ከሰዎች ጋር ሲነጋገር የራሱን ሃሳብ ብቻ ለመጫን አይጣደፍም። የፊታቸውን መለዋወጥ፣ የአይን አገላለጻቸውን እና ድምፃቸውን አይቶ "ውስጣቸው ምን እየተሰማቸው ነው?" ብሎ በንቃት ያስተውላል። በአንድ ነገር ተከፍተው ከሆነ፣ ህመማቸውን ሳያቃልል "እንደሚከብድ ይገባኛል፣ ካንተ ጋር ነኝ" በማለት ስሜታዊ ዋስትና (Emotional Validation) ይሰጣቸዋል።

ባህሪ 2፦ ከደመነፍስ ፍርሃት ወደ ሰብአዊ ፍቅር መሻገር

በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ሰው የተለየ ባህል ወይም እምነት ያለው ሰውን ሲያይ እንደ "ጠላት" ፈርቶ ይጮኽ ነበር። በዚህ በሁለተኛው ደረጃ ላይ ግን ሰውየው ሰብአዊነትን ያስቀድማል። "ቋንቋው፣ ብሄሩ ወይም ሃይማኖቱ ከእኔ ቢለይም፣ እሱም እንደ እኔ የሚርበው፣ የሚጠማው፣ የሚደሰተውና የሚያዝነው ሰው ነው" ብሎ ያስባል። ልዩነቶችን አልፎ እውነተኛውን ሰብአዊ ማንነት የመመልከት አይን አለው።

የዚህ ደረጃ መገለጫው እርዳታው ወይም አጋርነቱ ከጀርባው ምንም አይነት የግል ጥቅም (ዝና፣ ስልጣን ወይም ውለታ) የሌለበት መሆኑ ነው። ይህ ሰው መንገድ ላይ የወደቀን አቅመ-ደካማ ወይም ህጻን ሲረዳ ቪዲዮ ቀርፆ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ለመጫን ወይም "ደግ" ለመባል አይጓጓም። የሌላው ሰው ከስቃይ መውጣት የሚሰጠው የውስጥ እርካታ ብቻ ለእሱ በቂ ክፍያው ነው።

ይህ ሰው በአለም ሌላኛው ጫፍ ላይ የሚገኙ ህዝቦች በጦርነት፣ በበሽታ ወይም በተፈጥሮ አደጋ ሲሰቃዩ ሲሰማ የራሱ ሀገር ወይም ቤተሰብ ላይ እንደደረሰ አድርጎ ይተክዛል። "ሰው በመሆኔ ብቻ የሰው ልጅ ህመም ያመኛል" የሚል ሰፊና አጽናፈ-ዓለማዊ ልብ አለው።

ባህሪ 3፦ ጠያቂና ፈላስፋነት

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ከመንጋው አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ይወጣል። ትኩረቱና ጭንቀቱ የእለት ተእለት የሰዎች ወሬ ወይም ጭብጨባ ሳይሆን **ረቂቅ ለሆኑ ሃሳቦች፣ ለዓለም እውነቶች እና ሊወራላቸው ለሚገቡ ትልልቅ ጉዳዮች** ይሆናል። ይህንን ጠያቂነቱን እና ፈላስፋነቱን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፦

1. መደበኛ ፈላስፋነት

ይህ የመጀመሪያው ክፍል ሲሆን ፈላስፋው በዙሪያው ባለው ዓለም ላይ "እንዴት?" የሚል ጥልቅ ጥያቄ ያነሳል፤ ጥያቄው በቀጥታ በሳይንስ የማይመለስ በመሆኑም የራሱን መላምት (Hypothesis) ያስቀምጣል።

2. የላቀ ፈላስፋነት

ይህ ሁለተኛው እና የላቀው ክፍል ነው። ፈላስፋው ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ጥያቄ ቢያነሳም፣ የሚያነሳው ጥያቄ ግን ከእሱ በፊት በነበሩት ማህበረሰቦችም ሆነ ሊቃውንት በፍጹም ታስቦና ተጠይቆ የማያውቅ አዲስ በር የሚከፍት ነው

በአንደኛው ደረጃ ላይ የሰው ልጅ ጭንቀት በሙሉ "ሰዎች ምን አሉኝ? ያ ሰው ይወደኛል ወይስ ይጠላኛል?" በሚል የእንስሳዊ የደህንነት ፍርሃት ላይ የተመሰረተ ነበር። በዚህ በሁለተኛው (በሰው) ደረጃ ላይ ግን የሰውየው ጭንቀት ስለ ሃሳቦች ይሆናል።
ሊወራላቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ባህሪ 4፦ ትርጉም ፈላጊነት

ይህ ባህሪ የሰው ልጅ ከእንስሳዊው የመኖር ግብ (ለመብላት፣ ለመራባትና ለመትረፍ ብቻ ከመኖር) ሙሉ በሙሉ ተላቆ፣ ለህይወቱ ጥልቅ የሆነ ሰብአዊ መሠረት የሚጥልበት ክፍል ነው። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ቁሳዊ ምኞት፣ ስልጣን ወይም ዝና ስላለው ብቻ አይረካም። "የመኖሬ ትርጉም ምንድነው? ይህንን ምድር ሳልፍ ምን አሻራ ጥዬ እሄዳለሁ?" ብሎ ሌሊትና ቀን ይጨነቃል።

የኦስትሪያው የነርቭ ሐኪም እና የሳይካትሪ ባለሙያ ቪክቶር ፍራንክል በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በናዚ የህዝብ ማጠቃለያ ካምፖች (Concentration Camps) ውስጥ እጅግ አሰቃቂ መከራዎችን አሳልፏል። በዚያ የሞት ቀጠና ውስጥ ሆኖ ያስተዋለው ትልቅ እውነት አለ፦ “በረሃብና በበሽታ ቀድመው የሞቱት አካላቸው ደካማ የነበሩት ሳይሆኑ፣ የመኖር "ትርጉማቸውን" ያጡት ነበሩ።” **የታወቀው መጽሐፉ እና ፍልስፍናው፦** ፍራንክል ከካምፑ ከወጣ በኋላ "Man’s Search for Meaning" (*"የሰው ልጅ ትርጉምን የመፈለግ ጉዞ"*) የተሰኘውን ዓለም አቀፍ ዝነኛ መጽሐፉን ጻፈ። በእሱ ፍልስፍና (Logotherapy)

መሠረት፣ የሰው ልጅ ዋናውና መሠረታዊው አንቀሳቃሽ ኃይል ስልጣን ወይም ደስታ ሳይሆን "ትርጉምን መፈለግ" ነው።

የጀርመናዊውን ፈላስፋ የፍሬድሪክ ኒቻን (Friedrich Nietzsche) ሃሳብ በመዋስ እንዲህ ይላል፦ "He who has a why to live for can bear almost any how."

(*"የመኖሩን 'ለምን' ትርጉም የሚያውቅ ሰው፣ የትኛውንም አይነት 'እንዴት' መከራ ሊቋቋም ይችላል።"*)

ባህሪ 5፦ ኃላፊነት

በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ኃላፊነትን የሚያየው እንደ ሸክም ሳይሆን፣ የሰውነቱ መገለጫ አድርጎ ነው። ይህ ኃላፊነት ረቂቅ ከሆኑ ሃሳቦች አልፎ፣ በተግባር ምድር ላይ የሚታይ ቁሳዊ ስኬትን የመፍጠር እና የመታደግ ግዴታ ነው።

እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅ፦ **በህይወታችሁ ማሳካት የምትፈልጉት ዓላማ ምንድነው?**

ትንሽ ቆም በላችሁ አስቡት...**ቤት መግዛት፣ ዘመናዊ መኪና መንዳት፣ የተደላደለ ጥሩ ህይወት መኖር እና ደስተኛ ቤተሰብ መመስረት ነው መልሳችሁ** ?

በሚያሳዝን ሁኔታ የአበዛኞቻችን መልስ ይሄው ነው፣እውነታው ግን እኛ **ገና ዓላማ የለንም ማለት ነው!**

ይህ የምንመኘው ነገር ሁሉ እኮ ማንም ሰው ሊኖረው የሚገባ እጅግ "ተራ ነገር" ነው። ልክ አንዲት ትንሽ ፍሬ ምድር ላይ ስትዘራት፣ የዛች ፍሬ የመጀመሪያ ሩጫ ስሯን ወደ መሬት መስደድና ህልውናዋን ማቆየት እንደሆነው ሁሉ፤ ይህ ራስን የመቀለብና

የመኖር ፍላጎት ተራ የተፈጥሮ ህግ ነው። ሁሉም ፍሬ (ሁሉም ፍጡር) ሊያደርገው የሚገባ ግዴታ ነው።

ነገር ግን የአንድ ፍሬ እውነተኛ ሩጫና የመጨረሻ ዓላማ ስሯን መሬት ውስጥ ሰድዳ መቅረት ብቻ ሊሆን አይችልም። የዛች ፍሬ እውነተኛ ዓላማ የምድርን ከባድ ድንጋይና አፈር ሰንጥቃ መውጣት፣ ግንድ መሆን፣ ቅርንጫፍና ቅጠል ማውጣት፣ ማበብ፣ ማፍራትና በመጨረሻም ፍሬዋን ለዓለም አበርክታ **ዓለምን መመገብ** ነው!

እኛም የሰው ልጆች እንዲሁ ነን! ዓላማችን ከተራ ቤትና መኪና ምኞት በላይ ሊሆን ይገባል። እንዲህ በትንሽ ነገር እንድንረካና እንድንታሰር የሚያደርገንን ያንን (የእውቀት)የውስጥና (የገንዘብ) የውጭ ድህነት ሰብረን መውጣት አለብን። ራሳችንን፣ ቤተሰባችንንና ማህበረሰባችንን ከውድቀትና ከችጋር የመታደግ እና የመትረፍ ታላቅ ኃላፊነት አለብን።

እውነተኛ "ሰው" ማለት ይህ ነው! ከደረቅ ሃሳባዊ ፍልስፍና ባለፈ፣ በተግባር ምድር ላይ የሚታይ፣ ሌሎችን የሚታደግበት እና ዓለምን የሚቀይርበት **ላቅ ያለ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ስኬት** ያለው ነው።

ደረጃ 3 ታላቁ ሰው

በዚህ ምዕራፍ የምናየው እኛ ሰዎች እንዴት እያደግንና እየተለወጥን እንደምንሄድ ነው። የዚህ ሃሳብ መነሻ ፍሬድሪክ ኒቻ ከተባለው ታዋቂ ፈላስፋ እሳቤ ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም፣ እኔ ግን ሃሳቡን የተወሰነ አሻሽዬ ነው ያቀረብኩት። ኒቻ “ሰው ማለት በእንስሳ እና በታላቁ ሰው (Overman) መካከል ያለ ገመድ ወይም ድልድይ ነው” ይላል። እሱ ሰውን እንደ መሸጋገሪያ መስመር ብቻ ነው ያየው።

ነገር ግን እዚህ መሃል ላይ አንድ የጎደለ ትልቅ ነገር እንዳለ ተሰማኝ።

አንድ ሰው ከእንስሳዊ ባህሪ ተነስቶ በቀጥታ ወደ ታላቁ ሰው ሊዘል አይችልም። በመሃል ላይ “ሰው” የመሆን ራሱን የቻለ ትልቅ ደረጃ አለ! ለዚህ ነው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ሰውን” ለብቻው አንድ ደረጃ አድርጌ ያስገባሁት።

ባህሪ 1፦ ፈጣሪነት

"ሰውን ፈጣሪ" ማለት በብዙዎቻችን ዘንድ ፍርሃትንና መደናገጥን ይፈጥራል። "ኧረ እዛው ራስህን ችለህ ተቀሰፍ! ላንተ የወረደው መብረቅ ለእኛም እንዳይተርፈን!" ያስብላል። እኔም ብሆን በዚህ ፍርሃት እስማማለሁ፤ ነገር ግን እኔ "መፍጠር" ስል ስለ ምን ማውራት እንደፈለግኩ ሳስረዳችሁ ምን ለማለት እንደፈለኩ ትረዳላችሁ።

እኔ መፍጠርን በሁለት ከፍዬ አየዋለሁ፦ ካለመኖር ወደ መኖር እና ከመኖር ወደ መኖር

1. ካለመኖር ወደ መኖር (Creation ex nihilo)፦ ይህ ስም ሲነሳ ቀጥታ አእምሯችን ላይ የሚመጣው መለኮታዊው የመፍጠር መንገድ ነው። ከዚህ ቀደም በፍጹም ያልነበረን ነገር ከምንም ተነስቶ ህልው እንዲሆን ማድረግ ነው።

ለመምሳሌ በስነ-ፍጥረት ላይ የተጠቀሱት አራቱ መሠረታዊ ባህርያት (እሳት፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ መሬት) የተፈጠሩት በዚህ መንገድ ነው።

2. ከመኖር ወደ መኖር (Re-creation)፦ ይህኛው ደግሞ እኔ ልነግራችሁ የፈለግኩት፣ የታላቁ ሰው ምልክት የሆነው መንገድ ነው። ይህም አስቀድመው የተፈጠሩ ነገሮችን በመጠቀም አዲስ፣ ከዚህ ቀደም የሌለ ነገር መፍጠር ነው። ለዚህም የገዛ የራሳችን

አፈጣጠር በቂ ምሳሌ ነው፤ አስቀድመው ከነበሩት ከአራቱ ባህርያት (እሳት፣ መሬት፣ ነፋስ፣ ውሃ) እና በሦስቱ ባህርያተ ነፍስ ተዋህዶ፣ ከዚህ ቀደም በስነ ፍጥረት ላይ ያልነበረው "ሰው" የተባለው አዲስ ፍጥረት ሊገኝ ችሏል። ይህንን ሁለተኛውን መንገድ ግልጽ ለማድረግ "ዳግም-ፈጠራ" (Re-creation) ብለን ብንጠራው ይቀላል።

ነገር ግን እዚህ ጋር አንድ ችግር ይፈጠራል እሱም ሐሳብ ነው። በሃሳቡ ዓለም ውስጥ ከዚህ ቀደም የነበረን ቁስ ሳንጠቀም አዲስ ነገር መፍጠር እንችል ይሆን ? አእምሮአችን ላይ ሁሉንም ነገር ከምንም ነገር ተነስተን መፍጠር ይቻላልና።

ለምሳሌ ስልክን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠረው ሰው፣ መጀመሪያ በአእምሮው ውስጥ ነው የፈጠረው ይህንንም ለማድረግ ምንም አይነት ቁሳዊ ነገር አይጠቀምም፣ ሙሉ በሙሉ በምናቡ ዓለም ውስጥ ከምንም ተነስቶ (ካለመኖር ወደ መኖር) ነው የሳለው። ታዲያ እንደዛ ከሆነ የመጀመሪያውን የአፈጣጠር መንገድ እንችላለን ማለት ነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሰፋ ባለ መልኩ ላስረዳችሁ

የህይወት ታሪኬ ላይ እንዳስነበብኳችሁ፣ ለሁለት ዓመታት ያክል ያለምንም ስልክ፣ ኢንተርኔትና ትምህርት አሳልፌያለሁ። ታዲያ ያንን ሁሉ ትርፍ ጊዜ ምን እያደረግኩ የማሳልፈው ይመስላችኋል? የሚገመት ነው፤ የባጥ የቆጡን በማሰብ፣ በማሰላሰልና በመፈላሰፍ ነበር። በርግጥም በርከት ያሉ ጥልቅ የፍልስፍና ውጤቶች ላይ ደርሼ ነበር፤ ራሴንም እንደ ታላቅ ፈላስፋ ነበር የማየው። ያገኘኋቸውን ፍልስፍናዎችም መፃፍ ጀምሬ ነበር።

ነገር ግን አገር ሰላም ሆና ኢንተርኔት ማግኘት ስጀምር መረጃዎችን ማሰስ ያዝኩ። በዚህ ጊዜ ነበር ያልጠበኩት ነገር ያገኘሁት፤ እኔ የራሴ የሃሳብ ውጤቶች ናቸው ያልኳቸውን ፍልስፍናዎች፣ ታላላቅ የዓለም ሊቃውንት ቀድመውኝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ደርሰውባቸው አገኘኋቸው! ለምሳሌ አሁን የምፅፍላችሁን "ታላቁ ሰው" (The Overman) የተሰኘውን ማንነት፣ ያኔ መምህሬ ብዬ

የጠራሁትን ምናባዊ ሰው በ ፍሬድሪክ ኒቾ (Friedrich Nietzsche) ካስቀመጠው ባህሪ ጋር ተቀራራቢ ሆኖ አገኘሁት። ሁኔታው በጣም አስገርሞኝ "የሚገርም አጋጣሚ" ብዬ አለፍኩት።

ነገር ግን ነገሩ እየተደጋገመ መጣ አብዛኛውን ሐሳቦቼን ሌሎች ሰዎች ደርሰውበታል፣ በስተመጨረሻ ከእኔ በስተቀር ማንም ያልደረሰበት ሙሉ በሙሉ ንፁህ የሆነና በራሴ ስም የሚጠራ አዲስ "የቋንቋ ፍልስፍና" ብዬ የጠራሁትን አገኘሁ አልኩ እና በጣም ደስ ብሎኝ መፃፍ ያዝኩኝ፣ እንደተለመደው ሉድቪግ ቪትገንስታይን (Ludwig Wittgenstein) የተባለው ኦስትሪያዊ ፈላስፋ ገና በ20ኛው ክፍለ ዘመን ቀድሞኝ እንደፃፈው አወኩ! በጣም ነበር ያናደደኝ። "እዚህ ጋር የሆነ ልክ ያልሆነ ነገር አለ!" አልኩኝ። እሱን ለማወቅ ባደረግኩት ምርምር ነው አሁን ለእናንተ ወደማብራራላችሁ መደምደሚያ ላይ የደረስኩት።

የሃሳብ ዓለም

ሃሳብ ራሱን የቻለ የተለየ ዓለም ነው። በውስጡ እጅግ በጣም ሰፊና ማለቂያ የሌላቸው ነገሮች ያሉበት እውነተኛ ዓለም። እኛ ማሰብ ስንጀምር፣ ወደዚያ የሃሳብ ዓለም ውስጥ እንገባለን፤ እዚያ ዓለም ውስጥ ያገኘነውን ነገር ደግሞ ፈልፍለን ወደ እውነተኛው ቁሳዊ ዓለም እናመጣዋለን። ነገር ግን እኛ አገኘነው እንጂ፣ ያ ነገር አስቀድሞ በዚያ በሃሳብ ዓለም ውስጥ የተፈጠረና የነበረ ነገር ነው። ይህንን በምሳሌ ሳስረዳችሁ፡ የመጀመሪያው ሰው በአንድ የዓለም ጥግ (ለምሳሌ አፍሪካ ውስጥ) ሆኖ እሳትን ቢፈጥር፣ ከመጀመሪያው ሰው ጋር ምንም አይነት ግንኙነትና ትውውቅ የሌለው በሌላ የዓለም ጥግ (ለምሳሌ አሜሪካ ውስጥ) ያለ ሰው በተመሳሳይ መልኩ እሳትን ይፈጥራል። ሊኖር የሚችለው ልዩነት እሳቱን ለመፍጠር የተጠቀሙበት መንገድ ብቻ ነው፤ መነሻ ሃሳቡ ግን አንድ ነው።

አንድን ሰው "ፈጣሪ" የምንለው፣ በዚያ በሃሳብ ዓለም ውስጥ "የመጀመሪያው ተጓዥ" ሲሆን ነው፤ ከዚህ ቀደም ማንም ያልረገጠውን አዲስ መንገድ ብቻውን ሄዶ አዲስ ሃሳብ ይዞ ሲመጣ፤ ያ ሀሳብ ግን አስቀድሞ የነበረ ነው ካለ መኖር ወደ መኖር ያመጣው አይደለም እሱ ባይሄድበት እንኳ ሌላ ሰው ያንን መንገድ ተከትሎ ቢጓዝ በትክክል ያንኑ ተመሳሳይ ውጤት ላይ ይደርሳል ልክ በእኔና ቪትገንስታይን ላይ እንደሆነው ማለት ነው።

ነገር ግን አንዳንዴ የሰዎች ፈጠራ የመደጋገም ዕድሉ በጣም የጠበበ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ እንደ ስዕል ወይም ልብ-ወለድ መጽሐፍ ያሉ የጥበብ ስራዎችን ብንወስድ፤ ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ "ሞናሊዛን" (Mona Lisa) ባይስላት ወይም ፊዮዶር ዶስቶየቭስኪ "ወንጀልና ቅጣት" (Crime and Punishment) የተሰኘውን ልብ-ወለድ ባይፅፈው ኖሮ፣ ሌላ ሰው ያንን በትክክል አንድ አይነት ስራ የመስራት ዕድሉ እጅግ በጣም ጠባብ ነው።

ይህ ለምን ይሆናል? ምክንያቱም የሃሳብ ዓለም እጅግ በጣም ሰፊ በመሆኑና እነዚያን ሃሳቦች እርስ በርስ ለመገጣጠም በቁጥር የማይገለፅ ሰፊ አማራጭ ስላለን ነው። ለምሳሌ 8 በ 8 በሆነችው የቼዝ (Chess) ሰሌዳ ላይ ብቻ፣ እያንዳንዱ ሊደረግ የሚችል እርምጃ (possible move) ከበስተጀርባው 40-52 ዜሮዎች ያሉት ቁጥር ያህል ሰፊ አማራጭ አለው። በትንሿ ቼዝ ሰሌዳ ላይ ይህን ያክል አማራጭ ካለ፣ በሰፊው የሃሳብ ዓለም ውስጥ ምን ያህል ማለቂያ የሌለው አማራጭ እንደሚኖር መገመት ቀለቀል ነው! በተመሳሳይ መልኩ እኔ የለሁም ብልስ የሀሳቡ አለም ውሸት ነው ማለት ነው ምክንያጡም እኔ አለኋ። ይህ የሚሆነው በሃሳቡ አለም ውሰጥ በመጓዝ ሳይሆን ቃሌ ህግ ይሁን የሚል ቃላትን የመገጣጠም ጨዋታ ነው ለዚህም ሬኔ ዲካርስ “I Think Therefore I Am (አስባለሁ ስለዚህ አለሁ)” ሲል ታሪካዊ ምላሽ ሰጥቶበታል

በሀሳቡ አለም ውስጥ ያሉ ነገሮች አስቀድመው የነበሩ ነገሮች መሆናቸውን ካየን ባለቤታቸው ማን እነደሆነ ማወቅ ይቻላል "እግዚአብሔር" ነገር ግን እዚህ ጋር አነድ ችግር ይፈጠራል እጅግ በጣም አረመኔአዊ እና ሰይጣናዊ ሀሳቦች ታዲያ ከየት ይመጣሉ?የእነሱ ባለቤት ማነው? እግዚአብሔር እንዳንል ሰይጣናዊ ናቸው ታዲያ ሰይጣን ይፈጥራል ማለት ነው ? መልሱ አይደለም ነው ። እንዴት እንደሆነ ላስረዳችሁ ማንኛውም ነገር በውስጡ የማይነጣጠሉ ተቃራኒ ኃይሎች አሉት ይህንንም ልክ እንደ ሒሳቡ ዓለም Negative (-) እና positive (+) ማየት ይቻላል ። የሰይጣን ስራ የሚሆነው ነገሮችን ወደ -ve መቀየር ነው ለምሳሌ አንድን ስለታማ ነገር ተጠቅመን ምግብ ልናዘጋጅበት እንችላለን በተመሳሳሳ መልኩ ይህንኑ ስለታማ ነገር ተጠቅመን ነፍስ ልናጠፋበት እንችላለን፤ በዚህ መልኩ ነው በሀሰቡ ዓለም ውስጥ ሰይጣናዊ ሀሳቦች ሊኖሩ የቻሉት ።

እኛ የሰው ልጆች ይህንን ሰፊ ዓለም መዳሰስ የምንችለው "ቋንቋ" እስከፈቀደልን ድረስ ብቻ ነው። እርስ በርስ ለመግባባት የምንጠቀመው መደበኛ ቋንቋ አልበቃ ሲለን፣ ይህንን ሰፊ ዓለም ይበልጥ ለመጎብኘት ስንል አዳዲስ ቋንቋዎችን መፍጠር ችለናል። የሒሳብ (Mathematics) እና የፊዚክስ (Physics) ቋንቋዎች የሃሳብን ዓለም ይበልጥ በጥልቀት እንድንመረምር የረዱን መሣሪያዎቻችን ናቸው። ስለዚህ የእውቀታችንና የፈጠራችን ትልቁ ገደብ ራሱ ቋንቋ ነው። ቋንቋ እስከፈቀደልንና በቃላትና በምልክቶች መግለፅ እስከቻልን ድረስ በሃሳብ ዓለም ውስጥ እንደ ልብ መንሸራሸር እንችላለን።

በብዙዎች ዘንድ የሚያከራክር ነገር አለ። በአንድ ወገን "ይህ የፈጠራ ስራ ነው" ሲሉ፣ በሌላ ወገን ደግሞ "አይደለም፣ ሰው መፍጠር አይችልም፤ ግኝት (Discovery) ነው መባል ያለበት" ይላሉ። እውነታው ግን ሰው መፍጠር ይችላል! ነገር ግን እንደ መለኮቱ ካለመኖር ወደ መኖር ሳይሆን፣ ከላይ እንዳየነው ከመኖር ወደ ከመኖር (ዳግም-ፈጠራ) ነው። ቅድም እንዳልኩት፣ ፈጣሪ የሚባለው

ሰው በሃሳብ ዓለም ውስጥ የሚጓዝ የመጀመሩሪያ አሳሽ ነው። በዚያ ዓለም ውስጥ ለመጓዝ አስቀድሞ ምድር ላይ የነበረን ቁስ ስለማይጠቀም፣ ያመጣው ሃሳብ "ካለመኖር ወደ መኖር" የመጣ ይመስለናል። ነገሩን በጥልቀት ስናየው ግን፣ በሃሳቡ ዓለም ውስጥ እሱ "አግኚ ወይም አሳሽ" ነው፤ ያንን ያገኘውን ረቂቅ ሃሳብ ወደ እውነተኛው ቁሳዊ ዓለም አምጥቶ፣ አስቀድመው ባሉ ቁሶች ዳግም ሲሰራው ግን "ፈጣሪ" ይሆናል።

ይህ ዳግም-ፈጣሪነት ነው እንግዲህ፣ የታላቁ ሰው ዋነኛ እና አንደኛው

<u>ባህሪ 2፦ ጠቢብነት</u>

እስካሁን ያየናቸውን ደረጃዎች መለስ ብለን ስንቃኛቸው አስገራሚ ጉዞ እናገኛለን። መጀመሪያ ከእንስሳነት ደረጃ ተነሳን፤ በዚያ ደረጃ ላይ ጉዳያችን (ትኩረታችን) ሰዎችና ጥቃቅን ነገሮች ብቻ ነበሩ። ከዚያም ወደ ሰውነት ደረጃ ደረስን፤ እዚያ ደግሞ ትኩረታችን በዙሪያችን ያሉ ሁኔታዎች ሆኑ። በእነዚያ ሁኔታዎች ላይ ተፈላሰፍን፣ መገመትም ጀመርን። አሁን ግን ተጉዘን ተጉዘን ታላቁ ሰው ላይ ደርሰናል። ይህ ሰው “ጠቢብ” ነው።

እኔ ጠቢብ ስል ከፈላስፋ የተለየ ማለቴ ነው። ፈላስፎች ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፣ መልሱን ግን በትክክል አያውቁትም። ስለዚህ የራሳቸውን ግምት ያስቀምጣሉ፤ ይህ ግምታቸው ደግሞ እርስ በርሳቸው የተለያዩና በአንድ ሀሳብ ላይ ፀንተው እንዳይቆሙ ያደርጋቸዋል። ታላቁ ሰው ግን ጠቢብ ነው መልሱን ያውቀዋል። በተጨማሪም ጠቢብ ስንለው ብልህም ጭምር ነው።

በጥበቡ ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ንጉሥ ሰሎሞን ዝነኛ የሆነበት አንድ አስደናቂ ታሪክ አለ። (ሁለት እናቶች በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሁለቱም በቅርብ ቀናት ውስጥ ህፃናት ልጆችን ወለዱ።

ነገር ግን አንደኛዋ እናት በሌሊት ተኝታ ሳታስበው ልጇ ላይ ተኝታበት ይሞታል። ከዚያም በሌሊት ተነስታ የሞተውን ልጇን በሕይወት ካለው የሌላኛዋ እናት ልጅ ጋር ትቀይረዋለች።

ጠዋት ሲነጋ "ልጹ የአንቺ ነው የሞተው፣ ያንቺ ነው የሞተው" በሚል በመካከላቸው ትልቅ ጠብ ተነሳ። ጉዳዩም እስከ ንጉሥ ሰሎሞን ችሎት ድረስ ደረሰ። ሁለቱም "ሕያው የሆነው ልጅ የእኔ ነው" እያሉ ይከራከሩ ነበር።

በዚህ ጊዜ ሰሎሞን እውነተኛዋን እናት ለማወቅ አንድ ብልሃት ተጠቀመ። ወታደሮቹን "ሰይፍ አምጡና ሕያውን ሕፃን ለሁለት ሰንጥቃችሁ ለእያንዳንዳቸው ግማሽ ግማሽ ስጧቸው" የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ።

እውነተኛዋ እናት ልጇ እንዲሞት ስላልፈለገች በድንጋጤ አልቅሳ "እባክህ ጌታዬ አትግደለው፣ ለእሷው ስጣት" አለች። ሐሰተኛዋ እናት ግን "ለእኔም አይሁን ለአንቺም አይሁን፣ ይቆረጥ" አለች። በዚህ ጊዜ ሰሎሞን እውነተኛዋ እናት ልጇ እንዲሞት የማትፈልገዋ መሆኗን አወቀና ልጹን ለእሷ ሰጣት።)

እዚህ ጋ በግልጽ እንደምናየው፣ ጥበብ ማለት ዝም ብሎ መመራመር ሳይሆን "ዓላማህን ለማሳካት የምትሄድበት ብልሃታዊ መንገድ" ነው። ታላቁ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ለሚገጥሙት ውስብስብ ጥያቄዎች ግምትን ሳይሆን፣ እንደ ሰሎሞን ዓይነት ድንቅና ብልህ የሆኑ መፍትሔዎችን የሚያውቅ ጠቢብ ነው።

<u>ባህሪ 3፦ በየጊዜው ማደግ (የቀድሞ ማንነትን መብለጥ)</u>

ታላቁ ሰው ላይ የምናየው ሌላው ትልቅ ምልክት በየጊዜው ማደግ ነው። ይህ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ከፈላስፋው ፍሬድሪክ ኒቼ እሳቤ የተወሰደ ነው። ኒቼ ይህንን "ራስን ማሸነፍ/መሻገር" (Self-

Overcoming) ይለዋል። የታላቁ ሰው ሕይወት አንድ ቦታ ላይ ቆሞ “ደረስኩ፣ ጨረስኩ” የሚልበት መስመር የለውም፤ ይልቁንም በየቀኑ ካትናንት ማንነቱ የተሻለ ለመሆን የሚጋደልበት ቀጣይነት ያለው የዕድገት ጉዞ ነው።

ብዙ ሰዎች አንድ ደረጃ ላይ ሲደርሱ፣ ስኬት ሲያገኙ ወይም ማኅበረሰቡ “ጎበዝ ነህ” ብሎ ሲያጨበጭብላቸው በዚያው ይረካሉ፤ ማደጋቸውንም ያቆማሉ። ታላቁ ሰው ግን እንደነሱ አይደለም። እሱ ትልቁ ተፎካካሪውና ተቀናቃኙ የትናንትናው የራሱ ማንነት ነው።

ኒቼ እንዳለው፣ ሕይወት ማለት ራሷን በየጊዜው የምታሸንፍ፣ የምታድግና የምትቀያየር ኃይል ነች። ስለዚህ ታላቁ ሰው በየጊዜው ማደግን ባህሪው ያደረገ ሰው ነው፤ ልክ እንደ ንስር ወፍ በየጊዜው አሮጌ ላባውን እያረገፈ በአዲስ ጉልበት ወደ ሰማይ እንደሚበረው ። ቆሞ መቅረት መሞት መሆኑን ስለሚያውቅ፣ በየቀኑ አዲስ ማንነትን እየወለደ ወደ ፊት ይገሰግሳል።

ባህሪ 4፦ ጻድቅና ኃጢአተኛ

ወደ ታላቁ ሰው ስንመጣ የምናገኘው ሌላው አስገራሚ እውነት፣ እሱ ከሌሎቹ ደረጃዎች በተለየ መንገድ እሱ እውነተኛ ጻድቅና ኃጢአተኛ ነው።

ጉዳዩን በምሳሌ ግልጽ ላድርግላችሁ፦ በመጀመሪያው በእንስሳነት ደረጃ አንድ ሰው ክፉ ነገር ለማድረግ ቢነሳ መሰረቱ ደመ ነፍስ (Instinct) ነው። ለምሳሌ፣ አንበሳ አውሬ የሚያድነው ወይም አንዱ እንስሳ ሌላውን ጥሎ የሚሮጠው ስለጨከነ ሳይሆን በሕይወት ለመኖር ሲል ነው። በተመሳሳይ፣ በዚህ ደረጃ ያለ ሰው ሌላውን ገፍቶ ራሱን ሊያድን ቢሞክር የሚመራው በደመ ነፍስ ነው።

በሁለተኛው በሰውነት ደረጃ ያለ ሰው ደግሞ መልካም ነገር ቢሰራ መሰረቱ ሞራል(Moral) ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ለችግረኛ የሚመጸውተው ወይም ሕግ የሚያከብረው ማኅበረሰቡ “ይህ ጥሩ ነው” ስላለው፣ አሊያም “ካልሠራኸው ትቀጣለህ/ኃጢአተኛ ትሆናለህ” የሚል የሞራል ግዴታ ስላለበት ነው።

ታላቁ ሰው ግን የተለየ ነው! እሱ ለሚያደርገው ነገር የሚያስገድደው ደመ ነፍስም ሆነ ሞራል የለም። ለሚያደርገው ምርጫ ሁሉ ሙሉ ኃላፊነቱን የሚወስደው ራሱ ብቻ ነው።

እዚህ ላይ አንድ የታወቀ የፍልስፍና አመለካከት አለ፤ እርሱም የ“69” እሳቤ ነው። ይህ እሳቤ “እኔም ልክ ነኝ፣ አንተም ልክ ነህ” ይለናል። ቁጥሩን ከላይ ሆኖ የሚያየው “6” ሲለው፣ ከታች ሆኖ የሚያየው ደግሞ “9” ይለዋል። ሁለቱም ካሉበት ቦታ አንጻር እውነት አላቸው። ለምሳሌ፣ ሁለት አገራት ለሀገራቸው ሕልውና ሲሉ ጦርነት ውስጥ ቢገቡ፣ እያንዳንዱ ወታደር የሚዋጋው ለሀገሩ ሲል ስለሆነ በራሱ መንገድ “ትክክለኛ/ፃድቅ” ነው። በሌላው ወገን ያለውም እንዲሁ። ስለዚህ ሁለቱም ዋጋቸው እኩል ነው፤ ማንም ፍጹም ኃጢአተኛ ወይም ፍጹም ፃድቅ የለም። በኔ ቦታ ብትሆን እኔ ያደረግኩትን ታደርግ ነበር፣ እኔም ባንተ ቦታ ብሆን ያንተኑ ነበር የማደርገው።

ነገር ግን አንድ ምልከታ እንዲህ ይለናል “አንተ በዚያ ሁሉ መሃል የማድረግና ያለማድረግ ነፃ ፈቃድ (Free Will) አለህ”

ውጤቱ የሚሆነው ግን በእንስሳና በሰው ደረጃ ያሉ ሰዎች በተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ ነው የሚወድቁት። እንስሳዊው በደመ ነፍሱ ይገደዳል፣ ሰብአዊው ደግሞ በሞራል ይገደዳል። ሁለቱም በነፃ ፈቃዳቸውን አሳልው ሰጥተዋልና ።

ታላቁ ሰው ግን ምንም የሚያስገድደው ኃይል የለም። መኃል ላይ ቆሞ በነፃ ፈቃዱ ይወስናል። ስለዚህ እሱ በራሱ ምርጫና ኃላፊነት

ፃድቅም ኃጢአተኛም መሆን ይችላል። ድርጊቱን የሚወስነው ማኅበረሰቡ ሳይሆን የራሱ ሙሉ ነፃነት ነው።

ባህሪ 5፦ The Overman is a Bastard

ብዙ ሰዎች “ታላቁ ሰው” (Overman) ሲባል ፍጹም ሰላማዊ፣ ክንፍ የሌለው መልአክ አድርገው ያስቡታል። ነገር ግን እውነታው እንደዛ አይደለም ይልቁንም በተቃራኒው ከመደበኛው ሰው የተለጠ ከባድና የተለየ ግራ የሚያጋባ ችግር ያለበት ሰው ነው የሆነ ክትባት ያለፈው የሚመስል ልዩ ችግር።

ታላቁ ፈላስፋ ኒቻ እንኳ በሕይወቱ ዘመን ይህንን ታላቅ ሰው ለማግኘት ሲፈልገው እንደነበር፣ ነገር ግን ማግኘት እንዳልቻለና እንደናፈቀው በጽሑፎቹ ላይ በግልጽ ይታያል። እኔ እንደማስበው፣ ታላቁ ሰው በእርግጥም በምድር ላይ ነበረ፤ ነገር ግን ይህ ልዩ (Bastard) የመሆኑ ባህሪውና ያለበት በጣም የተለየ ከባድ ችግር፣ ኒቼ በትክክል እንዳያየው ዓይኑን ጋርዶት (ከልሎት) የነበረ ይመስለኛል።

ደረጃ 4፦ ከታላቁ ሰው በላይ (Beyond the Overman)

አሁን ደግሞ ወደ መጨረሻውና ወደ ላቀው አራተኛ ደረጃ ደርሰናል። ይህ ደረጃ “ከታላቁ ሰው በላይ” የምንለው ነው። እኔ እንደማስበው፣ ይህ ደረጃ ሊፈጠር የሚችልበት ሁለት መንገዶች አሉ።

የመጀመሪያው መንገድ፦ ይህንን ለመረዳት እኔ በግሌ ማንኛውንም ነገር ከ10ሩ ደረጃ ለመስጠት (Rate ለማድረግ) የምጠቀምበት ደረጃ አሰጣጥ አለኝ።

1-4ኛ ደረጃ ፦ እጅግ በጣም አስቀያሚ ነው። ቁጥሩ ወደ ታች በወረደ ቁጥር ነገሩ በጣም እየከፋ ይመጣል።

5ኛ ደረጃ፡ ጭራሽ ባይታሰብ ይሻላል ::

6ኛ ደረጃ፡ ቢቸግር ነው እንጂ ይሄም አይሆንም፤ ግን ከባዶ ይሻላል::

7ኛ ደረጃ፡ ግዴታውን የተወጣ፣ ማሟላት ያለበትን መሠረታዊ ነገር ያሟላ::

8ኛ ደረጃ፡ ከሚጠበቀው በላይ ያሟላ፣ ከግዴታው አልፎ አዲስ ነገር ያሳየ::

9ኛ ደረጃ፡ በጣም ድንቅ ነው፤ ነገር ግን የሆነች ትንሽ እንከን አለችበት:: እሷ ባትኖር ኖሮ ግን ፍጹም ነበር::

10ኛ ደረጃ፡ ምንም እንከን የሌለው ድንቅ የጥበብ ሥራ (Masterpiece) ነው:: እሱ አንተን ይመዝንሃል (Rate ያደርግሃል) እንጂ፣ አንተ እሱን ደረጃ ልትሰጠው አቅም የለህም::

ታዲያ “ከታላቁ ሰው በላይ” የሚባለው ሰው በዚህ መለኪያ እንዴት ይፈጠራል?

በማኅበረሰቡ ውስጥ ልክ የመፅሐፌ ርእስ መጠሪያ እንዳደረግሁት 7/10 የሆነውን (ግዴታውን የተወጣ) ሰው ስናገኝ፣ ወስደን 10 ላይ እንሰቅለዋለን:: ለምሳሌ አንድ ሰው ሰብአዊ ሥራ ቢሠራ፣ ቢመራመር፣ ቢጠይቅ ወዘተ... በጣም ተደንቀን በየሚዲያውና በየቦታው እንዘግባለን:: ሰብአዊነት ሊያሸልም የሚገባ ጉዳይ ሁኖ አይደለም ይህ ሁሉም ሰብአዊ ፍጡር ሊያደርገው የሚገባ ተራ ነገር ነበር፤ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆን አንድ የ you tube video አለ “how to drink water/ውሃ እንዴት ይጠጣል” ይላል በተንቀሳቃሽ ምስሉ ላይ አንድ ሰው ውሃ በብርጭቆ ቀድቶ ሲጠጣ ያሳያል/ያስተምራል፤ ከዚህ በፊት ሰው ውሃ እንዴት ነበር

የሚጥጣው? ልክ እንደዚህ ሁሉ ሰብአዊ ድርጊት ለወሬ የሚበቃ አልነበረም፤ ተራ ነገር ነው። ይህ የሚሆነው ግን አብዛኛው ሰው ከ 5 በታች ስለሆነ ነው ከዛ 7/10 የሆነ ስናገኝ ብርቅ ይሆንብን እና ወስደን 10/10 እንሰጠዋለን ።

በዚህ የተነሳ፣ የ 8 ወይም የ 9/10 የሆነ ሰው ስናገኝ፣ ከመጀመሪያው የ 7/10 ሰው እጅግ ስለሚበልጥብን፣ ከእኛ አቅም በላይ ይሆንና ከ10+ በላይ የሆነ ቁጥር እንሰጠዋለን። “ከታላቁ ሰው በላይ” የሆነው ሰው የሚፈጠረው የመጀመሪያው መንገድ እንዲህ ነው።

ሁለተኛው መንገድ፦ በርግጥም ይህ ከታላቁ ሰው በላይ የሆነው ሰው አለ ማለት ነው? ማን ይሆን?
ስለዚህ ሰው እኛ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ስለምን እያሰበ እንደሆነ፣ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ይህ ሰው እኛ የተጭበረበርንባትንና የተገዛንላትን ዓለም መልሶ ያጭበረበራት (የበለጣት) የላቀ ሰው ነው።

ሆኖም ግን አንዳንድ ምልክቶችን ማየት እንችላለን። ለምሳሌ፦ ከልጅነት፣ ከውልደት፣ አልፎም ገና ከፅንስ ጀምሮ ፍጹም ንቁ የሆኑ፣ ያንን እኛ ያሳለፍነውን እንስሳዊ ወይም ደመነፍሳዊ ደረጃን ፍጹም የማያውቁ ሰዎች አሉ።


በገድላቸው ላይ እንደተጻፈው እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት እና አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ያሉት ቅዱሳን በተወለዱበት ቀን ለሥላሴ ሰግደው ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል።

በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደተጻፈው መጥምቁ ዮሐንስ ገና በማኅፀን እያለ፣ ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ስትመጣ፣ የአምላክ እናት መሆኗንና አምላኩ ወደ እሱ መምጣቱን አውቆ በማኅፀን ውስጥ በደስታ ዘልሏል። እነዚህ ሰዎች ገና ሳይወለዱና ሳይደጉ እኛ የምንታገላቸውን ደረጃዎች በሙሉ አልፈው የተገኙ ናቸው።

ነገር ግን እውነቱን ለመናገር፣ በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በትክክል መረዳት በእኛ ደካማ አቅም ጨርሶ አንችልም!

የመኖር ፍላጎት (The Will to Live)

ግለ ታሪክ



የዚህ ሐሳብ መሥራች አርተር ሾፐንሃወር (Arthur Schopenhauer) የተባለ ጥልቅ አሳቢ የነበረ ጀርመናዊ ፈላስፋ ነው። ሾፐንሃወር ወደዚህ አስገራሚ የ“ፈቃድ” (Will) እሳቤ ሊደርስ የቻለው በዙሪያው ያለውን ዓለም፣ ተፈጥሮንና የሰዎችን የዕለት ተዕለት ሕይወት በትዝብት

በመመልከት ነው።

ሰዎች፣ እንስሳትና ዕፅዋት እንኳ ሳይቀሩ ያለምንም ማስተማርና ውጫዊ ግፊት በሕይወት ለመቆየት ቀንና ሌሊት የሚጋደሉትን ፍልሚያ ሲያጠና፣ ከሁሉ ነገር ጀርባ የሚገፋፋ አንድ ድብቅና እጅግ ግዙፍ የሆነ “ሁለንተናዊ ኃይል” እንዳለ ተገነዘበ። ያንን ኃይል ነው እንግዲህ “ፈቃድ/ፍላጎት” (Will) ብሎ የሰየመው።

እጅግ ከበለጸገ የሀብታም ነጋዴ ቤተሰብ የተወለደ በመሆኑ የገንዘብ ችግር ኖሮበት አያውቅም። ነገር ግን የውስጥ ሰላምና ደስታ ፍጹም የራቀው ሰው ነበር። ገና በወጣትነቱ የአባቱን አሳዛኝ የሞት ዜና ሰማ አባቱ ራሱን በገዛ ፈቃዱ አጥፍቶ ነበር። ይህ አስደንጋጭ ክስተት በሾፐንሃወር አእምሮ ውስጥ “ሕይወት ምንድነች? ለምንድስ እንኖራለን?” የሚል ትልቅ ጥያቄ እና የጭንቀት ጠባሳ ጥሎበታል። ከአባቱ ሞት በኋላ ደግሞ ከእናቱ ከዮሐና ሾፐንሃወር (Johanna Schopenhauer) ጋር ያለው ግንኙነት ፍጹም የሻከረና በንቀት የተሞላ ሆነ።

በወቅቱ እናቱ ዮሐና ሾፐንሃወር ከእሱ እጅግ በጣም የምትበልጥ፣ በጀርመን አገር ስሟ ናኝቶ የነበረ እጅግ ዝነኛ ሴት ነበረች! እንዲያውም በጀርመን የስነ-ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ በድርሰት ሥራዋ የመጀመሪያዋን ትልቅ የገንዘብ ገቢ ማግኘት የቻለችና በሙያዋ “ፕሮፌሽናል ደራሲ” መሆን የቻለች ስኬታማ ሴት ነች።

አባቱ ከሞተ በኋላ እናቱ የጀርመን የጥበብና የባህል ማዕከል ወደነበረችው ዌይማር (Weimar) ወደምትባል ከተማ ተዛወረች። እዚያም በቤቷ ውስጥ የኪነ-ጥበብና የባህል ስብሰባዎችን (Salons) ማዘጋጀት ጀመረች። በዚያ ስብሰባ ላይ በወቅቱ የነበሩ የዓለም ታላላቅ ጸሐፍት፣ ፈላስፎችና ገጣሚያን እንደ ታላቁ ገጣሚ ጎተ (Goethe) ሳይቀሩ በቤቷ ያመሹ ነበር። እሷ የዚህ ሁሉ ታላቅ ስብስብ መሪና ንግሥት ነበረች።

አርተር ሾፐንሃወር የመጀመሪያውንና ዋናውን መጽሐፉን “The World as Will and Representation” (ዓለም እንደ ፈቃድና ምስል) አሳትሞ ሲያበቃ፣ በወቅቱ አንድም ሰው ሊገዛውና ሊያነበው አልፈለገም። እንዲያውም መጻሕፍቱ ሙሉ በሙሉ ተረስተው መጋዘን ውስጥ ተከማችተው በስብሰው ነበር። በአንጻሩ ግን እናቱ አዲስ መጽሐፍ ባወጣች ቁጥር አድናቂዎቿ በከፍተኛ ጉጉት ይሸመት ነበር።

ለዚህ ነው በመካከላቸው የነበረው ፉክክር፣ ኩራትና ንቀት በጣም የከረረው። እናቱ የእሱን ፍልስፍና ሁልጊዜ ታጣጥልበት ነበር። በአንድ ወቅት “ያንተ መጽሐፍ ጨለምተኛና ለማንም የማይገባ ቆሻሻ ነው፤ ማንም አያነበውም!” ስትል አፌዘችበት። ይሁንና ሾፐንሃወር በራሱ ላይ ያለው መተማመን የሚናቅ አልነበረምና በምላሹ “ዓለም አንቺን ወደፊት የሚያስታውስሽ የሾፐንሃወር እናት ተብለሽ እንጂ በድርሰትሽ አይደለም! እኔን የሚረዳኝ ትውልድ ገና ወደፊት ይመጣል” ብሏታል።

በወቅቱ የእናቱ ዝና ሰማይ የነካ ቢሆንም፣ ዛሬ በታሪክ መለስ ብሎ ሲታይ ግን ልክ እሱ እንዳለው እናቱን ዓለም የሚያውቃትና የሚያስታውሳት “የታላቁ ፈላስፋ የሾፐንሃወር እናት” በሚለው ስሟ ብቻ ሆኗል።

የሚያሳዝነው ግን፣ በዘመኑ የነበረውና በዓለም ላይ እጅግ ዝነኛ የነበረው ሙዚቀኛ ሪቻርድ ዋግነር (Richard Wagner) የእሱን ፍልስፍና በጥልቀት አንብቦ፣ በሐሳቡ በመመሰጥ የሾፐንሃወርን “የመኖር ፈቃድ” እሳቤ መሠረት አድርጎ ድንቅ የሙዚቃ ሥራዎቹን በመሥራት ሾፐንሃወርን ታዋቂ ቢያደርገውም፣ የሾፐንሃወር እውነተኛ ዝና የገነነውና ዓለም ለእውቀቱ ትክክለኛ እውቅና የሰጠችው እሱ በሕይወት እያለ ሳይሆን፣ ከሞተ በኋላ ነው። እሱ ግን ይህ እንደሚሆን ገና ቀድሞ ያውቅ የነበረ ይመስላል ።

የመኖር ፍላጎት (The Will to Live) ማብራሪያ

እስኪ አሁን ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ፤ ለመሆኑ “የመኖር ፍላጎት” (Will to live) ምንድነው?

ቀደም ሲል በነበረው ርዕስ ላይ እንዳስነበብኳችሁ፣ “Will” ማለት በሁሉም ሕይወት ባላቸው ፍጡራን ላይ የተጫነ የሶፍትዌር አፕሊኬሽን (Software Application) እንደሆነ እና ይህ የ“Will” ሶፍትዌር እኛ በተፈጥሮ ውስጥ የጎደለንን ነገር በውስጣችን ሆኖ የሚሞላና ሥርዓት ነው ብዬአችሁ ነበር።

ይህኛው “የመኖር ፍላጎት” (Will to live) የተባለው ሶፍትዌር በውስጣችን የሚሞላልን ጎደሎ ነገር ሕይወትን ነው፤ ሕይወትን እየሞላ እኛን በ ሕይወት እንድንቆይ ያደርገናል ።

እዚህ ጋር “ቆይ! የጎደለንን ነገር የሚሞላ ከሆነ፣ ታዲያ እኛ አሁን ሕይወት የለንም እንዴ? ምኑን ነው የሚሞላልን?” የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ነገሩ መጀመሪያ ላይ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ቢመስልም፣ ቀስ ብዬ በምሳሌዎች ሳስረዳችሁ ግን በጣም ቀላል ነው የሚሆነው። ነገር ግን ይህንን ክፍል በጥልቀትና በደንብ ለመረዳት ሞክሩ እኔም ከልሎቹ አንፃር ሰፋ አድርጌ አብራራለሁ፤ ምክንያቱም ወደፊት የምናያቸው ቀሪዎቹ ሦስቱ የፍላጎት (Will) ዓይነቶች በሙሉ ልክ እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆነ የሶፍትዌር እና ጎደሎን የመሙላት ባህሪ ነው ያላቸው።

ይህ ሶፍትዌር እኛ ሳናውቀው በሕይወታችን ውስጥ እንዴት ማስተርማይንድ (Mastermind) ሆኖ እንደሚጫወትብን ለማየት፣ እስኪ ጥቂት የዕለት ተዕለት እውነታዎችን በምሳሌ እንመልከት፦

አንድ ወጣትን እንደ ምሳሌ እንውሰድ፤ አንዲትን ቆንጆዬ ልጅ ይመለከታል፣ በፍቅሯም ጭንቅላቱ ይዞራል (ጠብ ይላል)። ሁሉ ነገሩ፣ ዓለሙ እሷ ትሆናለች። ይጠይቃትና እድለኛ ሆኖ እሺ ትለዋለች (በርግጥ እዚህ ጋ በእድል ጉዳይ ሆኖ አይደለም፣ ለምን እንደሆነ ኋላ ላይ አስረዳችኋለሁ)። ከዛማ የሚያስቀና ፍቅር ውስጥ ይገባሉ፤ በመጨረሻም ተጋብተው ትዳር ይመሰርታሉ። ታዲያ የዚህ ሁሉ መሯሯጥ መጨረሻው ምንድነው? ልጆች መውለድ አይደል? በፊት ልጅ እያለን ከሴቶች መሀል መቀመጥ እንደ እፍረት ወይም እንደ ቅጣት ይቆጠር እንዳልነበር፣ አሁን በድንገት ውሎህ፣ አዳርህና ሐሳብህ ሁሉ ስለ ሴት ይሆናል፤ ፍቅር ፍቅር ትላለህ፣ ጥቅስ ትጠቅሳለህ፣ ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን አንተ ያፈቀርክ ይመስልሃል፤ ነገር ግን እውነታው ባንተ ውስጥ ያለው “የመኖር ፍላጎት” (Will to Live) ባንተ ውስጥ ሁኖ እንድታፈቅር የሚያደርገው ። ለዚህም ዝሙትን እንደ ልዩ ስሜት ይጠቀማል አስቡት ዝሙት ተራ ስሜት ቢሆን ኖሮ ማንም ልጅ ይወልድም ነበር ።

የጉዳዩ ምጸት ያለው እዚህ ጋር ነው፤ በልጅነታችን የምናደርገው ማንኛውም ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ መኖር ደስ ይል ነበር ጣፋጭ ስንቀምስ ሳይክል ስንነዳ ስንጫወት ወዘተ... ሁሉንም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ምናረገው ስናድግ ግን ይህ አይሆንም ፈረንጆቹ “Rut” ብለው የሚጠሩት፣ ምንም አዲስ ነገር የሌለው አሰልቺ ኑሮ የሚባል ነገር አለ ስያሜውን ያገኘው በክብ የብረት ሽቦ መሰል እሽክርክሪት ከምትሮጠው እንደ ቤት እንስሳ ለሆነችው የአይጥ ዝርያ (hamster) ነው ።

አግብተህ ልጆች በምትወልድበት እድሜ ላይ፣ በተለይ በ 30ዎቹ የዕድሜ ክልል አካባቢ ይህ ስሜት በብዛት ይከሰታል። “የምለፋለት ነገር በሙሉ ከንቱ ይሆናል፤ ለምን ብዬ ነው የምለፋው?” ማለት ትጀምራለህ። ነገር ግን ልጆች ሲኖሩህ፣ እነሱን ማፍቀር ትጀምራለህ፤ በጣም ትወዳቸዋለህ። ቀድሞ ዓለምህ ሁሉ ሴቶች እንዳልነበሩ፣ አሁን ግን ልጆችህ ይሆናሉ። ከዚህ ቀደም ተሰምቶህ

የማያውቅ አዲስ የልጅ ፍቅር የሚባል ስሜት ይሰማሃል፤ ዓለምህ ሁሉ እነሱ ይሆናሉ። ለነሱ ስትል **መኖር ትጀምራለህ፤ "እኔ የምኖረው ለልጆቼ ነው"** ትላለህ። አሁን የምትኖርበት ትልቅ ምክንያት አገኘህ! በዚህ መሃል ግን ይህንን ሁሉ ነገር ስታደርግ አንተ ራስህ በፈቃድህ ያደረግከው ይመስልሃል፤ ነገር ግን እውነታው ባንተ ውስጥ ያለው የመኖር ፍላጎት (Will to live) ጊዜውን እየጠበቀ፣ የጎደለህን ሕይወት ሞልቶ፣ ዘር እንድትተካ እና አንተም በልጆችህ አማካኝነት እስከመጨረሻው በሕይወት እንድትኖር አደረገ ።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ እንመልከት፤ ወንዶች ወይም ሴቶች ለምን የሚማግጡ ይመስላችኋል? እዚህ ጋር የ Will እጅ ይኖርበት ይሆን? መልሱ አዎ ነው! ነገሩ እንዲህ ነው፤ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ጋር ብቻ ቢወሰን፣ ዘር ማስቀጠል የሚችለው በጣት በሚቆጠር ልጅ ብቻ ነው። ነገር ግን የእሱ (Possibility) የመውለድ አቅሙ በመቶዎች እና በሺዎች የሚቆጠር ነው። በውስጡ ያለው Will ደግሞ የሚፈልገው እነዛን ሺዎች ነው፤ ስለዚህ ከአንድ ሴት ጋር ከሚወሰን ይልቅ፣ በርካታ ሴቶች ጋር ሆኖ ብዙ ዘር እንዲተካ ስለሚፈልግ በደመነፍስ ለመማገጥ ይጋብዘዋል።

ሴቷም ጋር በተመሳሳይ፤ እሷ በሕይወቷ መውለድ የምትችለው ጥቂት ልጆችን ብቻ ስለሆነ፣ በውስጧ ያለው Will "ምርጥ ዘር" (Best Genes) ነው የሚፈልገው። ስለዚህ ከተለያዩ ጂኖች (Genes) ጠንካራ፣ ቀይ፣ ጠይም፣ ቆንጆ፣ ብልህ፣ ረጅም ወዘተ የሆኑ ልጆችን ይፈልጋል። ከአንድ ሰው ብቻ ከሆነ ተመሳሳይ ጂን ስለሚሆን ሊደርሳት የሚችለው፣ ምርጥ ምርጡን ከተለያዩ ወንዶች ጋር እንድትፈልግ ይጋብዛታል።

ነገር ግን እኛ የሰው ልጆች ይህ ስርአት ሙሉ በሙሉ እንዳይቆጣጠረን በ ሞራል ገድበን ይዘነዋል የዚህንም ሞራል ስም ትዳር ብለን ጠርተን ሰው መሆናችንን እና ከልሎች እንስሳት እንደምንለይ አስመስክረናል ።

“እኛ ሰዎች 95% የአእምሯችንን ክፍል አንጠቀመውም” ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል። ይህንን 95% ክፍል ሰርቫይቫልን (Survival) ጨምሮ የተለያዩ የደመነፍስ (Instinct) ሥርዓቶች ስለሚቆጣጠሩት ነው እኛ ቀጥታ የማናዘዘው። ብዙ ጊዜ ይህንን የ 95% ምስጢር ተጠቅመው የአነቃቂ ተናጋሪዎች (Motivational Speakers)፦ “አእምሮህ ትልቅ ድብቅ ኃይል አለው፣ ተጠቀመው!” እያሉ እንደ super power አድርገው ይስሉታል። እኛ የሰው ልጆች ደግሞ የማናውቀው ወይም ምስጢራዊ ነገር ስናገኝ ምንግዜም በጣም ተአምራዊ ነገር እንጠብቃለን። ለምሳሌ፦ “የግብፅ ፒራሚድ ተሠራ” ሲባል “እንዴት በሰው ኃይል ይሆናል? ኤልየኖች (Aliens) ናቸው የሠሩት!” ወዘተ እንላለን ግን አይደለም ራሳችን ነው የሰራነው፤ እውነት ምንግዜም ቀላሉ መልስ ነው! በተመሳሳይ ያ 95% የአእምሯችን ክፍል ደመነፍስ ነው። እስኪ አስቡት፤ ሙሉ ሰውነታችን ላይ ሥልጣን ቢኖረንና 100% አእምሯችንን ብንጠቀም የልብ ትርታችንን፣ ኩላሊታችንን፣ ሳንባችንን እኛው ራሳችን 24 ሰዓት ሙሉ አስልተን ማስተካከል ቢኖርብን ኖሮ ምን እንሆን ነበር? አንድ ቀን “አቦ እኔ ዛሬ ደብሮኛል!” ብለን የልብ ትርታችንን ስንተወው! ስለዚህ ይህ የማይሰለች፣ የማይደክም ደመነፍሳዊ Will የቀረውን ፐርሰንት ወስዶ ትልቁን የሕይወት ሥራ ይሠራል።

ሌላው መላው ዓለም የሚስማማበትን የ“እንጆራ እናቶች ክፉ ናቸው” የሚለውን እውነታ እንይ (በርግጥ ሁሉም ማለት አይደለም፣ ግን ክፉዎቹን እንመልከት)። ለመሆኑ ምን አስጨከናቸው? እናት አይደሉም እንዴ? ካልን ያው የፈረደበት Will ነው! አንዲት ሴት አንዴ እናት ከሆነች ጀምሮ በውስጧ ያለው የ Will ሥርዓት አዲስ ደመነፍስ Unlock ያደርግላታል እሱም የእናትነት ደመነፍስ ነው። እሱ ልጇን ብቻ እንድትወድና እንድትጠብቅ ያደርጋታል። በዚህ ጊዜ ያ ሌላው (የእንጆራ ልጇ) እንደ ምን ይታያታል መሰላችሁ? እንደ “አረም” ነው የሚታያት! የእሷ ደመነፍስ ለገዛ ልጇ የምታደርገውን እንክብካቤና ሀብት እየተሻማ፣ ልጇን የሚያቀረጭጭ አረም አድርጎ ስለሚያየው Will ያንን ልጅ

እንድታስወግደው ወይም እንድታገለው ይገፋፋታል። ስለዚህ የእንጀራ እናቶች ጭካኝ ይሆናሉ ማለት ነው ።

ነገር ግን በዚህ መሃል ልክ እንደ እውነተኛ እናት የሆኑ ድንቅ እንጀራ እናቶችም አሉ። እነሱ ማን ናቸው ካልን ያንን የ Will ዕውር ደመነፍሳቸውን በሞራል የገዙትና ያሸነፉት ናቸው! “አይ! እኔ አንተንም እንደ ገዛ ልጄ ነው የማየው” ትላለች፤ ለልጇ የምታደርገውን እንክብካቤ ሁሉ ለእሱም እኩል ትሰጣለች። ይህ እንግዲህ እውነተኛው የሰውነትና የሞራል ከፍታ ምልክት ነው። እኛ ሰዎች ይህ የ Will ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ እንዳይቆጣጠረን በሞራል እናስረዋለን ማለት ነው።

Will እና ዝግመተ ለውጥ (The Will and Evolution)

እዚህ ላይ “ሰው ከዝንጀሮ መጣ” ልላችሁ አይደለም ይልቁንም በዚህ በምናወራለት የ Will ሥርዓት እና በዝግመተ ለውጥ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማስረዳት ነው።

ቀደም ሲል እንዳየነው የ Will To Live ሥርዓት በዋናነት የሚጠቀመው በውስጣችን ያሉትን ደመነፍሶች (Instincts) ነው። ደመነፍስ ደግሞ በባህርዩ በጂናችን (Genes) ውስጥ የሚዘዋወርና በትውልድ የሚተላለፍ የሕይወት ኮድ ነው። እነዚህ ጂኖች ደግሞ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር እየተላመዱ ራሳቸውን የሚያድሱትና የሚቀያይሩት በዝግመተ ለውጥ ሂደት ውስጥ ነው።

ለምሳሌ ያህል፣ አፍሪካውያን ለምን ጥቁር ቆዳ እንዳላቸውና አፍንጫቸው አጠር ብሎ ደፍጠጥ እንዳለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አውሮፓውያን ነጭ ሆነው አፍንጫቸው ለምን እንደረዘመ ብናይ ምስጢሩ የ Will እና የተፈጥሮ መላመድ ነው።

በአፍሪካ ከፍተኛ ሙቀትና ኃይለኛ የፀሐይ ብርሃን ስላለ፣ የ Will ሥርዓት ቆዳን ከካንሰር ለመጠበቅ ሜላኒን የተባለውን ንጥረ ነገር በማብዛት ጥቁር ቆዳ እንዲኖረን አድርጓል። አፍንጫችን አጠርና ሰፋ ማለቱ ደግሞ ያንን ሞቃት አየር በቀላሉ ወደ ውስጥ ለማስገባትና ሰውነታችንን ለማቀዝቀዝ ነው። በአንጻሩ አውሮፓውያን ያሉበት አካባቢ ብርድና ደመናማ በመሆኑ፣ ቆዳቸው የፀሐይን ብርሃን በቀላሉ ስቦ ቫይታሚን ዲ (Vitamin D) እንዲሠራ ነጭ ሆነ፤ አፍንጫቸው መርዘሙ ደግሞ ያንን የቀዘቀዘ አየር ወደ ሳንባ ከመግባቱ በፊት በትቦው ውስጥ አሙቆ ለማሳለፍ ነው። ይህ እንግዲህ Will በጂን አማካኝነት ሕይወትን ለማስቀጠል ያደረገው የረዥም ዘመን ዝግመተ ለውጥ ነው።

ነገር ግን ማስተዋል ያለብን ነገር፣ ሁሉም ነገር በዘር አይተላለፍም። ለምሳሌ አገስት ዌይስማን (August Weismann) የተባለ ሳይንቲስት የአይጦችን ጅራት እስከ 20 ትውልድ ድረስ በየተራ እየቆረጠ ምርምር አድርጎ ነበር። “የተቆረጠ ጅራት ያላቸው አይጦች ይወለዱ ይሆን?” ብሎ ቢጠብቅም፣ የተወለዱት አይጦች በሙሉ ግን ረዥም ጅራት ይዘው ነበር የተወለዱት። በወቅቱ የነበሩ ሊቃውንት “ወንዶች ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ለሺዎች ዓመታት ሲገረዙ ቢመጡም፣ አሁንም ድረስ ግን ወንድ ሕፃናት ሲወለዱ ከነወሸላቸው (ሳይገረዙ) እንደሚወለዱ ማስተዋል በቂ አልነበር እንዴ” ብለው በሳይንቲስቱ ሞኝነትና ጅልነት ክፉኛ ስቀውበታል። ይህም የሚያሳየው Will በደመነፍስ ውስጥ የሚቀርጸው ነገር በአካል ላይ የሚደርስን ለውጥ ሳይሆን፣ በውስጣዊው የጂን ኮድ ውስጥ የታተመውን የህልውና ሥርዓት ብቻ መሆኑን ነው።

ይህ የ Will እና የዝግመተ ለውጥ ሥርዓት አጋርን (የሕይወት ጓደኛን) በመምረጥ ረገድም የሚገርም ሚና አለው። ወንዶች አጋር ሲመርጡ በብዛት ውበትና ጥቃቅን ነገሮች ላይ ሲያተኩሩ፣ ሴቶች ደግሞ በተቃራኒው ጥንካሬ፣ ገንዘብ፣ ሥልጣንና ሌሎች ጠንከር ያሉ ነገሮችን ያስቀድማሉ።

ይህም የሚሆነው በጥንት ዘመን ዝግመተ ለውጥ ውስጥ ሴቶች በሚያረግዙበትና ልጅ በሚያሳድጉበት ጊዜ በጣም ይዳከሙ ስለነበር ነው። በነዚያ በድካም ጊዜያቶቿ አድኖ የሚያበላት፣ ከአራዊትና ከሌሎች ጎሳዎች ጥቃት የሚጠብቃት ጠንካራ ወንድ ትፈልጋለች። ሴቷ በወቅቱ "ውበትን" ብቻ ቅድሚያ መስፈርት አድርጋ ብትመርጥ ኖሮ፣ እሷም ልጇም የተዋቡ የአውሬ እራቶች (ምግቦች) መሆናቸው አይቀሬ ነበር። ስለዚህ የእሷ Will ጥንካሬንና ሀብትን (የመጠበቅ አቅምን) እንድትመርጥ ቀረጸት።

ይህንን ምርጫ ለማካሄድ ደግሞ በሰውነታችን ውስጥ ልክ እንደ ብሉቱዝ (Bluetooth) አይነት ሥርዓት አለ። በወንድም ሆነ በሴት ውስጥ ያለው ይህ ሥርዓት አጋርን ሰርች (Search) ሲያደርግ ነው የሚውለው። ያገኘውንና ያየውን ሰው ሁሉ በደመ ነፍስ ይመረምራል፤ የጂን ጥንካሬውን፣ ውበቱን፣ አቅሙን ያጠናና በውስጣዊ ዝርዝር (List) ውስጥ ያስገባዋል። ከዛም ዝርዝሩ ውስጥ የተሻለ የነጥብ አብላጫ ያገኘው ሰው አሸናፊ ሆኖ የሕይወት አጋርህ ይሆናል ማለት ነው።

ነገር ግን ትልቁ አደጋ ያለው እዚህ ጋር ነው። ባለፉት 500 ዓመታት ውስጥ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮና ቴክኖሎጂ እጅግ በጣም በፈጣን ሁኔታ ተለወጠ። ይህ ፍጥነት ደግሞ በውስጣችን ያሉትን የቆዩ ደመነፍሶች ሙሉ በሙሉ ግራ እያጋባቸው መጥቷል።

ለምሳሌ፣ የእኛ ደመነፍስ ከጥንት ጀምሮ የለመደው ሥርዓት አለ፤ ወንድ ለአቅመ አዳም፣ ሴትም ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ (ገና በወጣትነት ዕድሜ) ወዲያውኑ ወደ ትዳር መግባት አለባቸው በሚለው ነው። በውስጣችን ያለው የ Will ሶፍትዌር ዕውር ስለሆነ የውጩ ዓለም ላይ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ማየት አይችልም። እሱ የሚያውቀው "ዕድሜው ደርሷል፣ ዘር መተካት አለበት" የሚለውን ብቻ ነው። ስለዚህ ለአቅመ አዳም/ሔዋን ስትደርስ ከፍተኛ የሆነ የዝሙት (የወሲብ) ፍላጎት በውስጥህ

ይለቅብሃል። በሱ ቤት አንተ አግብተሀልና ልጅ እንድትወልድ ማድረጉ ነው።


አሁን ግን ዓለም ፈጽሞ ተቀይራለች! ትምህርት፣ ሥራ፣ ዶክትሬት፣ ማስተርስ ስንል በፊት ከነበረው የትዳር መያዣ ዕድሜ በእጅጉ አልፈን ሄደናል። ታዲያ ምን ይሆናል? ይህንን በ Will የተለቀቀብንን ከፍተኛ የዝሙት ፍላጎት ማቆም ስለማንችል፣ ወደ ግለ-ወሲብ (Masterbation) እንቀይረዋለን። በዚህም ምክንያት ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ በሆኑ ተጓዳኝ ከባድ ስነ-ልቦናዊ ቀውሶችና የጥፋተኝነት ስሜቶች ውስጥ እንገባለን። ደመነፍሱና የዘመኑ ዓለም መጋጨት ካመጡት ቀላል ከማይባሉ ችግሮች አንዱ ይህ ነው።

ሌላኛው አስከፊ ነገር ደግሞ የዘመኑ ወጣቶች ለሕይወት ወዲያው እጅ እንዲሰጡ (ራስን ለማጥፋት እንዲጋለጡ) ማድረጉ ነው። ቆም ብላችሁ ስታስቡት፣ እኛ ካለብን የሕይወት ውጥረትና ችግር በላይ የወላጆቻችን ችግርና መከራ እኛ አለብን ከምንለው ጋር ፊፅሞ አይገናኝም፤ ነገር ግን እኛ ራስን ለማጥፋት በጣም ቅርብ ስንሆን፣ እነሱ ግን ስለሱ ጭራሽ አያስቡም። ለምን? ምክንያቱም እነሱ የሚኖሩት ለኛ ነው! የ Willን ሥርዓት ተከትለው ወልደውናል፣ ስለዚህ Will በውስጣቸው የእናትነትና የአባትነትን ኃይለኛ ደመነፍስ Unlock ስላደረገላቸው ለልጆቻቸው ሲሉ መከራን የመቋቋም አቅማቸው የላቀ ሆነ። እኛ ግን በትምህርትና በሥራ ምክንያት ያንን የ Will ሥርዓት (ማግባትና መውለድን) ስለዘለልነው፣ ልጆች ስለማይኖሩን የሕይወት ድግግሞሽና ባዶነት በቀላሉ ያሸንፈናል፤ ይህም ለድባቴና ለተለያዩ ተጓዳኝ የአእምሮ ችግሮች አሳልፎ ይሰጠናል።

እንግዲህ የመኖር ፈቃድ (Will to Live) የምንለው ኃይል በእንደዚህ ዓይነት እጅግ በተወሳሰበ፣ ረቂቅና በረጅም ዘመን የዝግመተ ለውጥ ሥርዓቶች በተለያዩ ደመነፍሶች የተሞላ ድንቅ የሕይወት ሥርአት ነው።

እንግዲህ እንዲህ ነው፤ “የመኖር ፍላጎት” (Will to live) የምንለው ሥርዓት ዘር እንድንተካ እያደረገ፣ እኛንም እስከመጨረሻው ድረስ በሕይወት እንድንቆይ የሚያደርገን ኃይል ነው። ለዚህም ደመነፍሶችን በየጊዜያቸው Unlock እያደረገ፣ እኛ ባላወቅነው ወይም ባልነቃንበት መልኩ እየኖርን ቢመስለንም፣ እሱ ግን በውስጣችን ሆኖ በራሱ መንገድ እንድንኖር ያደርገናል።

የኃይል ፍላጎት The Will to Power



የመኖር ፈቃድን ካየን ዘንድ፣ አሁን ደግሞ ፍጹም ወደተለየና የሰው ልጅን ንቃተ-ህሊና ወደሚቀሰቅስ ሁለተኛ የፈቃድ ፍልስፍና እንገባለን፤ እሱም “ የኃይል ፍላጎት” (The Will to Power) ይባላል። የዚህ ኃይለኛ ፍልስፍና ባለቤት፣ በዓለም ታሪክ ውስጥ እጅግ የሚፈራው፣ የሚወደደውና በተሳሳተ መንገድ የሚተረጎመው እብሪተኛው ጀርመናዊ ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቻ (Friedrich Nietzsche) ነው።

ኒቼ የተወለደው በሃይማኖተኛ የቄስ (ፓስተር) ቤተሰብ ውስጥ ነበር። ነገር ግን ገና የ5 ዓመት ልጅ እያለ፣ አባቱ በአእምሮ ሕመም ምክንያት በከፍተኛ ስቃይ ሞተ፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ ብቸኛ ወንድሙ ሕይወቱ አለፈች። ይህ በሕፃንነቱ ያየው የሞትና የድክመት ስቃይ፣ በውስጡ ትልቅ የስነ-ልቦና ቀውስ ጥሎበታል።

የሚገርመው ነገር፣ ኒቼ በወጣትነቱ እጅግ ምጡቅና ሊቅ ስለነበር፣ ገና በ24 ዓመቱ በባዝል ዩኒቨርሲቲ የፊሎሎጂ (የቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ጥናት) ፕሮፌሰር መሆን የቻለ ድንቅ ወጣት ነበር።

ይሁንና አካላዊ ጤንነቱ ፍጹም የተረገመ ነበር፤ በከባድ ራስ ምታት፣ በአይን ሕመም እና በጨጓራ ስቃይ በየቀኑ ይማቅቅ ነበር። እንዲያውም ሕመሙ ስለበረታበት ገና በ34 ዓመቱ ከዩኒቨርሲቲ ሥራው ለመልቀቅ ተገደደ። በዚህ የተነሳ ኒቻ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ፣ በብቸኝነትና በስቃይ እየናወዘ ነው ዘመኑን ያሳለፈው። ታዲያ ይህ አካሉ የደከመውና በበሽታ የተደበደደው ሰው ነው እንግዲህ “ዓለምን የሚመራት ትልቁ ኃይል የመኖር ፍላጎት ሳይሆን፣ የኃይልና የሥልጣን ፍላጎት ነው” የሚለውን ፍልስፍና የፈጠረው።

ኒቻ ወደዚህ ፍልስፍና የደረሰበት ቀደም ሲል ያየነውን የአርተር ሾፐንሃወርን መጽሐፍ በወጣትነቱ በድንገት ማግኘቱ ነው። ነገሩ የሆነው እንዲህ ነው፤ ኒቻ በአንድ ወቅት በከባድ የሕይወት ውጥረትና ጭንቀት ውስጥ ሆኖ መንገድ ላይ ሲንገዘገዝ፣ አንድ ያገለገሉ አሮጌ መጻሕፍት የሚሸጡበት ሱቅ (Second-hand bookstore) ያያል። ዝም ብሎ ገብቶ ሲበረብር፣ የሾፐንሃወርን “The World as Will and Representation” የተሰኘውን መጽሐፍ በአጋጣሚ አገኘው። መጽሐፉን ገዝቶ ወደ ቤቱ እንደወሰደው፣ ለአሥራ አራት ቀናት ያህል እንቅልፍ አጥቶ በተከታታይ አነበበው። መጀመሪያ ላይ በሾፐንሃወር “የመኖር ፈቃድ” ተማርኮና ተመስጦ የነበረ ቢሆንም፣ ቆይቶ ግን ማጎበረሰቡንና የራሱን ሕይወት ሲመረምር በሾፐንሃወር ሃሳብ ላይ ትልቅ ስህተት አገኘ። ኒቼ ምን አለ? **“የሰው ልጅ ትልቁ ግብ ዝም ብሎ በሕይወት መኖር (Survival) ብቻ አይደለም፤**

ምክንያቱም በሕይወት ለመቆየት መጀመሪያ መኖር እኮ አለብህ። ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ሁሉ የሚፈልጉት ዝም ብሎ መኖርን ሳይሆን፣ በሕይወታቸው ላይ የበላይ መሆንን፣ ማደግን፣ መግዛትንና ኃይላቸውን መግለጥን ነው" አለ።

ኒቼ በጀርመንና በፈረንሳይ ጦርነት ወቅት የወታደር የሕክምና ረዳት ሆኖ በሠራበት ጊዜ፣ የቆሰሉና ሊሞቱ የተቃረቡ ወታደሮች በዚያ በስቃይ ሰዓት እንኳን የሚፈልጉት ዝም ብሎ በሕይወት መትረፍን ሳይሆን፣ ማሸነፍንና የጀግንነት ኃይልን ማሳየት እንደሆነ በአይኑ ተመለከተ። ከዚህ ትዝብቱ ተነስቶ ነው እንግዲህ፣ ከሁሉም የሕይወት ትግል ጀርባ ያለው እውነተኛው ሞተር "The Will to Power" (የኃይል ፍላጎት) መሆኑን ያወጀው። በዚህ እሳቤውም እንደ "Thus Spoke Zarathustra"(እነሆ ዛራዬሽት ተናገረ) እና "Beyond Good and Evil"(ከ መልካም እና ክፉ ባሻገር) ያሉ በዓለም ላይ እጅግ ዝነኛ የሆኑ መጻሕፍቶቹን ለመጻፍ በቃ። ይሁንና ኒቼ በዘመኑ እጅግ የተጠላና የተገለለ ሰው ነበር። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ምክንያት በወቅቱ ማኅበረሰብ ዘንድ ከባድና አስደንጋጭ የነበረውን "እግዚአብሔር ሞተ" (God is dead) የሚለውን ንግግሩን በመናገሩ ነው። ሰዎች እሱ ሃይማኖትን ለመሳደብ ብቻ የተናገረው መስሏቸው ክፉኛ ጠሉት፤ ነገር ግን እሱ ማለቱ የነበረው ማኅበረሰቡ ከሳይንስና ከኢንዱስትሪ ዕድገት ጋር ተያይዞ እውነተኛውን የሞራልና የእምነት መሠረት ማጣቱን፣ ዓለምም ወደ ከንቱነትና ወደ ባዶነት (Nihilism) እያመራች መሆኑን ለማስጠንቀቅ ነበር።

የኒቻ ትልቁ አሳዛኝ ታሪክ ግን ከሞተ በኋላ የደረሰበት ክህደት ነው። ኒቻ ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ለአሥር ዓመታት ያህል ሙሉ በሙሉ አእምሮውን ስቶ (ፓራላይዝድ ሆኖ) በአልጋ ላይ ነበር። በዚህ ሰዓት መጻሕፍቶቹንና ያልታተሙ ማስታወሻዎቹን የምትጠብቀው እህቱ ኤልሳቤጥ (Elisabeth Förster Nietzsche) ነበረች። እህቱ ግን ፍጹም ዘረኛና የናዚ አመለካከት የነበራት ሴት ስለነበረች፣ ዓለም የኒቻን ፍልስፍና እንዳይረዳው አድርጋ የኒቻን ጽሑፎች በራሷ

ፍላጎት እየቆረጠችና እየቀያየረች አሳተመቻቸው። ይህንን ያደረገችው በወቅቱ በጀርመን ይነሳ ለነበረው የፋሺስቱ ናዚ እና የዶልፍ ሂትለርን ቀልብ ለመሳብ ስትል ነበር። በዚህም የተነሳ የጀርመን መንግሥት የኒቻን የተቀየሩ ጽሑፎች ወስዶ ለውትድርና ማነቃቂያ፣ ወጣቶችን ለጦርነትና ለጭካኔ መገፋፊያ ፕሮፓጋንዳ አድርጎ ተጠቀመበት። በዚህ ተንኮል ምክንያት ኒቻ ለብዙ ዘመናት "የናዚ ፈላስፋ" ተብሎ በተሳሳተ መንገድ ሲጠላ ኖረ።

ነገር ግን አሁን ላይ ያለው አዲሱ ትውልድና ዘመናዊ ሳይንቲስቶች እውነቱን አውጥተዋል፤ የጽሑፎቹን ትክክለኛ ምንነት በመመርመር ኒቻ ስለ ሰብአዊነትና ስለ ውስጣዊ ኃይል እንጂ ስለ ናዚዝም እንዳልጻፈ በሚገባ ተረድተውታል።

<u>የጽንሰ-ሀሳብ ማብራሪያ (Concept Clarification)</u>

አብዛኛው ሰው "ሥልጣን" ወይም "ኃይል" (Power) ሲባል በአእምሮው የሚመጣው የጡንቻ ጉልበት፣ የጦር መሳሪያ ወይም ሰዎችን በግዴታ መግዛትና የበላይ መሆን ብቻ ነው። ነገር ግን የኒቼን ፍልስፍና በጥልቀት ለመረዳት፣ አስቀድመን "ኃይል ምንድነው?" የሚለውን ነገር በትክክል ማየት ይኖርብናል።

ነገሩን ቀለል አድርገን ለመመልከት ኃይል ማለት ማድረግ የመቻል አቅም (The capacity to act/do) ማለት ነው። ለምሳሌ ከ 50 ብር እና ከ 500 ብር ብንነሳ፣ ይበልጥ ኃያሉ 500 ብር ነው፤ ምክንያቱም የተሻለና የበዛ ነገርን የማድረግ (የመግዛት) አቅም አለው። ነገር ግን ይህ ኃይል አንጻራዊ ነው፤ ኃያልነቱ የሚወሰነው ባለበት ቦታና ሁኔታ ላይ ነው። ለምሳሌ ከ 500 ብር አጠገብ 5,000 ብር ሲመጣ፣ ቅድም "ኃያል" የተባለችው 500 ብር አሁን ወዲያው ተበልጣለች ። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ኃይል ዘላቂ አንድ ቅርጽ የለውም፣ ቅርጹን ይቀያይራል እንጂ። ያን ጊዜ ነው እንግዲህ "ገንዘብ" ተብሎ የሚጠራው።

“የምን ገንዘብ? አሁን ስለ ገንዘብ አላወራንም እንዴ?” ካላችሁ፣ መልሱ አዎም አይደለምም ነው! ምክንያቱም ቅድም ያወራነው ስለ ብር (currency) ብቻ ነው። እኔ እዚህ ጋር “ገንዘብ” የምለው ኃይል ያለውን አጠቃላይ መግለጫና ቅርጽ ነው። ለምሳሌ፦ የአንድ ተማሪ እውነተኛ ገንዘቡ ትምህርቱና እውቀቱ ነው፤ የአንዲት እናት ትልቁ ገንዘቧ ልጇ ነው፤ የባለሀብት ገንዘቡና ንብረቱ ሲሆን፣ የገበሬው ደግሞ ከብቶቹ ናቸው። የአንድ ጻድቅ ሰው ገንዘቡ ደግሞ የሠራው ጽድቅ ነው። ስለዚህ ኃይል በእነዚህና በሌሎች ልዩ ልዩ ቅርጾች ራሱን ይገልጻል።

ማድረግ አለመቻል ደግሞ የኃይል ተቃራኒ የሆነው “ድህነት” ይሆናል። ድህነት ማለት “ማድረግ አለመቻል” ማለት ነው። ከሁሉም አስከፊ ነው ብዬ የማስበው የድህነት ዓይነት ግን “በማሰብ ብቻ መቅረት” የሚባለው የጭንቅላት ድህነት ሳይሆን፣ የቁስ ድህነት ነው። በዚህ የድህነት ዓይነት በብዛት የተቀጡት የጥንት ሊቃውንትና አሳቢዎች ነበሩ። ምን የመሰለ ድንቅ ጭንቅላት ኖሯቸው፣ ነገር ግን ያሰቡትን ረቂቅ ሐሳብ ወደ እውነተኛው ዓለም ለማምጣት የሚሆን ቁሳዊ ኃይል (ገንዘብ) ዓለም አልሰጠቻቸውም። ለምሳሌ፦ አንድ የጥንት ዘመን ሊቅ “በ 500 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሆኖ ወዲያውኑ መልዕክት መለዋወጥ እንዴት ይቻላል?” ብሎ በጭንቅላቱ ቢያስብም፣ በዘመኑ ቁሳዊ አቅም ወደ ተግባር ማዋል አይችልም ነበር። ስለዚህ የተሻለ የሚሆነው እዚያው በሐሳብ የሚደረግ ረቂቅ ፈጠራና ምርምርን መምረጥ ነው፤ በዚህም ምክንያት ወደ ፍልስፍና ያደላሉ። በዘመናችን ፈላስፋ የማናየው ወይም ፍልስፍና እየተመናመነ የመጣው ለዚህ ነው! አሁን ላይ ሊቃውንቱ ያሰቡትን ሁሉ ወደ ምድር ለማውረድ ዓለም ቁሳዊ አቅሟን ፈቅዳላቸዋለች። ጨረቃ ላይ መውጣት አሰብን አደረግነው፤ በሰማይ መብረር አሰብን አደረግነው! ለዚህ ነው አሁን ያለው ትውልድ ከሐሳባዊ (Philosophical) ይልቅ ወደ ቁሳዊ (Material) ፈጠራ ያደላው። ከዚህ ዝቅ ሲል ግን የበለጠ አስከፊው ድህነት ይመጣል ለምሳሌ፦ በጣም ምርጥ የቢዝነስ ፕላን ኖሮህ በቁስ ድህነት

የተነሳ ምንም ማድረግ ሳትችል ስትቀር፣ ወይም እንጀራ ለመብላት ፈልገህ ማግኘት አቅቶህ ሳትበላ ስትቀር... እነዚህ በማሰብና በመመኘት ብቻ የሚቀሩ አስከፊ የድህነት ገጾች ናቸው።

ነገር ግን ማስተዋል ያለብን ነገር፣ ኃይል እና ድክመት ፈጽሞ የሚነጣጠሉ ነገሮች አይደሉም፤ እርስ በርሳቸው የሚተጋገዙ እንጂ! በፊዚክስ ሕግ (Law of Conservation of Energy) "ኃይል አይፈጠርም፣ አይጠፋምም፤ ቅርጹን ይቀይራል እንጂ" እንደሚባለው ሁሉ፣ በእውነተኛው አለምም ላይ እንዲሁ ነው።

ለምሳሌ፦ በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ ባይታመም እና ፍጹም ጤነኛ ቢሆን ኖሮ፣ በዓለም ላይ በትሪሊዮን የሚቆጠር የህክምናና የመድኃኒት ቢዝነስ ተቋረጠ ማለት ነበር። ያ ሁሉ ትሪሊዮን ገንዘብ በድንገት የተፈጠረ ሳይሆን፣ አስቀድሞ በበሽተኞች ደካሞች እጅ የነበረ ኃይል ነው። በሽታው ኃይሉን ከታማሚዎች ወስዶ ወደ ሕክምና ተቋማቱ ቀየረው፤ በዚህም ለዚያ ቦታ ኃይልን ሰጠ። በተመሳሳይ መልኩ፣ አንድ ሰው ለነዳያን እና ለችግረኞች ሲረዳ ወይም ሲያግዝ "ጽድቅ" እንደሚሆንለት በሁሉም ሃይማኖቶች ይታወቃል። ታዲያ ያንን ሰው ለማፅደቅና ኃያል ለማድረግ አስቀድሞ ያ ነዳይ ወይም ችግረኛ መኖር ነበረበት አይደል? በዚህ ነው እንግዲህ ኃይልና ድክመት እርስ በርሳቸው የሚተጋገዙና የማይነጣጠሉ ናቸው የምንለው።

እስኪ ይህንን ጥያቄ መልሱልኝ፦ የኃይል መጨረሻው ምንድነው? ሁለገብ አድርጋችሁ አስቡት፤ ከታላላቅ ሰዎች፣ ከታላላቅ አገራት፣ ከታላላቅ ድርጅቶች እስከ አጽናፈ ዓለም ድረስ እዩና የኃይል መጨረሻውን ንገሩኝ።

ነገሩ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ቢመስልም እውነታው ግን ይህ ነው **የኃይል መጨረሻው "ተራ መሆን" ነው።** በቃ! ኃይል ከፍተኛው ጥግ ላይ ሲደርስ መጨረሻው ተራ መሆን ነው። ያ ሁሉ የጦር መሣሪያ

ኃይል፣ ያ ሁሉ የዕውቀት ኃይል፣ ያ ሁሉ የሀብት ማማ ጥጉን ሲነካ በቃ ተራ ይሆናል!

ምናልባ እንዲህ ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፦ ዓለምን ሁሉ የፈጠረው ኃያሉ አምላክ ኪሩቤል እና ሱራፌል በግርማው ፊት የሚንቀጠቀጡለት፣ ከእሱ በላይ ምንም ኃይል ሊኖር የማይችለው ታላቁ አምላክስ ተራ ነው? መልሱ፦ አዎ ነው! ለምን እንዳልኩ ላስረዳችሁ።


እግዚአብሔር ይህንን የረቀቀ አጽናፈ ዓለም ሲፈጥር፣ ሲያከብር፣ ሲቀስፍ፣ እሳትን ከሰማይ ሲያወረድ፣ በፍል ውሃ ምድርን ሲቀጣ፣ ከአለት ላይ ውሃን ሲያፈለቅ የነበረ አምላክ፣ መጨረሻ ላይ ተራ ሆነ ከዙፋኑ ወረደ። ሰው ሆኖ በምድር ላይ ተመላለሰ፤ ተራበ፣ ተጠማ፣ አልፎም ተሰደበ፣ ተገረፈ። በዘመኑ የውርደት መጨረሻ በነበረው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ዓለምን አዳነ።

አምላክ ሆኖ ከነክብሩና በኃይሉ ማዳን ሲችል፣ እሱ ግን ተራ መሆንን መረጠ። ለምን? ምክንያቱም ይህኛው (ተራ የመሆኑ ምስጢር) ከቀደመው የመቅሰፍትና የመፍጠር ኃይሉ ይልቅ እጅግ የበረታና የላቀ የኃይል መጨረሻ ስለሆነ ነው! ለዚህም ነው አባቶቻችን ሊቃውንት “ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡና ኃይሉ ይልቅ፣ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡና ይበልጣል” ያሉት።

ይህንን ሐሳቤን የሚደግፍ ሆኖ ያገኘሁት “The Dunning-Kruger Effect” የተባለውን የስነ-ልቦና እውነታ ነው።

እስኪ ይህንን ለማየት የ 3 ተማሪዎችን ምሳሌ እንውሰድ። ሦስቱም ለፈተና ቀርበዋል፤ ፈታኙ ብሬ ስለነበር መኮረጅ አይታሰብም። የመጀመሪያው ተማሪ ስለ ትምህርት ምንም የሚያውቀው ነገር የሌለ ሰነፍ ነው፤ ሁለተኛው ተማሪ አጥንቶና ተዘጋጅቶ የመጣ መካከለኛ ነው፤ ሦስተኛው ልጅ ደግሞ ያንን ሳብጀክት (Subject)

ጥጥ አድርጎ ያጠና ቀለሜ ነው። የተሰጣቸው የፈተና ጊዜ 40 ደቂቃ ቢሆን፣ ጊዜያቸውን እንዴት የሚጠቀሙ ይመስላችኋል?



የመጀመሪያው ተማሪ ምንም የሚያውቀው ነገር ስለሌለ፣ በ 5 ደቂቃ ውስጥ ወዲያው ሞልቶ ይጨርሳል።

ሁለተኛው ተማሪ የተዘጋጀበትን በጥንቃቄና አስልቶ ስለሚሠራ፣ የተሰጠውን 40 ደቂቃ በጠቅላላ ይጠቀማል። ሦስተኛው ተማሪ ግን፣ ፈተናው በጣም ስለሚቀለውና ስላወቀው፣ ልክ እንደ መጀመሪያው ተማሪ ሁሉ በ 5 ደቂቃ ውስጥ ወዲያውኑ ሰርቶ ይጨርሳል።
እዚህ ጋር አስተውሉ፤ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ተማሪ የተለያየ ምክንያትና መነሻ ቢኖራቸውም፣ ያሳዩት ባህሪና ውጤት ግን ፍጹም ተመሳሳይ ነው (ሁለቱም በ 5 ደቂቃ ጨርሰዋል)።

ሌላ ምሳሌ ብንወስድ፦ ምንም ነገር የማያውቅ ተራ ሰው ይመጣና "እግዚአብሔር አለ፣ ሁሉንም ዓለም የፈጠረ እሱ ነው" ይላል።

ዓለምንና ሳይንስን መረዳት የጀመረው ሁለተኛው ሰው ይመጣና ደግሞ "እግዚአብሔር የሚባል የለም፤ ሁሉም ውሸት ነው፤ ዓለም በተፈጥሮ ሥርዓት የምትመራ እንጂ አስተዳዳሪ የላትም" ይላል።

ሦስተኛው እውነተኛው ጥግ የደረሰው ሊቅ ሲመጣ ግን፣ ድጋሚ መለስ ይልና "እግዚአብሔር አለ! የዚህ ሁሉ ረቂቅ የተፈጥሮ ሥርዓት ባለቤት እሱ ነው" ይላል።

በመጀመሪያው (ተራው) እና በመጨረሻው (ሊቁ) ሰው መካከል የውጤት ተመሳሳይነት አለ፤ ነገር ግን ምክንያታቸው ፍጹም የተለያየ ነው። ይህም የሚያሳየው ኃይልና እውቀት ወደ ላይ ብቻ ቀጥ ብሎ የሚሄድ ሳይሆን፣ ሳይክል (Cycle) እያደረገ ወደነበረበት "ተራነት" እየተመላለሰ የሚኖር መሆኑን ነው። ነገር ግን ማጎበረሰቡ የሚያየውና የኃይል ምልክት የሚያሳየው ያንን መካከለኛውን (2ኛውን ደረጃ) ብቻ ነው።

የጃፓኑ ዝነኛ የአኒሜሽን ደራሲ ቲቴ ኩቦ (Bleach Mangaka) (Tite Kubo)፣አይዘን ሶስኬ (Aizen Sosuke) በተሰኘው ዝነኛ እና ተወዳጅ ካራክተሩ በኩል ስለ ኃይልና ሥልጣን ያለውን እይታ የሚገልጽ አንድ ድንቅ የፍልስፍና ንግግር አለው።

አይዘን እንዲህ ይላል፦"No one can survive without trusting someone, someone they feel is better, more worthy than themselves. Those who are worthy look even higher, searching for more superior beings. And those superior do the same. This is how all kings are created it is also how Gods are born."

ትርጉም፦ (ማንም ሰው ከራሱ የተሻለና የሚበልጥ መስሎ የሚሰማውን አካል ሳይታመንና ሳይደገፍ በሕይወት መቆየት አይችልም። ያ የሚበልጠውና የበላይ የተባለው አካል ደግሞ ከእሱየበለጠ ከፍተኛ ኃይል ያለውን የበላይ ፍጡር ወደ ላይ ይመለከታል። ያ የበላዩም በተመሳሳይ ይበልጡን ይፈልጋል። ነገሥታት በሙሉ የሚፈጠሩት በዚህ መልኩ ነው፤ ልክ እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔርም እንዲህ ነው የሚወደለው)

ዓለም የምትመራው በእንደዚህ ዓይነት የኃይል ሰንሰለት ነው። እሱ "እግዚአብሔር ተወለደ" ሲል በሰዎች ልብ ውስጥ ማለቱ ነው። በጥንት ዘመን የነበሩ ሰዎች ለተፈጥሯዊ

ክስተቶች ፍጹም እንግዳና ደካማ ነበሩ። ለምሳሌ ኃይለኛ ጎርፍ መጥቶ ያለ የሌለ ሀብታቸውን ጥርግርግ አድርጎ ሲወስድባቸው፣ ወይም መብረቅ ወድቆ የሕይወትና የንብረት ጉዳት ሲያደርስባቸው ክፉኛ ይፈሩ ነበር። ከእነሱ የሚበልጥና ከተፈጥሮ ቁጣ የሚጠብቃቸው ኃያል አካል ይፈልጋሉ፤ በዚህም በውስጣቸው "እግዚአብሔር" ይወለዳል። ለሱ እየተገዙ፣ እነሱ ከማይችሉት ተፈጥሮ እንዲጠብቃቸው ይማጸናሉ። ይህንን ጥበቃ ያገኙበትን ነገር ሁሉ ደግሞ አምላካቸው ያደርጉታል። ለምሳሌ ጎርፍ ሲያጥለቀልቃቸው ሮጠው ወደ ተራራ ወጥተው ሲድኑ፣ "አምላክ ማለት ይህ ተራራ ነው" ብለው ያማረውንና የተዋበውን መሥዋዕት ለተራራው ያደርጋሉ፤ ወይም አውሬ ሊበላቸው ሲያሳድዳቸው ትልቅ ዛፍ ላይ ወጥተው ሲድኑ፣ "አምላክ ዛፍ ነው" ብለው ያመልኩታል። በጥንት ዘመን ጣኦት አምላኪነት በጣም የተለመደ የነበረው ለዚህ ነው።

ነገሩን ቀለል አድርገን በዘመናችን እንኳ ብናየው፡ ፈተና ኖሮብን በደንብ ከተዘጋጀን ገብተን ሰርተን እንወጣለን፤ ነገር ግን ምንም የማናውቅ ከሆነ፣ ወዲያው በልባችን አምላክ ይወለድና "ፈጣሪ ሆይ እርዳኝ" ብለን ጸሎት መጸለይ እንጀምራለን።

ሁሉም ነገር የሚወጠጣው በገባበት ነውና፤ መብረቅ እንዳይጎዳን የመብረቅ መከላከያ (Lightning rod) ሠራን፣ ጎርፍን በግድብ ከለከልን፣ በሽታን በክትባት አሸነፍን። አሁን መብረቅና የተፈጥሮ አደጋ ስለማያስፈራን "እግዚአብሔር አሁን ምን ይሰራልኛል?" ማለት ጀመርን።

በዚህም ምክንያት ከሌላው ጊዜ በበለጠ አሁን ባለው ዘመን "ፈጣሪ የለም" የሚል የኤቲዝም (Atheism) አመለካከት ተሰራጨ።

ይህም የሚሆነው አስቀድሞ ከፈጣሪ ጋር በነበረን የ"ጥቅም" ግንኙነት የተነሳ ነው። የማንችለውና አቅም የሚያጥረን ነገር ሲመጣ ብቻ ነው በልባችን እግዚአብሔር የሚወለደው፤ ይህ ደግሞ

ግንኙነቱን የጥቅምና የራስ ወዳድነት ያደርገዋል። ነገር ግን ያላወቅነው ነገር ቢኖር፣ እግዚአብሔር የደካሞች ብቻ ሳይሆን፣ የኃያላንም አምላክ ጭምር መሆኑን ነው!

እስካሁን ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ሞራል ነው እያልን መጥተናል ሞራል ግን እንዴት ነው የሚፈጠረው ? ሞራል እንዴት ነው በሰዎች ልብ ውስጥ የሚወለደው ? ለዘመናት አከራካሪ የሆኑ ብዙ ጉዳዮች ብዙ ያልተሰሩ የቤት ስራዎችን የያዘ ጉዳይ ቢሆንም ነገር ግን እሱን እነ ኢማኑኤል ካንት ይጨነቁበት ብለን ትተን ከአከራካሪ ርእሶቹ ባሻገር እንዴት ይወለዳል የሚለውን እንይ ::

ሞራል የሚወለደው በ ኃይል እና ድክመት መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያገለግል ድልድይ ሆኖ ነው ::
ነገር ግን ኃይልም ሆነ ድክመት ወጥ የሆነ ወይም ቋሚ የሆነ መለኪያ የላቸውም ይልቁንስ እንደየቦታቸው ይወሰናሉ :: ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ ሆኖ ያገኘሁት radar chart ወይም spider chart የሚባለው ነው ሀሳቡ እንድን አካል በተለያዩ መመዘኛዎች ብቃቱን መፈተን ነው ለምሳሌ የአንድን መኪና ብቃት ለመወሰን ፍጥነትና ጉልበት ፣ ነዳጅ ቆጣቢነት ፣ ምቾት ፣ ዋጋ ፣ ደህንነት safety ፣ ወዘተ በሚል መስፈርት ይመዝነዋል ከዛ ሁሉንም መመዘኛዎች ከ10 ቢይዛቸው ፍጥነት 9 ቢያመጣ ሌሎቹን ደግሞ 7,6,7,5,7 ቢያመጣ ያመኪና በፍጥነት መመዘኛ ባስመዘገበው ከፍተኛ ነጥብ ፈጣን ተብሎ ይጠራል ነገር ግን በውስጡ ሌሎቹንም ያሟላል መጠሪያው የሚሆነው ግን ከሁሉም ጎልቶ በወጣው ብቃቱ ነው ::



ይህንን በምሳሌ ለመረዳት ምርጡ እና ቀላሉ ምሳሌ የኢሶጵ ተረት የሆነው "አንበሳ እና አይጥ" ታሪክ ነው::

አንበሳና አይጥ

አንድ ቀን፣ የአራዊት ንጉሥ የሆነው አንበሳ በጫካ ውስጥ ባለው ጥላ ሥር ጋደም ብሎ ከባድ እንቅልፍ ወስዶት ነበር። በዚህ ጊዜ አንዲት ትንሽ አይጥ በጫካው ውስጥ በደስታ ስትሮጥ፣ ሳታስበው በተኛው አንበሳ አካል ላይ ወጣችና መጫወት ጀመረች። በአፍንጫውና በባቱ ላይ ስትረማመድ አንበሳው ከእንቅልፉ ተነሳ። አንበሳው በከፍተኛ ንዴት እያጉረመረመ ነቃ! ትልቁንና ኃይለኛውን መዳፉን ዘርግቶ ትንሿን አይጥ ያዛትና ሊውጣት አፉን ከፈተ።

ትንሿ አይጥ በከፍተኛ ፍርሃት እየተንቀጠቀጠች መማጸን ጀመረች፦

"እባክህ የንጉሦች ንጉሥ! ማረኝ፣ አትግደለኝ! በዚህ ጊዜ ብትምረኝ ውለታህን መቼም አልረሳውም። አንድ ቀን እኔም አንተን ልረዳህ እችል ይሆናል!"

አንበሳው ይህንን ሲሰማ በሳቅ ፈረሰ። *"አንቺ ትንሿ ፍጡር እኔን ታላቁን ንጉሥ እንዴት ልትረጂኝ ትችያለሽ?"* በማለት በነገሩ በመገረም፣ምን እንደምታመጣ ለማየት መዳፉን አነሳና ለቀቃት። አይጧም እግሬ አውጪኝ ብላ አመለጠች።

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ አንበሳው በጫካው ውስጥ ለምግብ ፍለጋ ሲዘዋወር አዳኞች በዘረጉለት ጠንካራ መረብ ውስጥ ወደቀ። ምንም ያህል ቢታገልና ቢፈራገጥ ከመረቡ ሊያመልጥ አልቻለም። በከፍተኛ ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ ጫካውን ባናወጠ ድምፅ ይጮኽና ያገሳ ጀመር።

በዚያው አቅራቢያ የነበረችው ትንሿ አይጥ የአንበሳውን የጭንቀት ጩኸት ሰማች። ወዲያውኑ ድምፁን ተከትላ ወደ ቦታው ፈጠነች። አንበሳው በመረብ ተጠፍሮ ሲያለቅስ ስታየው፦

"ንጉሥ ሆይ፣ አትፍራ! እኔ አድንሃለሁ" አለችው።

አይጧ በሹል ጥርሶቿ የመረቡን ገመዶች አንድ በአንድ በጥንቃቄ መበጣጠስ ጀመረች። ብዙም ሳይቆይ ዋና ዋናዎቹን ገመዶች በጣጥሳ አንበሳው እንዲያመልጥ አደረገችው።

አንበሳው ከመረቡ ወጥቶ ነፃ ከሆነ በኋላ ወደ ትንሿ አይጥ ተመልክቶ በታላቅ አክብሮት እንዲህ አላት፦

"በዚያ ቀን 'እረዳሃለሁ' ስትይኝ ሰቁብሽ ነበር። ዛሬ ግን ትንሿ አይጥም የታላቁን አንበሳ ሕይወት ማዳን እንደምትችል በተግባር አሳየሽኝ።"

ከዚያ ቀን ጀምሮ በአንበሳውና በአይጧ መካከል ያለው የ"አዳኝና የታደኝ" ወይም የ"ገዢና የተገዢ" ግንኙነት አበቃ። አንበሳው ለአይጧ የነበረው የንቀት ስሜት ጠፍቶ፣ በጫካው ውስጥ ካሉት እንስሳት ሁሉ በላይ ትልቅ ክብር ይሰጣት ጀመር። ትንሿ አይጥም የአንበሳው የቅርብ አማካሪና እውነተኛ ጓደኛ ሆነች።

1. ሰሙ (ገጸ ባህሪያቱ እና የሃይል ደረጃቸው)

- **አንበሳው (ሀያሉ)**፡ የጫካው ንጉስ ነው፣ ጉልበት አለው፣ ማንም አይደፍረውም፣ ሁሉንም የመግዛት አቅም አለው።
- **አይጧ (ደካማዋ)**፡ ትንሽ ናት፣ ጉልበት የላትም፣ በቀላሉ ልትረገጥ የምትችል ናት።

2. ወርቁ (ሞራሉ የት ላይ ነው?) እዚህ ጋር ሀያሉ (አንበሳው) የሌለውን ክህሎት ደካማዋ (አይጧ) አላት።

- በዚህ ጊዜ በመካከላቸው የተፈጠረው የአንበሳው ድክመትና የአይጧ ኃያልነት "ሞራልን" ሊፈጥር ችሏል በዚህም በሁለቱ

መካከል ያለውን የኃይል ልዩነት እንደ ድልድህ ሁኖ እኩል አድርጓቸዋል ::

በዚህ መንገድ ኃይል እና ድክመት ያላቸውን ክፍተን እኩል ለማድረግ ድልድይ ሆኖ በልባችን ውስጥ ይወለዳል ነገር ግን ይህ ስርአት እኛ የሰው ልጆች ልይ ብቻ ነው የሚሰራው እኛ ግን በዚህ ስርአት ዓለም እንድትመራበት እንጠብቃለን ታማኝ የሆነ እንዲሳካለት ወንጀለኛና አጭበርባሪ እንዲቀጣ እንዲከስር ወዘተ ዓለም ላይ ግን በተቃራኒው ነው ዓለም የምትመራበት ህግ ሞራል አይደለም በዚህ የተነሳ እንደ ክፉ እናያታለን እንጠላታለን፤ ዓለም የምትመራበት ህግ ማን በመንገዱ ሔደ ነው መንገዱ ምንም አይነት ይሁን ተከትለህ ከሔድክ ማንም ሆንክ ማን ትሰጥሃለች ::

የኃይል ፍላጎት (The Will to Power) ማብራሪያ

ይህኛው የ Will ዓይነት በውስጣችን የሚሞላልን ጎደሎ ነገር ኃይልን ነው:: ኃይልን እየሞላ በሕይወት እንድንቆይ ያደርገናል

ለምሳሌ አሁን ላይ ምንም ነገር የለህም እንበል:: አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታህ ሆነህ፦ “እንደው አንድ 50 ሚሊዮን ብር ቢኖረኝ ኖሮ ከዚህ በላይ ምንም ነገር አልፈልግም ነበር፤ ምርጥ ቤት ይኖረኛል፣ መኪና እገዛለሁ... በአጠቃላይ ጽድት ያለና የተደላደለ ኑሮ እኖር ነበር” ትላለህ::

ነገር ግን እውነታው እንደዛ አይደለም! አንዴ የተመኘኸው 50 ሚሊዮን ብር እውን ሆኖ እጅህ ላይ የገባ ዕለት፣ ወዲያውኑ መቶ ሚሊዮኖች ይታዩሀል :: መቶው ሲሞላ ደግሞ ወደ ቢሊዮኖች ለመድረስ ትጓጓለህ::

እዚህ ጋር ልታስተውለው የሚገባው ሚስጢር፦ አንተ የፈለግኸው ቁሱን ወይም ገንዘቡን አይደለም፤ ከጅምሩ በውስጥህ ያለውና የሚያስገድድህ የ Will to Power (የኃይል ፍላጎት) ነው። ሁልጊዜም ከበላይ እንድትሆን፣ በዙሪያህ ባለው ነገር ላይ ቁጥጥርና ኃይል እንዲኖርህ የሚያደርግህ እሱ ነው። ያንን ኃይል ለማሳደድ በምታደርገው ጉዞ ደግሞ በሕይወት እንድትኖር ያደርግሃል።

ሀገራችን በአንድ ወቅት መላው ዜጋ ቀንና ሌሊት ይረባረብ የነበረው ለ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ነበረ። ልክ ያንን ግድብ ገድበን ጨረስን ካልን በኋላ ገን ወዲያውኑ ቀጥታ ወደ ቀይ ባሕር ነው የተሻገርነው። አሁን ደግሞ ልክ እንደ ግድቡ ሁሉ የሕልውና ጉዳያችን የባሕር በር ሆኗል። ይህም የሆነው በዚሁ በ ኃይል ፍላጎት የተነሳ ነው

ይህ የኃይል ፍላጎት ሥርዓት ብዙውን ጊዜ በአንድ በኩል ደግሞ Comfort Zone (የምቾት ቀጠና) ውስጥ ተደብቀን እንድንቆይ ያደርገናል። የምንችለውና የምናውቀው ነገር በሙሉ ለእኛ ኃይላችን መገለጫ ነው። ያንን የምናውቀውን የኃይል እናጥርና በውስጡ እንደ ልባችን እንፈነጥዝበታለን፤ ነገር ግን ከዚያ ከለመድነው አጥር መውጣት ፍርሃት ይለቅብናል።

ይህንን ይበልጥ ለመረዳት በትምህርት ሕይወት ውስጥ የሚገጥመንን አንድ ቀላል ምሳሌ እንመልከት

አንተ በትምህርት ቤት ሒሳብን (Maths) ወይም አንድን የትምህርት ዓይነት ፍፁም የምትጠላ ሰው ነህ እንበል። በቃ ያ ትምህርት ጭንቀት ይሆንብሃል፣ መጽሐፉን ስታየው እንኳ ያስጠላሃል። ነገር ግን የሆነ ቀን፣ በአጋጣሚ በጥሩ አስተማሪ ወይም በትጋትህ ያንን ከባድ ትምህርት 'ከተረዳኸው' እና ሚስጢሩ ከገባህ በኋላ በውስጥህ ትልቅ ደስታና መነቃቃት ይፈጠራል። ወዲያውኑ ፍርሃትህ ጠፍቶ

“ተማር ተማር፣ አሁኑኑ አንብብ” የሚልህ የውስጥ ስሜት ይቀሰቀሳል።

ለምን መሰለህ? ምክንያቱም ያ ትምህርት ቀድሞ ካንተ የዕውቀት ኃይል ውጭ የነበረ ‘የማይታወቅ ጠላት’ ስለነበር ውስጥህ ይሸሸው ነበር። አንዴ ግን ዕውቀቱን ጨብጠህ በሱ ላይ ኃይል ስታገኝ፣ አጥሮቹን ሰብረህ አዲስ የኃይል ቀጠና ፈጠርክ ማለት ነው።

ይህ ሥርዓት መሠረታዊ አሰራሩ እኛን ከአደጋ ለመጠበቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነበር። በውስጣችን ያለው መከላከያ፡ “የማይታወቅና አዲስ ነገር ከሆነ ጠላት ሊሆን ይችላል፣ ስለዚህ እዚያ ውስጥ አትግባ” በሚል ስጋት ይመራናል። እኛ ግን ይህንን መከላከያ አላግባብ በመጠቀም Comfort Zoneን አላስፈላጊ በሆነ መልኩ እንዳናድግ፣ አዳዲስ ነገሮችን እንዳንመረምር ገድቦ የሚይዘን ሰንሰለት አድርገነዋል።

እዚህ ላይ ጥፋቱ የሥርዓቱ ሳይሆን የኛ የራሳችን ነው! እሱ ዕውር ሥርዓት ስለሆነ የውጭውን ዓለም ማየት የሚችለው በእኛ በኩል ብቻ ነው። እኛ ግን ለዚህ ዕውር ሥርዓት የምናሳየው የውጭው ዓለም ጠማማ ጠማማውን ብቻ ሆነ። ይህ ሁሉ ቀውስ የሚፈጠረው ደግሞ፣ ራሳችንንና የውስጥ ፍላጎታችንን ባለማወቃችን የተነሳ ነው።

የፍቅር ፍላጎት The Will to Love



እስካሁን ድረስ አስቀድሜ ታሪካቸውን ያስነበብኳችሁን ሁለቱን ታላላቅ ፈላስፎች ምናልባት ስለ እነሱ ሰምታችሁ አልያም አስቀድማችሁ ታውቋቸው ይሆናል። ነገር ግን አሁን ላስተዋውቃችሁ ስላለው ስለዚህ ሰው ምንም ዓይነት ፍንጭ ይኖራችኋል ብዬ አላስብም። ይህ ሰው ማነው? **ፋሩቅ አልመግሪቢ** (Farouk Al-Maghribi) ማነው?

ፋሩቅ ትውልዱና እድገቱ ሞሮኮ ውስጥ ሲሆን፣ አሁን ላይ የ 30 ዓመት ወጣት ነው። ልክ እሱ ራሱ ደጋግሞ እንደሚለው ተራ ሰው ነው፤ ምንም ዓይነት የተለየ ነገር የለውም።

በጉርምስና ዕድሜው ላይ ባጋጠመው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድህነት የተነሳ፣ በቀን አንዴ ብቻ እስከ መብላት የሚደርሱ ብዙ አስቸጋሪና መራራ ጊዜያትን ለተከታታይ 10 ዓመታት አሳልፏል።

ከእነዚህ ከባድ ቀናት በአንዱ ቀን፣ በ MBC 2 የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ አንድ በጣም የሚስብ ፊልም እያየ ባለበት መሃል ድንገት መብራት ይጠፋል። ፊልሙ በጊዜው በጣም አጓጊቶት ስለነበር፣ ካቋረጠበት ለመቀጠል መብራት ሲመጣ ጠበቆ በጎረቤታቸው ዋይፋይ ግድግዳ ስር ተለጥፎ ለማውረድ ሞከረ። ነገር ግን ፊልሙን ለማውረድ ስልኩ በቂ የ Storage አቅም ስላልነበረው፣ የፊልሙ ሳይዝ (መጠን) ስልኩ ከሚይዘው አቅም በላይ ሆነበት። በዚህ ነገር ክፉኛ ተናደና ተበሳጭቶ ትቶት ወጣ።

በኋላ ግን አንድ ጓደኛው ያ ያየው ፊልም ከልብ ወለድ የተወሰደ መሆኑንና ልብ ወለዱን በጽሑፍ ማንበብ እንደሚችል መከረው። ኢንተርኔት ላይ ፈልጎ ሲያየው መጽሐፉን በ ጥቂት MB አገኘው! በሳይዙ ማነስ በጣም ደስ አለውና ወዲያውኑ አውርዶ አነበበው።

ከዚህ ቅጽበት ጀምሮ ነው እንግዲህ የፋሩቅ የማንበብ ባሕል የተጀመረው። እነዛን የጨለማና የድህነት ጊዜያት በማንበብና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስራዎችን በመመልከት አሳለፋቸው። ከነሱም መካከል ሥነ-ጽሑፋዊ ልብ ወለዶች (Literary Novel) ፣ ተከታታይና ተከታታይ ያልሆኑ የምዕራባውያን ፊልሞች፣ አብልጦ እስከ ሚወደው የምስራቁ ዓለም የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ወደ ሆኑት Web Novels፣ Light Novels፣ Manga (የጃፓን ኮሚክስ)፣ Manhua (የቻይና ኮሚክስ)፣Manhwa (የኮሪያ ኮሚክስ)፣ Anime እና በመጨረሻም አርፍዶ የጀመራቸው የፍልስፍና መጻሕፍት ናቸው።

ታዲያ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት እሱ ራሱ ሳያስበውና ሳይረዳው፣ በአእምሮው ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየበሰለ፣ ነገሮችን በጥልቀት የሚያስተውል እየሆነ መጣ። መጀመሪያ ላይ ለመዝናናትና ጊዜ ለማሳለፍ ብቻ ብሎ ያነበባቸው መጻሕፍትና ያያቸው ፊልሞች፣ ከጊዜያዊ መዝናናት ባለፈ፤ ልክ እኛ አሁን በምንዝናናበት ሳቅና ጨዋታ ልክ እንዳለቀ ሁሉም ነገር አብሮ እንደሚያልቀው በተቃራኒ በውስጡ ዘላቂና እጅግ የሚጠቅም አሻራ እየተውለት አልፉ።

ስለሚወደው ነገር ለመናገር እና ከእሱም የተወሰነ ገቢ ለማግኘት በማሰብ በከፈተው የዩቲዩብ (YouTube) ቻናል ባጠራቀማት ገንዘብ መጀመሪያ ላይ የማስተርስ ዲግሪውን ለመማር አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ በኋላ ግን ሐሳቡን ቀይሮ አሁንም ድረስ ወደሚኖርባት ወደ ፖላንድ አገር ለኑሮ ተሰደደ።

እዚያ አገር ሲደርስ ግን ሕይወት አልጋ በአልጋ አልሆነችለትም፤ በከፍተኛ የብቸኝነትና ድብርት (Depression) ተጠቃ። ከዚህ አስከፊ

የብቸኝነት ስሜት ለመላቀቅ በሚል፣ ቀደም ሲል በነበረው የዩቲዩብ ቻናሉ ላይ ቀጥታ ስርጭት (Live Stream) ማስተላለፍ ጀመረ።

በስትሪሙ ውስጥ ስለ ረቂቅና ጥልቅ የሕይወት ሐሳቦች፣ ስለ ፍልስፍና አወራለሁ ብሎ አስቦ ነበር፤ ነገር ግን ያገኘው ተመልካች በሙሉ ዋዛ ፈዛዛና ጨዋታዎችን ብቻ የሚወድ ሆነበት። በዚህ ነገር እየተበሳጨና እየተናደደ፣ በስትሪሙ ላይ አልባሌና ጸያፍ የሆኑ ቃላትንና ቁጣዎችን መናገር ጀመረ። የሚገርመው ነገር፣ ተመልካቹ እሱ የተናገራቸውን እነዚያን ቁጣዎችና ቪዲዮዎች እያቆራረጡ በሶሻል ሚዲያ (ቲክቶክና ፌስቡክ) ላይ ለቀቋቸው። እነሱም ከፍተኛ እይታና ተመልካች አገኙ። በዚህም ምክንያት እሱ ፈጽሞ ባልፈለገውና ባላሰበው መንገድ በአንዴ ታዋቂ ሆነ።

“ይህንን ነገር ለማንም እናገራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር” ሲል ይጀምራል በ2022 ኪታር የ ዓለም ዋንጫ በምታዘጋጅበት ወቅት ላይ ባድገው ቀጥታ ስርጭት “እኔ በዚህ መንገድ አይደለም ሰው እንዲያውቀኝ የምፈለገው የራሴ የሆነ ፍልስፍና አለኝ ግን ለማንም እናገራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበረ፤ ወቅቱ አንደኛ አመት የ University ተማሪ የነበርኩበት ነው በትምህርቴ ከፍተኛ አወዳደቅ የወደቅሁበት ነበር እናም የራሴን ፍልስፍና ስፅፍ ነበር ምንም እንኳ በወቅቱ የፍልስፍና ማንበብ ቀርቶ በጊዜው ዝነኛ የሚባሉትንም ፍልስፍናዎች አላውቅም ነበር ።

ሆኖም ግን ስለ ክፋት የሚያብራራ ፍልስፍና ላይ ደርሼ ነበር የሰው ልጅ ተፈጥሮው ክፋት ነው ደግነት ማለት ዝቅተኛ የክፋት መጠን ማለት ነው ደግ ሰው የሚባል ነገር የለም ሁላችንም ክፉዎች አጭበርባሪዎችና አስመሳዮች ነን እያንዳንዳችን የታሪካችን hero/ጀግኖች ሳንሆን villain/ክፉዎች ነን እርስ በርሳችን መጎዳዳትና ከሁለም በላይ ደግሞ ራሳችንን መጉዳት ነው የሚል ነበረ ።

ተስፋ የመቁረጥ ፍልስፍና ነው በጊዜው ዝቅተኛው የህይወቴ ክፍል ላይ የነበርኩበት ነበረ ቤተሰቦቼ የጠበቁትንም አላደረኩም በሕይወትህ በጣም መጥፎው ነገር ቢኖር የጠበከው ነገር ሳይሳካ ሲቀር ነው አደርገዋለሁ ይሳካል ያልከው ሳይሳካ ሲቀር በራስህ ተስፋ ስትቆርት ይሄ ነው በጣም መጥፎው ነገር ሌላውማ ሌላ ነው ምንም ቢሆን ስሜቱን 100% ልትረዳው አትችልም የራስህን ስሜት ግን ትረዳለህ ::

እኔ የ ችግሬ/ሀዘኔ ጥግ ላይ እንደነበርኩ የታሪኬ villan/ክፉ ራሴ ነኝ ለሚያጋጥሙኝ ነገሮች በሙሉ ተጠያቂው እኔ ነኝ ብዬ አስብ ነበር ነገር ግን በጊዜ ሒደት ይህንን ፍልስፍና አሻሻልኩትና እስከመጨረሻው የክፋት ፍልስፍና የሚል ነገርን ተውኩ:: በምትኩ ከ አርተር ሾፕንሀወረና ፍሬድሪክ ኒቻ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ስለ ፍላጎት/Will የሚያስረዳ ፍልስፍና ላይ ደረስኩ እኔም ይህንን ፍልስፍና አሻሽዬ የፍቅር ፍላጎት ብዬ ጠራሁት ::

በጣም የማዝነው ግን ሁሌም ለመፃፍ እሞክርና እንዴት እንደምፅፍ ግን አላውቅም ስለ ዓለም ያለኝን ፍልስፍና እነዚህንና ሌሎችም መፃፍ በጣም ነው የምፈልገው ግን አላውቅም ምናልባት Professional ጸሐፊ ሐሳቤን እየነገርኩት እንዲፅፍልኝ ማድረግ እችላለሁ ግን ደሞ እኔ እንደዛ ለፍቼ ያመጣሁትን ሐሳብ የስነ ጽሑፍ ችሎታውን ብቻ ተጠቅሞ በራሱ ስም ቢያሳትመውስ? ብቻ አላውቅም የምናገረው ነገር ዋጋ እንዳለው ከማወቅ በስተቀር ::

ነገር ግን አሁን ላይ የምመራበት ፍልስፍና የዳቦ/እንጀራ ፍልስፍና ይባላል :: ፍልስፍናም ገደል ይግባ የራሱ ጉዳይ ሐሳብም ገደል ይግባ የራሱ ጉዳይ ምንም አይጠቅምም እንጀራህን ብቻ አሳድድ ጠረንጴዛህ ላይ እንጀራን ሊያመጣልህ የሚችልን ነገር ብቻ አድርግ::

በዚህ ፍልስፍና ሀሳባዊ የሆኑ ነገሮችን በሙሉ የማስወግድበት እና ቁሳዊ ነገር ላይ የማተኩርበት ነው ምክንያቱም ያኔ ስለ ፍልስፍና

በማስብበትና የፍልስፍና መፅሐፍ እፅፋለው ምናምን በምልበት ወቅት የማልረባ/loser ነበርኩ ነገር ግን ወደ እውነተኛው አለም ስወጣ እንጀራዬን ማሳደድ እና ኢኮኖሚዬን ማሻሻል ስጀምር ቀስ በቀስ እነዛ ሀሳቦች እየጠፉ መጡ የመኖር ትርጉሙ ምንድነው ምናምን የሚሉ ጥያቄዎች ጠፉ ለካ እነዛ ሀሳቦች ይመጡ የነበሩት ስራ በመፍታት ነው።

ብቻ አገላለፅ ስለማልችል ነው እንጂ የምናገረው ነገር ዋጋ እንዳለው አውቃለሁ።" ሲል ይናገራል

ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ ነውና አሁን ይህንን ፅሑፍ በማዘጋጅበት ሰአት ላይ ፋሩቅ እየፃፈ ያለውን እና ለመጠናቀቅ ጥቂት ገፆች የቀሩትን እንደተመኘው ስለ ተለያዩ ነገሮች ያነሳበትን ልክ እንደ ሾፕንሀወር መፅሐፍ (The World as Will and Representation) የመፅሐፉ መጠሪያ/ርዕስ ካደረገው የ እንጀራ ፍልስፍና ጨምሮ ብዙ ነገሮችን አንስቷል እናም ዋና ጉዳያችን ስለሆነው ስለ የፍቅር ፍላጎት/Will To Love የተናዘዘው በዚሁ ንግግሩ ነው ።

<u>የፍቅር ፍላጎት (The Will to Love) ማብራሪያ</u>

እዚህ ጋር እንድታስተውሉልኝ የምፈልገው ነገር ፍቅር ስል በወንድና ሴት መካከል ያለውን ፆታዊ(Romantic) ፍቅር አይደለም አሱ በ መኖር ፍላጎት/will to live ስር ነው ምድቡ በርግጥ አሁን ላይ ስለ ፍቅር መናገር አስቸጋሪ ነው ቅርፁን እየቀየርን እየቀየርን ወደአልሆነ ነገር ቀይረነዋል ። ፍቅር ስል እንደአጠቃላይ ከሰዎች የምናገኘውን ነው ከቤተሰብህ ከጓደኞችህ ከህዝብህ ወዘተ...

ይህ የ will ክፍል የሚሞላልን ጎደሎ ነገር ፍቅርን ነው ፍቅርን እየሰጠን በሕይወት እንድንቆይ ያደርገናል ።

ለዚህም ጥሩ ምሳሌ social media ነው ። ሶሻል ሚድያ ማለት የፍቅር ፍላጎታችንን የምንሞላበት ተቋም ነው በዚህ ከፍተኛ የፍቅር ጉደልት ባለበት ዘመን የሶሻል ሚድያዎች በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ስኬት ማስመዝገብ አይገርምም ።

ለምሳሌ አንድ ወጣትን እንመልከት ከፍተኛ ድብርት ውስጥ ገብቷል ህይወት ጨለም ብላበታለች ከዛ በ ሶሻል ሚድያ ላይ “ብንሄድ ይሻላል” ከዚህ በኋላመኖር እንደማይፈልግና ማረፍ እንደሚፈልግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያሳውቃል እዚጋ ልናስተውል የሚገባው ምንም እንኳ ያሰበው ልክ ባይሆንም ለብቻው ሊያደርጠው የሚችለው ነገር ነው ሶሻል ሚድያ ላይ መልቀቁ ምን አስፈለገ? ምክንያቱም የዚህ ወጣት ችግሩ ፍቅር ነው ውስጡም ያንን ፍቅር ስለሚፈልግ እየተጣራ ነው። እነዚህ ሰዎች የሚያዳምጣቸው አለሁ የሚላቸው ነው የሚፈልጉት።

ሌለው ደግሞ ፀሎታቸውን በ ሶሻል ሚድያ የሚፀልዩ "ፈጣሪዬ ሆይ የነገርኩህን አደራ" ወዘተ... የሚሉ ሰዎች ናቸው፤ ፈጣሪ ሶሻል ሚድያ ተጠቃሚ አይደለምኮ! ነገር ግን በውስጣቸው ያለው የፍቅር ፍላጎት ፍቅር ፍለጋ እየተጣራ ስለሆነ ነው።

ሌላው ደግሞ አንድ ወጣት ጂም እየሰራ ጥሩ የሰውነት ቅርፅ ገንብቷል በዚህ የተነሳ የሚያጋራቸው ፎቶዎቹ እና ቪድዮዎች የሰውነቱን ጡንቻ የሚያሳዩ ናቸው ወይም አንዲት ቆንጆ ልጅ የሚያምር አይን ካላት አይኗን መልክ ካላት መልኳን ቅርጽ ካላትም ቅርጿን ነው በሶሻል ማሚድያ የምታጋራው ይህም የሚሆነው አለን የምንለውን ኃይላችንን ተጠቅመን ፍቅርን ስለምንገዛ ነው፤ መኪና ያለው መኪናውን ያሳያል ስልክ ያለውም ስልኩን ወዘተ። ይህም በ Will to power እና Will to love መካከል ያለ ጥምረት ነው ። ነገር ግን ከላይ የጠቀስናቸው ነገሮች ኖሯቸው ግን የማያሳዩ አሉ ጥሩ ጡንቻ እያለው አያሳይም ቆንጆ ናት ግን አታሳይም ለሰዎች ማሳየት ግድ አይሰጣቸውም ይህ የሚሆነው እነዚህ ሰዎች አለን

የሚሉት ልላም ተጨማሪ ኃይል አላቸው ብዙውን ጊዜ ጂኒየሶች ናቸው ጥሩ ጭንቅላት አላቸው ::

ሌላው ደግሞ content creator'ኦችን የሚመለከት ነው በተለይ የዕለት ከእለት ኑሯቸውን እንዴት በቅንጦት እንደሚኖሩ የግል ጉዳያቸውን የሚያጋሩትን እኛም ምንም ከኛ ሕይወት ጋር የማይገናኝ ነገር ቁጭ ብለን እናያለን እነሱ በኛ በኩል የፍቅር ፍላጎታቸውን እየሞሉ ነው፤ እዚህ ጋር ግን የማናስተውለው አንድ ነገር አለ ከግል ተሞክሮዬ ጋር አጣምሬ ላስረዳችሁ::

አንድ ቀን ክላስ ውስጥ ቁጭ ብዬ እየፃፍኩ እጅ ፅሁፌን አልወደድኩትም ከዛ አስተካክዬ ስፅፍ ቆንጆ የሆነ የእጅ ፅሁፍ ወጣልኝ ወደድኩትና ደስብሎኝ መፃፍ ጀመርኩ ከዛ የፃፍኩትን ሳየው ተመልሶ ተበላሽቷል 5 መስመር ብቻ ነው ቆንጆ አድርጌ የፃፍኩት ከዛ ቡኃላ ያለው ተመልሶ ወደ ቀደሞው አስጠሊታ የእጅ ጽሁፍ ተቀይሯል በሁኔታው በጣም ተገርሜ ክስተቱን የእጅ ፅህፈት ህግ/The hand writing effect ብዬ ጠራሁት::

ይሄው ህግ ነው እነሱም ላይ የሚሆነው እነሱ የሚያሳዩን አለን የሚሉት ነገር ያቺን 5 መስመር ውብ ጽሑፍ ነው የቀረውን ይሸፍኑታል ፍቅር የሚገዛው አለን በምንለው ኃይል ነውና የቀረውን ገፅ እንኳን ሊያሳዩን ለራሳቸውም አይፈልጉትም ከዛ እኛ ያቺን 5 መስመር እናይና እንደነሱ ካልሆንን ብለን ሰላማችንን እናጣለን ይህ ነገር እነሱ ላይ ብቻም አይደለም ለምሳሌ አንድን ሰው ምክር አስፈልጎት አንተ ራሱ ከየት እንዳመጣኸው የማታውቀውን የሚገራርም ምክር ትመክረዋለህ አንተ ራስህ ግን አንዱንም አታደርገውም ሌላው ደግሞ አንዲትን ሴት ስትተዋወቅ መልአክ መስለህ ነው እሷም እንዲሁ ከዛ አንድላይ መሆን ከጀመራችሁ በኋላ የተሸፈነው ገፅ ይወጣል ያኔ እንደዚህ አይነት ሰው አትመስለኝም ተባብላችሁ ደግሞ ትለያያላችሁ ::

ከዚሁ ፍቅርን ባለን ኃይል የመሙላት ነገር ጋረ ተያይዞ አንድ ማስተዋል ያለብን ነገር ቢኖር አለን በምንለው ኃይላችን በተለይ ውጫዊ ኃይላችን እንደ መኪና፣ ቤት እና ብር የመሳሰሉ ቁሳዊዎቹን ማለት ነው። እነሱን ተጠቅመን ከሰዎች ፍቅርን እንገዛና ያ ኃይላችን ሲጠፋ ሁሉም የምንገዛው ፍቅር አይኖርም ሁሉም ነገር በገባበት ነውና የሚውጣው በዚህም ሰዎች ይርቁናል ያኔ ለምን ራቁን ሲኖረኝ ብቻ ነው እንዴ የሚፈለጉኝ ወዘተ ብለን ሰዎችን በክፉ ዓይን እናያለን ራሳችንንም እንደ ተበዳይ/Victim እናይና በተሳሳተ አመለካከት ሌሎች ችግሮች ውስጥ እንገባለን፤ ይህ የሚሆነውም ራሳችንን ባለማወቅ ነው።

የደስታ ፍላጎት (The Will to Happiness)



አንድን ሐሳብ ለመረዳት የሐሳቡን ባለቤት እንዴት እንደደረሰበት በሱ ቦታ ሁነን እሱ በተመለከተበት መነጽር ማየት አለብን ብዬ ስለማምን የሶስቱንም አሳቢዎች ግለ ታሪክ በጥቂቱ አስነብቤያችኋለሁ የእኔንም በመግቢያው ላይ ስላስነበብኳችሁ እንዴት ለመፃፍ እንደተነሳሳሁ ከመናገር በስተቀር ምንም የምጨምርላችሁ ነገር ::

ስለ will ካወቅሁ በኋላ ሁሉ ነገራችን ከሱ ጋር የተያያዘ መሆኑን አስተዋልኩ ስለ will የሰማሁትም ነገር ቢኖር ደረቅፍቺ እንጂ ዝርዝር ነገር አልነበረም :: ሀሳቡ ስለገባኝ ግን ከሁሉም ነገር ጋር እያገናኘሁ ይበልጥ ተረዳሁትና በጣም ስለወደድኩት እንዳይጠፋብኝ ብዬ ለራሴ መፃፍ ጀመርኩ ከዛ ሳየው ግን እኔ በተረዳሁበት መልኩ የሚያስረዳ ምንም ነገር የለም የ ፈላስፎቹ ፅሑፍ ላይ ራሱ እኔ በተረዳሁበት መልኩ ቀለል አድርጎ አያብራራም ስለዚህ ሌሎች ሰዎች የሚጠቀሙበት መስሎ ተሰማኝና ለራሴ ያልኩትን ለሁሉ አደረኩት::

ይህንን ፅሁፍ ሳዘጋጅ የከበደኝ ነገር ቢኖር 4ኛውና አዲሱ ፍልስፍና ነው የደስታ ፍላጎት/Will To Happiness፤ ስለ will በጣም ከመረዳቴ የተነሳ ነበረ በፍልስፍናው ውስጥ ጉድለት ታየኝና የደስታ ፍላጎት ላይ የደረስኩት :: ግን እኔ የመጀመሪያው አሳቢ ልሆን አልችልም ሌላ ሰው አስቦት ይሆናል ብዬ Internet ላይ ፈለኩኝ ማንም የቀደመኝ የለም ይልቁንም ተቀራራቢ ሐሳብ ያነሱ እንደነ **ኤፊቆሮስን** (Epicurus) እና **አሪስጣጣሊስን** (Aristotle) የመሳሰሉ የግሪክ ፈላስፎችን አገኘሁ ከዛ ፅሁፉን ሳዘጋጅ will to happiness የሚለውን ለብቻው ያለ ባለቤት ላቀርበው አሰብኩና ባዶውን ፃፍኩት ልክ ስምኦን "ድንግል በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ትወልዳለች"

የሚለውን ሲተረጉም ይህማ እንዴት ይሆናል ሰዉስ ምን ይለኛል ብሎ ድንግል የሚለውን ሴት እያለ እንደተረጎመውና መልአኩ እየፋቀ ድንግል ብሎ ሲፅፍበት ስምኦን ደግሞ መልሶ እየፋቀ ሴት ይል እንደነበረው እኔም አንዴ ባዶውን አንዴ ስሜን ስፅፍ ቆየሁና መጨረሻ ላይ ግን ለምን? አልኩኝ እነዛ ሰዎችኮ ስለ will አያውቁም በነሱ ጊዜ የነበረው free will/ነፃ ፍቃድ ነው ከአሁኑ ፍልስፍናምጋር ቀጥተኛ የሆነ ነገር አልተናገሩም ከሁሉም በላይ ደግሞ እኔ እነዛን ታላላቅ ሰዎች የምበልጣቸው አንድ ነገር አለ እኔ በሕይወት አለሁ እነሱ ግን የሉም ሞተዋል ምንም ነገር ማድረግ አይችሉም እኔ ግን አለሁ እነሱን መብለጥ እችላለሁ እነሱ ሊያደርጉ የማይችሁትን እኔ ማድረግ እችላለሁ ስለዚህ በስሜ ነው የምፅፈው በሕይወት ስላለሁ ብቻ እኔ እነሱን እበልጣለሁ **መኖር ብቻውን ማሸነፍ ነው** ::

<u>የደስታ ፍላጎት (The Will to Happiness) ማብራሪያ</u>

ይህ የ Will አይነት የሚሞላልን ጎደሎ ነገር ደስታን ነው ደስታን እየሞላ በሕይወት እንድንቆይ ያደርጋል

የሁሉም ነገር መነሻ፣ የሁሉም ነገር የመጨረሻ ግብና ዓላማ የሰው ልጅ በዘመኑ ሁሉ ያደረገው ይህችንኑ ደስታን ፍለጋ ነው። ከዚህ ቀደም በዚህ መጽሐፍ ላይ ስናያቸው የነበሩት የ'Will' ፍላጎቶች በሙሉ፣ መጨረሻ ላይ ተያይዘው የሚሰጡን ይህንኑ የደስታ ስሜት ነው።

በWill to Live አማካኝነት ብናፈቅር፣ ብንጋባና ልጅ ብንወልድ የሕይወትን ቀጣይነት የምንሻው ለደስታችን ስንል ነው። በWill to Power አማካኝነት ተምረን ዕውቀት ብናገኝ፣ ሀብትና ንብረት ብናከማች፣ አልፎም ሥልጣን ብንይዝ ይህ ሁሉ ልፋት ለዚሁ ለደስታ ስሜት ነው። በWill to Love አማካኝነት ከሰዎች ጋር ጥልቅ ትስስርና ፍቅርን ብንሻ ለዚሁ ደስታ ስንል ነው።

በአጠቃላይ፣ የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚያደርገው እያንዳንዱ ትግል፣ ድካምና ልፋት ይህችንኑ ደስታ ፍለጋ ነው።

ታላቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን (Albert Einstein) በአንድ ወቅት ያጋጠመው ገጠመኝ ሳስበው ይገርመኛል፤ እ.ኤ.አ 1992 ዓ.ም አንስታይን በጃፓን ቶኪዮ በሚገኘው የኢምፔሪያል ሆቴል እያለ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ዝናን ያተረፈበትን የኖቤል ሽልማት እንዳሸነፈ የሚገልጽ ዜና ደረሰው። በዚያው ቅጽበት አንድ መልእክተኛ ወደ ክፍሉ መጥቶ ደብዳቤ ሲሰጠው፣ አንስታይን ለመልእክተኛው የሚሰጠው ጥሬ ገንዘብ (ቲፕ) አልነበረውም።

በገንዘብ ምትክ ግን አንስታይን በሆቴሉ ማስታወሻ ወረቀት ላይ ስለ ደስታ ቀመር በጀርመንኛ ቋንቋ "ሞንጫር ሞንጫር" አድርጎ ሁለት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን ጻፈለት። ለመልእክተኛውም፦ *"ዕድለኛ ከሆንክ ይህች ወረቀት ወደፊት ከተራ ቲፕ የበለጠ ዋጋ ታወጣለች"* አለው። እ.ኤ.አ. በ2017 በኢየሩሳሌም በተደረገ የጨረታ ሽያጭ ላይ፣ ያቺ አንስታይን የሞነጫራት ታሪካዊት ወረቀት በ1.56 **ሚሊዮን ዶላር** ተሸጠች። የአለማችን ጂኒየሱ ሰው የደስታን ቀመር ደረሰበት መሆኑ ነው እንግዲህ።

ደስታ በትርጉም ላይ የተመሰረተ ነው። አንዱን የሚያስደስተው ነገር ሌላውን ፈጽሞ ማስደሰት አይችልም። ለምሳሌ አንድ ወጣትን ብንወስድና እሱ የእግር ኳስ ጨዋታን በጣም የሚወድ ቢሆን፣ ቀኑን ሙሉ ስለ ኳስ ማውራት፣ ጨዋታዎችን መከታተልና መጫወት ይፈልጋል። ኳስ ለሱ ሁሉ ነገሩ፣ ዓለሙ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ሌላኛውን ወጣት ብንመለከት፣ ኳስ ለእሱ በሜዳ ላይ የምትንደባለል ተራ ክብ ነገር ብቻ ናት፤ ምንም ስሜት አይሰጠውም።

ይህ ልዩነት የመጣው ሁለቱ ሰዎች ለኳስ ጨዋታ ከሰጡት "ትርጉም" የተነሳ ነው። ኳስ በራሱ ፍፁም አስደሳች ነገር ቢሆን

ኖሮ፣ ለሁለቱም እኩል ስሜትንና እኩል ደስታን በሰጣቸው ነበር። ስለዚህ ደስታ የሚመነጨው ከቁሱ ሳይሆን፣ እኛ ለቁሱ ከምንሰጠው ትርጉም ነው።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ እጅግ ዝነኛና አከራካሪ የሆነ Consequentialism የሚባል እሳቤ አለ። በኛ አነጋገር “የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጪው” አአይነት ነገር ነው።

ሰዎች ወደ ደስታ ለመድረስ በሚያደርጉት ጉዞ ላይም ይህንን መንገድ ሲከተሉ ይስተዋላል። “መንገዱ ምንም ይሁን ምን፣ ዋናው እኔን ደስ ይበለኝ” የሚል። ለዚህም በታሪክ በርካታ ክስተቶች ተመዝግበዋል።

ከነሱም ውስጥ የሮማውያን ታሪክን መመልከት እንችላለን። በታሪክ እጅግ ጨካኝና እብድ ተብሎ የሚታወቀው የሮማው ንጉሥ **ኔሮ** (Nero)፣ በ64 ዓ.ም. የሮም ከተማ በከባድ እሳት ስትቃጠልና ሕዝቡ በታላቅ ስቃይና ጭንቅ ውስጥ ሆኖ እየጮኸ ሳለ፣ እሱ ግን በቤተ-መንግሥቱ በረንዳ ላይ ቆሞ የሮምን መውደም በደስታ እየተመለከተ በገና (ሊራ) ይጫወትና ይዘምር ነበር ይባላል። የከተማዋ መቃጠልና የሰዎች ስቃይ ለእሱ የደስታ ምንጭ ሆኖለት ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የጥንት ሮማውያን በታላቁ ስታዲየም (Colosseum) ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሆነው ተቀምጠው፣ ግላዲያተሮች (ታጋዮች) እርስ በርስ ሲጨራረሱ ወይም የሰው ልጅ ከተራቡ አንበሶች ጋር ሲፋለምና በደም ሲታጠብ እያዩ በታላቅ ጩኸት ይደሰቱና ይጨበጭቡ ነበር። ደስታ ሲባል የዚህ ዓይነቱ ግራ የሚያጋባ ገጽታዎችም አሉት።

ስለ ደስታ እየተወራ አጅሬውን ዶፓሚንን (Dopamine) መዝለል ፈጽሞ አይቻልም! በተለይ ደግሞ በዚህ ዘመን በየሴኮንዱ በሚደረግ የሞባይል ስክሪን ንክኪ (Scrolling) የዶፓሚን ሱሰኛ ለሆንነው የዘመናችን ወጣቶች የዚህን ሆርሞን ሚስጢር ማወቅ ግድ ይላል።

ዶፓሚን ምንድን ነው? ዶፓሚን በአንጎላችን ውስጥ የሚመነጭ፣ ለሰውነታችን መልእክት የሚያስተላልፍ የነርቭ አስተላላፊ ኬሚካል (Neurotransmitter) ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች "የደስታ ኬሚካል" ይሉታል፤ እውነታው ግን ዶፓሚን የደስታ ሳይሆን **"የጉጉት፣ የፍላጎት እና የሽልማት ማሳደጃ"** (Anticipation and Motivation) ኬሚካል ነው።

ዛሬ ላይ የ Gen Z ትውልድ ይህንን ዶፓሚን በከፍተኛ መጠን የሚያገኝባቸው መንገዶች በጣም ቀላልና አደገኛ ናቸው። የማኅበራዊ ሚዲያ 'Like' እና 'Notification'፣ አጫጭር የቲክቶክና ኢንስታግራም ቪዲዮዎች (Shorts/Reels)፣ የቪዲዮ ጌሞች፣ እና ፈጣን ምግቦች አንጎላችንን በከፍተኛ የዶፓሚን መጠን ያጥለቀልቁታል። ይህ በስነ-ልቦናው እይታ **የሀዶኒክ ደስታ** (Hedonic Well-being) በመባል የሚታወቀው አይነት ጊዜያዊ ደስታ አመንጪ ነው።

በርግጥ ያለዚህ ዶፓሚን እኛ ምንም ዓይነት ተነሳሽነት የሌለን፣ ፍላጎት አልባ ደረቅ ሮቦቶች እንሆን ነበር። ነገር ግን ይህንን ዶፓሚን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረን መፍቀድ ፈጽሞ የለብንም። በሱ ተጽዕኖ ስር ሆነን የምንወስናቸው ውሳኔዎች በሙሉ አላስፈላጊና ስሜታዊ ስለሚሆኑ፣ በመጨረሻ ራሳችን ጋር እንድንጣላና ወደ ከባድ የጥፋተኝነት ስሜት ውስጥ እንድንገባ ያደርጉናል።

ለምሳሌ፦ በአንድ ወቅት ወደ እምነት ቦታ ሄደህ፣ አልያም አንድ በጣም ስሜት ቀስቃሽና አነቃቂ ንግግር (Motivational Speech) ሰምተህ በውስጥህ ከፍተኛ የዶፓሚን መነቃቃት ይፈጠራል። በዛች

ቅጽበት ከራስህ ጋር ቃል ትገባለህ፦ *“ከዛሬ ጀምሮ በየቀኑ እጸልያለሁ፣ እጾማለሁ፣ በደንብ አጠናለሁ፣ Gym እገባለሁ ወዘተ...”* ትላለህ። ነገር ግን በማግስቱ ጠዋት ስትነቃ፣ ትናንት ያንን ሁሉ ቃል እንድትገባ ያደረገህ ሙድ (የዶፓሚን መጠን) ሙሉ በሙሉ ቀዝቅዞ ታገኘዋለህ። ወዲያውኑ ራስህን፦ *“ትናንት ምን ነክቶኝ ነው እንደዛ ሰል የነበረው?”* ትላለህ። የገባኸውንም ቃል ሳትፈጽም ትቀራለህ፤ በዚህ የተነሳም በራስህ ላይ እምነት በማጣት ራስህን እንደማይረባና ደካማ ሰው አድርገህ መመልከት ትጀምራለህ።

ስለዚህ፣ ይህንን ሳንጠጣ እንድንሰክር፣ ሳንቅም እንድንመረቅን የሚያደርገንን አደገኛ የዶፓሚን መጠን ገደብ ልናበጅለት ይገባል። ይህ የቁጥጥር ሥርዓት **የዶፓሚን ጾም** (Dopamine Fasting) ተብሎ ይጠራል።

ይህንን ሆርሞን ለመዋጋት እጅግ አስቸጋሪ የሚያደርገው አንድ ትልቁ ተግዳሮት የተፈጥሮ ባህሪው ነው፦ **የዶፓሚን መጠናችን ወደ ላይ ሲጨምር አናውቀውም፤ ይልቁኑ የሚታወቀንና የሚሰማን መጠኑ ወደ ታች ሲቀዘቅዝ ነው!**

ስለዚህ አሁን ላይ የወሰንከው ውሳኔ በትክክል የራስህ ፍላጎት ነው፣ ወይስ በቅጽበታዊ የዶፓሚን መጨመር የመጣ ስሜት? ይህንን ለማወቅ ትልቁ መፍትሔ **ማንኛውንም ትልቅ ውሳኔ በዛች ቅጽበት ወዲያውኑ አለመወሰን** ነው። ይልቁኑ ውሳኔህን ለሚቀጥለው ቀን ማቆየት ይገባሃል። በቀጣዩ ቀን በአንጎልህ ውስጥ ያለው የኬሚካል መጠን ረግቶና ተረጋግቶ ስታገኘው፣ ትናንት ያሰብከውን ሐሳብ በምክንያታዊነት መዝነህ ትክክለኛውን ውሳኔ ትወስናለህ።

ልብ ልንለው የሚገባው ነገር፦ ይህ ማረጋገጫ የግድ በቀጣዩ ቀን ብቻ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ያንን ሐሳብ በአእምሮህ ስላሰብከው ብቻ በዛች ቅጽበት ድጋሚ የዶፓሚን መጠኑ ሊጨምር ይችላል። ስለዚህ ይበልጥ ቆም ብሎ መረጋጋትና አእምሮ ሙሉ በሙሉ ሰላም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ይህ አሰራር በዕለት ተዕለት የሥራና የትምህርት ሕይወታችን ላይ የሚኖረውን መዋዠቅ ደግሞ እንመልከት

ዛሬ ጠዋት ስትነቃ የመሥራት ፍላጎትህ በጣም ጨምሯል፤ ያለ የሌለ ኃይልህን ተጠቅመህ ቀኑን ሙሉ በትጋት ትሠራለህ። ስትጨርስም ባሳካኸው ነገር ልብህ በደስታ ይሞላል። በማግስቱ ጠዋት ወደ ሥራህ ትመጣለህ፤ ነገር ግን የዛሬው ቀን እንደ ትናንቱ አይደለም። የሥራ ሙድህ (Dopamine) አልመጣልህም። ስለዚህ ሥራውን እንደነገሩ ነካክተህ ትተኸው ትሄዳለህ። እንዲህ እያደረግህ ስትቀጥል፣ በሕይወትህ ብዙ ነገሮችን በከፍተኛ ስሜት ጀምረህ፣ ስሜቱ ሲቀዘቅዝ ደግሞ አጋማሽ ላይ የምትተወው ቀጣይነት (Consistency) የምታጣ ትሆናለህ ሕይወትህ በዶፓሚንህ መጠን ብቻ የሚወሰን የባርነት ሕይወት ይሆናል።

ነገር ግን በአንዳሩ ዛሬ የመሥራት(የመማር) ፍላጎታችን በጣም ጨምሮ፣ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ነገር ጠቅልለን ልንጨርሰው የምንችልበት ከፍተኛ ሙድ ላይ ሆነን እንኳ **“አይሆንም፣ ለዛሬ ይበቃል!”** ብለን የውስጥ ፍላጎታችንን በገዛ ፈቃዳችን ማስቆም አለብን።

ፍላጎቱ እያለህ በልኩ አቁመህ ለነገ ታስቀምጠዋለህ። በማግስቱ ስትመጣ፣ የመሥራት(የመማር) ፍላጎትህ እንደ ትናንቱ ላይኖር ይችላል፤ ነገር ግን ልክ ትናንት ፍላጎትህ እያለ በኃይል እንደገታኸው ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ፍላጎትህ ጠፍቶ እያለ በኃይል ቀስቅሰህ ታነሳዋለህ! ትናንት በሠራኸውና ባጠናኸው ልክ ዛሬም በተመሳሳይ ደረጃ ትሠራለህ።

በዚህ መንገድ ዶፓሚናችንን በመገደብና አጥሮች በማበጀት የፈለግነውን ቅርጽ እናስይዘዋለን። መሥራት ስንፈልግ **በልኩ**፣ መሥራት ሲያስጠላንም **በልኩ** በማድረግ፣ ከጊዜያዊ ስሜታችን በላይ የሆንን “ዓይናማ” መሪዎች እንሆናለን።

ለደስታ ያለን የተሳሳተ ግንዛቤ ማለትም ደስታ ማለት ፍጹም ምኞትና ችግር የሌለበት ሕይወት ነው ብሎ ማሰብ ለሁለተኛውና ለአስከፊው የሕይወት ገጽታ፣ ይኸውም ለሀዘን/ችግር አሳልፎ ይሰጠናል። ራሱ ችግርን አለመረዳት ትልቅ ጥፋት ነው። የሰው ልጅ ስህተት የሚጀምረው “በሕይወቴ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ አስወግዳለሁ” ብሎ ማሰብ ሲጀምር ነው። ችግርን ከሕይወት ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ፈጽሞ አይቻልም! ምክንያቱም አንድን ችግር ስንፈታ፣ ያ መፍትሔው ራሱ ሌላ አዲስ ችግርን ይወልዳል። እኛ ችግርን ስንፈታ አስቀድሞ የነበረውን ነባር ችግር እንፈታለን እንጂ ችግርን ሙሉ በሙሉ አናጠፋውም።

ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ሌቦች ቤቱን በተመሳሳይ ቁልፍ ከፍተው እንዳይሰርቁበት ለመከላከል ፈልጎ፣ ነባሩን ቁልፍ አስወግዶ ቤቱን በአሻራ (Fingerprint) ወይም በምስጢር ቃል (Password) በሚቆለፍ ዘመናዊ የዲጂታል ቁልፍ ይቆልፈዋል። በዚህ መፍትሔ ምክንያት ሌቦች መጥተው በተለመደው ዘዴ (በተመሳሳይ ቁልፍ መክፈት) ተጠቅመው መክፈት አይችሉም፤ ይህም ባለብቱ ችግሩን በተሳካ ሁኔታ እንዲፈታ አስችሎታል። ሙሉ በሙሉ ነው ግን? ፈጽሞ፤ አሁን አዲስ ችግር ተፈጥሯል የሳይበር ዕውቀትና የቴክኖሎጂ ክህሎት ያላቸው ሌሎች ሌቦች (Hackers) በሩን በዲጂታል መንገድ ሰብረው መግባት ይችላሉ። ሰውየው ያስቀረው የመጀመሪያውን ችግር እንጂ፣ ችግርን ሙሉ በሙሉ አይደለም። ይህ ማለት ችግር የሚጠፋ ነገር አይደለም፤ የአኗኗር ዘይቤያችን ሲቀየር አብሮ መልኩን የሚቀይር የሕይወት አካል ነው ማለት ነው “ችግር ጥበብን ይወልዳል” እንዲሉ አባቶቻችን አብሮን እየኖረ ጥበብን እንድንወልድ ያደርጋል።

ይህንን እውነታ እጅግ አጥርተው የተረዱት የStoic (ስቶይክ) ፈላስፎች ነበሩ። *“በቁጥጥርህ ውስጥ ያለውን ነገር ተቆጣጠር፤ ከቁጥጥርህ ውጪ የሆነውን ነገር ደግሞ አምነህ ተቀበል”* ይላሉ።

ለምሳሌ፦ በመንገድ ላይ እየሄድክ ሳለ አንድ ሰው ድንገት ይጋጭሃል፤ ከዚያም ቆሞ ፀብ ይፈልጋል። ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ የስድብና የዛቻ መዓት ያወርድብሃል። ይህ ሰው መጋጨቱና መሳደቡ ካንተ ቁጥጥር ውጪ ስለሆነ አምነህ ትቀበለዋለህ። ነገር ግን በምላሹ አንተም ተነስተህ የምትጣላ ከሆነ፣ አልያም ተረጋግተህና ስሜትህን አረጋግተህ በሰላም የምታልፍ ከሆነ ይህ ውሳኔ ባንተ ቁጥጥር ውስጥ ስለሆነ እሱን መቆጣጠር ትችላለህ።

ስቶይኮች ውጫዊውን ዓለም ሳይሆን፣ ውስጣዊውን(ስሜታችንን) ነው የምንቆጣጠረው ይላሉ።

ግን የእውነት ይህ "ችግር" የምንለው ነገር የሕይወታችን ጠንቅ ነውን? መልሱ፦ አይደለም ነው ፈጽሞ አይደለም! እንደውም በተቃራኒው ነው። ሁልጊዜ ከሕይወታችን ላይ ፈጣሪያችን እንዲያጠፋልን በጸሎት የምንለምነው ችግር፣ ይልቁኑ እኛ በዚህች ምድር ላይ በሕይወት እንድንቆይ የሚረዳን ዋና ሞተራችን ነው።

ለዚህም አሜሪካዊው የስነ-ባህሪ ተመራማሪ በሆነው በጆን ቢ ካልሆን (John B. Calhoun) በአይጦች ላይ የተደረገው ታዋቂው የ"ዩኒቨርስ 25" (Universe 25) ሙከራ ፍጹም ማሳያ ነው።

ይህ ታሪካዊ ሳይንሳዊ ሙከራ "Universe 25" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በታዋቂው አሜሪካዊ የስነ-ባህሪ ተመራማሪ (Ethologist) ጆን ቢ ካልሆን (John B. Calhoun) በ1960ዎቹ መጨረሻ እና በ1970ዎቹ መጀመሪያ የተከናወነ ነው። የዚህ ሙከራ ዋና ዓላማ፦ "አንድ ማህበረሰብ ሊያጋጥመው የሚችለው ችግር፣ መከራ፣ ድህነት እና የአዳኝ ፍርሃት በሙሉ ቢቀረፍና ፍጹም ምቾት (Utopia) ቢሰጠው ምን ሊፈጠር ይችላል?" የሚለውን ለማየት ነበር።

ካልሆን ለአይጦቹ ፍጹም የሆነች “ገነት” ገንብቶ የነበረ ሲሆን፣ የሳጥን መሰል ዓለሙ (Universe 25) መቼት የሚከተሉትን ያካተተ ነበር፦

የማያልቅ ምግብና ውሃ፦ ለአይጦቹ በጭራሽ የማያልቅና ያለምንም ልፋት የሚገኝ የምግብ እና የውሃ አቅርቦት ተዘጋጀ።

ንጹህ መኖሪያ፦ እስከ 3,840 አይጦችን በምቾት የመያዝ አቅም ያላቸው ንጹህ ሳጥኖችና መወጣጫዎች ተገነቡ።

ፍጹም ደህንነት፦ ምንም ዓይነት አዳኝ እንስሳ (Predator) እንዳይገባ ተደረገ፤ የሙቀት መጠኑም የተስተካከለ እና ከበሽታ ፍጹም ነጻ ነበር።

በአጭሩ፣ አይጦቹ ለመኖር፣ ለምግብ፣ ለደህንነት ወይም ለግዛት መታገል የማይጠበቅባቸው፣ ሁሉም ነገር በነጻ የቀረበላቸው “የምቾት ገነት” ተፈጠረላቸው። ሙከራው የተጀመረው 4 ጥንድ (8) ጤናማ አይጦችን ወደዚህ ዓለም በማስገባት ነበር። ሂደቱም በአራት ዋና ዋና ታሪካዊ ደረጃዎች አለፈ፦

ደረጃ 1፦ የመላመድ ጊዜ (The Strive Period)

ይህ የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን አይጦቹ አዲሱን አካባቢ የተለማመዱበት፣ የተጋቡበት እና የመጀመሪያ ግዛታቸውን የከለሉበት ወቅት ነበር። የመጀመሪያዎቹ 104 ቀናት በዚህ ሰላማዊ ሁኔታ አለፉ።

ደረጃ 2፦ የፈጣን እድገት ወርቃማ ጊዜ (The Exploit Period)

አይጦቹ አካባቢውን ከተለማመዱ በኋላ በከፍተኛ

ፍጥነት መባዛት ጀመሩ። ምንም ዓይነት የምግብ እጥረት ወይም ስጋት ስላልነበረ፣ የህዝብ ቁጥሩ በየ 55 ቀኑ እጥፍ ይሆን ነበር። ይህ ለአይጦቹ ፍጹም “ወርቃማውና የደስታ ጊዜያቸው” ነበረ።

ደረጃ 3፦ የችግር መጀመሪያ እና የባህሪ ማሽቆልቆል (The Equilibrium Phase)

በቀን 315 ላይ የህዝብ ቁጥሩ እድገት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ጀመረ። እዚህ ጋር ልናስተውለው የሚገባው ትልቁ ምስጢር፦ **ምንም ዓይነት የምግብ፣ የውሃ ወይም የመኖሪያ ቦታ እጥረት አልነበረም!** ነገር ግን አይጦቹ ያጋጠማቸው ትልቁ ችግር “የማህበራዊ መጨናነቅ እና የሚታገሉበት ዓላማ ማጣት” ነበር። በዚህ ወቅት ካልሆን “Behavioral Sink” (የባህሪ መቀልበስ ወይም ማሽቆልቆል) ብሎ የጠራው አስከፊ ክስተት ተከሰተ

የተገለሉ ወጣቶች፦ ወጣት አይጦች በህብረተሰቡ ውስጥ የራሳቸውን ማህበራዊ ቦታና ሚና ማግኘት ተሳናቸው። የቀድሞዎቹ (ሽማግሌዎቹ) አይጦች ስልጣንና ግዛታቸውን ስላልለቀቁና የሚጋፈጡት ውጫዊ ጠላት ስላልነበረ፣ ወጣቶቹ አይጦች ሙሉ በሙሉ ተገፍተው ወደ ሳጥኑ መሃል ሜዳ ተሰበሰቡ።

- **ምክንያት አልባ ጠበኛነት፦** እነዚህ የተገለሉ ወንድ አይጦች ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይኖራቸው እርስ በርስ መናከስና ከባድ ግጭት ውስጥ መግባት ጀመሩ። በቡድን እየሆኑ ደካሞችን ያጠቁ ነበር።

- **የእናትነት ስሜት መጥፋት፦** ሴቶቹ አይጦች በደረሰባቸው ማህበራዊ መጨናነቅ የተነሳ እጅግ ጠበኛ (Aggressive) ሆኑ። አስከፊው ነገር ደግሞ፣ የራሳቸውን ልጆች የመንከባከብ የተፈጥሮ ስሜታቸው ጠፋ፤ ልጆቻቸውን መመገብ አቆሙ፣ አንዳንዶቹም የገዛ ልጆቻቸውን ይገድሉና ይበሉ ነበር።

- **“ውቦቹ” (The Beautiful Ones) ፦ በዚህ ትርምስ ውስጥ አንድ በጣም የተለየና የሚገርም የወንድ አይጦች ቡድን ተፈጠረ። ካልሆን እነዚህን “The Beautiful Ones” (ውቦቹ) ሲል ጠራቸው። እነዚህ አይጦች ከማንኛውም ጠብና ማህበራዊ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ይርቃሉ። ለሴቶች ምንም ዓይነት ስሜትና ፍላጎት የላቸውም (ለመራባት ፈጽሞ አይሞክሩም)። ሙሉ 24 ሰዓታቸውን የሚውሉት በመብላት፣ በመተኛት እና የገዛ ፀጉራቸውን በምላሳቸው በማፅዳት (Grooming) ብቻ ነበር። በማህበራዊ ሕይወትና በትግል ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አድርገው ስለማያውቁ ሰውነታቸው ላይ አንድም ጠባሳ አልነበረም፤ ለዚህ ነው “ውቦቹ” የተባሉት። ነገር ግን እነዚህ አይጦች በሕይወት እያሉ የሞቱ በድን ነበሩ።**

ደረጃ 4፦ የሞት ጊዜ (The Die Phase)

የህዝብ ቁጥሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ (ወደ 2,200 ገደማ) ደርሶ ከቆመ በኋላ፣ የአዲስ አይጦች መወለድ ሙሉ በሙሉ ቆመ። የመጨረሻዋ አይጥ በ1973 ዓ.ም በሞት ተለየች። “Universe 25” ፍጹም ምግብና ምቾት እያለው ወደ መቃብርነት ተቀየረ። አይጦቹ የሞቱት በረሃብ ሳይሆን፣ በማህበራዊ ክህሎት እጥረት፣ በስነ-ልቦና ቀውስ እና የመኖር ፍላጎታቸው (Will to Live) ሙሉ በሙሉ በመክሰሙ ምክንያት ነበር።

ጆን ካልሆን ራሱ በዚህ ሙከራ ላይ አንድ ወሳኝ ታሪካዊና ፍልስፍናዊ አባባል ተናግሯል። አይጦቹ አካላዊ ሞት ከመሞታቸው በፊት “First Death” (የመጀመሪያው ሞት) ወይም “የመንፈስ ሞት” ተከስቶባቸዋል ይላል። የመንፈስ ሞት ማለት አንድ ሕያው ፍጡር ገና በሕይወት እያለ፣ የመኖር ትርጉሙና ዓላማው ሲሞት ማለት ነው።

ለምን የመንፈስ ሞት መጣ? ምክንያቱም የሚፈቱት ምንም ዓይነት ችግር አልነበረም! በተፈጥሮ የተሰጣቸው “የመኖር ትግል”

(Survival instinct) በምኞት ብዛት ተገደለ። ፍላጎታቸው ሁሉ ያለምንም ልፋት ስለተሟላ፣ አእምሯቸው መሥራት አቆመ።

አንዳንድ የስነ-ልቦና እና የማኅበራዊ ሳይንስ ሊቃውንት ይህንን ሙከራ በቀጥታ ከሰው ልጅ ባህሪ ጋር ያያይዙታል። የሰው ልጅም ቢሆን ሥራ ሲያጣ፣ ማህበራዊ ሚናው ሲጠፋ፣ እና የሚታገልለት የወደፊት ተስፋው ሲጨልም (ልክ እንደ "ውቦቹ" አይጦች) ወደ ራሱ መገለል (ለምሳሌ በጃፓን *Hikikomori* እንደሚባለው የቤት ውስጥ መሸሸግ ክስተት)፣ ወደ እጽ ሱሰኝነትና ወደ ከንቱ ጠበኛነት ሊቀየር እንደሚችል ይጠቁማሉ።

እዚህ ጋር ምናልባት *"ሰው እኮ ከአይጥ ይለያል! የሰው ልጅ ምግብና ውሃ ስለተደላደለለት ብቻ ከመንፈስ አይሞትም፤ ይልቁንስ ስፖርት ይሠራል፣ ጥበብ (Art) ይፈጥራል፣ ሳይንስን ይመረምራል፣ ወይም ስለ አጽናፈ ዓለም ለማወቅ ለመመራመር ይሞክራል"* ትሉ ይሆናል።

መልሴ የሚሆነው፦ እውነት ነው ሰው ከአይጥ ይለያል። ነገር ግን ያ ሰው የሚፈጥረው "ስፖርት፣ ጥበብ፣ ፍልስፍና ወይም የጠፈር ምርምር" እኮ በራሱ **"ሰው ሰራሽ ችግር"** (Artificial Struggle) ነው! የሰው ልጅ በተፈጥሮ የቀረበለት መሠረታዊ ችግር (ረሃብና ደህንነት) ሲቀረፍለት፣ በሕይወት ቀጥ ብሎ ለመቆየት ሲል በራሱ ላይ "ግብ" (Goal) የሚባል አዲስ ተራራና አዲስ ችግር ይፈጥራል። ያ የሚታገልለት ሰው ሰራሽ ግብና ችግር ከሌለው ግን፣ ሰውም ቢሆን ልክ እንደ ዩኒቨርስ 25 አይጦች ወደ ከባድ ድብርት (Depression) እና ፍፁም ትርጉም አልባነት ይገባል።

ይህንን እውነታ ይበልጥ ለመረዳት ፍፁም ሳይንሳዊ በሆነው በጠፈርተኞች (Astronauts) ሕይወት መመልከት እንችላለን፦

ጠፈርተኞች ወደ ጠፈር ሲወጡ፣ እዚያ ምንም ዓይነት የስበት ኃይል (Gravity) ስለሌለ አካላቸው ላይ ምንም ዓይነት ጫናና ክብደት አይሰማቸውም፤ ፍጹም ነጻና ምቾት ላይ ናቸው። ነገር ግን ይህንን ምቾት የሚቃወምና ሰውነታቸውን ወደ ታች የሚጎትት “የስበት ኃይል (ችግር)” ስለሌለ፣ ጠፈር ላይ በሰነበቱ ቁጥር የሰውነታቸው ጡንቻ ይሟሽሻል፣ አጥንታቸው ይሳሳል፣ ደማቸው ይበላሻል። ወደ መሬት ሲመለሱ በገዛ እግራቸው እንኳ መራመድ አቅቷቸው በባለሙያ ይደገፋሉ።

ይህ ምሳሌ የእኔን ፍልስፍና በሚገባ ያረጋግጣል፦ ግራቪቲ (ችግር) ወደ ታች የሚጎትተንና የሚያደክመን መስሎን እንጠላዋለን፤ ነገር ግን እኛን ጠንካራ፣ ጤነኛና ቀጥ አድርጎ በሕይወት ያቆመን እሱ ራሱ ነው!

ችግር ኃያላን ሰዎችን ሲፈጥር ፣ ኃያላን ሰዎች ደግሞ ችግርን አጥፍተው ምቾትን ይፈጥራሉ ፣ ምቾት ደግሞ ደካማ ሰዎችን ይፈጥራል ፣ ደካማ ሰዎች ደግሞ ችግርን መልሰው ይፈጥሩታል ።

በዚህ ስርአት ነው ታሪክ ራሱን እየደጋገመ የሚኖረው አሁን ያለንበት ዘመን ኃያላን የፈጠሩት የምቾት ዘመን ነው በአንድ ወቅት በመላው አለም ታዋቂ የነበሩት እንደነ አልበርት አንስታይን፣ ቶማስ ኤዲሰን፣ አይዛክ ኒውተን፣ ሜሪ ኩሪ የመሳሰሉ የሳይንስ የምርምርና የጥበብ ሰዎች ነበሩ አሁን ላይ ታዋቂዎች የዋዛ ፈዛዛ ሰዎች ናቸው።

ችግር በሕይወታችን ላይ ሲመጣ በቀላሉ እጅ ሰጥተን ራሳችንን እናጠፋለን ነገር ግን ያ ችግር እኛን በሕይወት ለማቆየት ነበር አመጣጡ እኛ ግን ይህችን ምድር ክፉ እናደርጋታለን እሷ እኛን ለማኖር ማድረግ ያለባትን ሁሉ እያደረገች ነው

ከየትኛውም ዘመን በላይ የእኛ ትውልድ፣ በሚያሳዝን ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ ድብርታምና ሐዘንተኛ ትውልድ ሆኗል። ምክንያቱም ፍላጎቶቻችን፣ ምኞቶቻችን እና ከሕይወት የምንጠብቃቸው ነገሮች ካለፈው ትውልድ በብዙ እጥፍ ስለበዙ ነው።

በጥንት ዘመን የነበሩ ነገሮች በሙሉ “የመጀመሪያ ደረጃ ጥቅም” (Primary Function) ብቻ ነበር የነበራቸው። በጥንቱ ዘመን ቤት ማለት የሚያድሩበትና ከብርድና ከዝናብ የሚጠለሉበት ብቻ ነበረ። ልብስ ማለት ሰውነትን መሸፈኛና ሙቀት ማግኛ ብቻ ነበረ። ጋሪ፣ ፈረስና በቅሎም መጓጓዣ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹም የሰው ልጅ ቁሶች እንዲሁ ለቀላል ፍላጎቶች መሟያ ብቻ ያገለግሉ ነበር።

አሁን ባለንበት ዘመን ግን ሁሉም ቁሶች ከመጀመሪያ ጥቅማቸው አልፈው ጥሰው ሄደዋል። ዛሬ ላይ ቤት ማደሪያ ብቻ አይደለም ፤ ልብስና መኪናም እንዲሁ ።

ከቀድሞው ሰው ይልቅ እኛ በነዚህ ልዩ ልዩ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች የተነሳ፣ ከቁሳዊው ዓለም ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ተጣምረናል ። በዚህም ምክንያት ከዚህ ከቁሳዊው ዓለም በጣም ብዙ ነገር እንፈልጋለን እንጠብቃለን።

እነዚህን የምንመኛቸውን ማለቂያ የሌላቸውን ቁሳዊ ነገሮች እንደፈለግነው ማግኘት ሳንችል ስንቀር፣ አእምሯችን በቀጥታ ወደ ከባድ ድብርት (Depression) እና ሐዘን ውስጥ ይከተናል። ስለዚህ ከዚህ የባዶነትና የድብርት ስሜት ለማምለጥ ሲባል፣ በተለያዩ ጊዜያዊ ነገሮች ውስጥ እንሸሸጋለን ለሱስ፣ ለማኅበራዊ ሚዲያ እና ለተለያዩ መጥፎ ልማዶች ተጋላጭ እንሆናለን። ነገር ግን ይህ ሽሽት ድብርቱን ለጊዜው ይደብቀዋል እንጂ ፈጽሞ አይፈታውም።

እኔ ለዚህ ትልቅ ቀውስ እንደ መፍትሔ አድርጌ ያስቀመጥኩት **“እሾህን በሾህ”** የሚለውን ጥንታዊ ጥበብ ነው። በግል ታሪኬ ላይ እንዳስነበብኳችሁ ካሳለፍኩት ከባድ ድብርት ውስጥ የወጣሁት፣

በትልልቅና ውድ በሆኑ ነገሮች ሳይሆን፣ እጅግ በጣም ቀላልና ተራ በሚባሉ በትናንሽ ነገሮች ነው።

ይህንን የውስጥ ለውጥ ሂደት እኔ **“የስትራፖ ሕግ”** (Strappo Effect) ብዬ እጠራዋለሁ።

ልክ የአካል ብቃት እንቅስቀሴ (Gym) ለመጀመሪያ ቀን ስንገባ፣ 5 ኪሎ ግራም (5kg bench press) ብናነሳ፣ በቀጣዩ ቀን ጠዋት የሰውነታችን ጡንቻ እንዳለ በከፍተኛ ሁኔታ ይቆስላል በ“ስትራፖ” ይመታል።

ነገር ግን በነጋታው ወደ ጂም ተመልሰህ ስትገባና ስትሠራ፣ ያቺ ትናንት ሰውነትህን ያደቀቀችው 5 ኪሎ ግራም ክብደት ዛሬ ላይ በጣም ቀላል ሆና፣ እንደ ቀልድ ስታነሳት ታገኘዋለህ። እንዲያውም አቅም አግኝተህ ሌላ ከበድ ያለ ክብደት ለመሥራት ትዬዳለህ። ወደ ቤትህ ተመልሰህ ስትገባም ምንም ዓይነት ሕመም አይሰማህም። ምክንያቱም የአካልህ ገደብ የነበረውን ያንን የ5 ኪሎ ግራም ሕመም አልፈህ ሄደሃል! ያቺን 5 ኪሎ ግራም የፈለገውን ያህል ጊዜ ደጋግመህ ብታነሳሳት ዳግመኛ ጡንቻህን ልታመው አትችልም። ነገር ግን ከዛ ጊዜያዊ ህመም ስትራፖ ሽሽት ስፖርታዊ እንቅስቃሴውን ብታቆም ያቺ 5kg ባገኘችህ ቁጥር ስታሰቃይህ ትኖራለች እንድታማርር እና እንድትጠላት ትሆናለህ።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ ድብርትና ሐዘን በሕይወታችን ላይ በሚመጣበት ጊዜ፣ በተለያዩ ሱሶችና የጊዜ ማሳለፊያዎች ውስጥ ተደብቀን ልናመልጠው መሞከር አያስፈልግም። ይልቁኑ **“ድብርትን ራሱን መደበር”** ነው!

ያንን የድብርት ስትራፖ አንዴ ካሳለፍነውና የውስጥ አቅማችንን ካሳደግን በኋላ ግን፣ ለቀጣይ ያ ተመሳሳይ ድብርትና ችግር መልሶ ሊደብረን ወይም ሊጥለን አይችልም። ምክንያቱም እኛ ልክ እንደዛች 5kg የድብርቱን ገደብ ሰብረን አልፈነው ሄደናልና። እኔም በግል

ሕይወቱ የመጨረሻ የምለውን የችግር ጥግ በዛ ጦርነት ስላሳለፍኩ አሁን ላይ የሚመጣ ማኛውም ችግር ለኔ ምንም ነው በቀላሉ ነው የማልፈው እንደዛ እጠላው የነበረው ጊዜ ለካ በጣም ይጠቅማል ታዲያ ችግር መጥፎነቱ ምን ላይ ነው አልኩኝ ይህቺን ምድር ተረዳኂት ችጋራሟን ዓለም ወደድኳት ደስ ብሎኝ የምኖርባት ሆነች።

ማናችንም ብንሆን፣ ደስታ ጥሎን እስኪሄድ ድረስ ከእኛ ጋር እንደነበረ ማወቅ አንችልም። የሰው ልጅ ተፈጥሮ ያለውን ነገር ዋጋ የሚረዳው ሲያጣው ብቻ መሆኑ ነው።

ታመን አልጋ ላይ ስንተኛና በሕመም ስንማቅቅ፣ ጤነኛ ሆነን ስንንቀሳቀስ ምንኛ የታደልን እንደነበርን እና በዚህች ምድር ላይ ምንም ነገር ከጤና እንደማይበልጥ እንረዳለን። ለትምህርት(ጊቢ) እና ለሥራ ከቤት ስንወጣና ስንርቅ ልክ እዚያ እያለን በየቀኑ በትንሽ በትልቁ ስንጨቃጨቃቸውና ስንነታረካቸው የነበሩት ቤተሰቦቻችን፣ እናታችን፣ አባታችን፣ ወንድምና እህቶቻችን ለእኛ ምን ያህል ትልቅና የማይተካ ዋጋ እንደነበራቸው ይገባናል። ሌሎቹም የሕይወት ስጦታዎች በሙሉ ልክ እንደዚሁ ናቸው።

ነገር ግን በተቃራኒው፣ በእጃችን የሌሉትንና ለእኛ ግዙፍ መስለው የሚታዩንን ከማሳደድ፣ በእጃችን ያሉትንና ጥቃቅን መስለው የሚታዩንን ነገሮች ከእኛ ጋር ሳሉ፣ ገና ጥለውኝ ሳይሔዱ ልናጣጥማቸው ይገባል።

ምድር እጅግ ውብ ናት በውስጧ ብዙ ደስ የሚሉ ነገሮችን ይዛለች ስላልተረዳናት ግን ሌሎች ነገሮችን በማሳደድ ራሳችንን ጠምደን እሷን እንደክፉ ማየት ጀምረናል አስቡት እስኪ ሌሊት ማጎሌት ለምስጋና አድራችሁ ከምድር ያላችሁ እስካይመስል በሰማያዊ ዝማሬ በተመስጦ ነግቶ ፀሀይ እስክትወጣ፤ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ለበዓል ተሰብስባችሁ ስታከብሩ፣ ቀዝቀዝ ባለ አየር ወክ ስታደርጉ፣ የምትወዱትን ምግብ ስትመገቡ፣ ምሽት ላይ ጨረቃና ከዋክብቱን

እያያችሁ ተፈጥሮን ስታደንቁ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ reverend insanity እና Lord of The mysteries እና ሌሎች ውብና ረቂቅ የሰው ልጅ በምናቡ የፈጠራቸውን አስገራሚ የድርሰት ታሪኮች ስታነቡ። እጅግ በጣም ብዙ ቀላል የሚመስሉ ግን ውብ በሆኑ ነገሮች የተሞላች ናት ምድራችን ።

ማጠቃለያ

ከሁሉም ነገር አስቀድመን፣ ስለ ራሳችን እና ስለ ውስጣዊ ፍላጎታችን ልናውቅ ይገባል ብዬ አምናለሁ። ስለ 'Will' (ስለ ውስጣዊ ፈቃድና ፍላጎት) ስናውቅ ስለ ራሳችን እናውቃለን በውስጣችን ምን ዓይነት ነገር እየተካሄደ እንዳለ በግልጽ እንረዳለን።

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ በተፈጥሮ የተሰጠን ዕውር ሥርዓት ከእኛ በላይ ሆኖ ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ እንዳይቆጣጠረው ገደብ እናበጅለታለን።

በመኖር ፍላጎት (Will to Live) **ላይ** ፦ ከሰውነት ተራ ወጥተን ወደ እንስሳነት እንዳናዘነብል

በኃይል ፍላጎት (Will to Power) ፦ ወደ ኃይል በምናደርገው ጉዞ ወደ ስግብግብነት፣ ጭካኔና ሌሎችን ወደ መርገጥ እንዳይቀየር

በፍቅር ፍላጎት (Will to Love) ፦ ከሰዎች ጋር የምንፈጥረው ጥልቅ ትስስር የራሳችንን ማንነት አጥፍቶ በሌሎች ሰዎች ላይ ፍፁም ጥገኛ (Dependent) እንዳያደርገን።

በደስታ ፍላጎት (Will to Happiness) ፦ ምኞትን ብቻ በማሳደድና ችግርን በመሸሽ ራሳችንን ለከፍተኛ ድብርት (Depression) እና ለትርጉም አልባነት አሳልፈን እንዳንሰጥ።

ለዚህ ሁሉ የ‘Will’ ፍላጎት ገደብ ስናበጅለት እሱ ከላይ ሆኖ እኛን በባርነት እንዲነዳን ሳይሆን፣ እኛ ከላይ ሆነን ያንን ዕውር ሥርዓት በዕውቀት እንድንመራው ያስችለናል።

እኛ ለዚያ ዕውር የተፈጥሮ ኃይል “ዓይን” እንሆንለታለን። ዕውር ዕውርን እየመራ ወደ ገደል እንዲገባ ሳይሆን፤ ይልቁኑ ዓይናማው እኛነታችን ዕውሩን የውስጥ ኃይል እየመራ፣ በትክክለኛው መንገድ ላይ በጽናት እንድንጓዝ ያስችለናል።

ተፈጸመ

“ሰው ለመሆን የሚጥረው እንስሳ ሰውም ከታላቁ ሰው በላይ ነው”

ዘአብ ዘሚካኤል

መክፈል ለማትችሉ ተከፍሎላችኋል፤ መክፈል የምትችሉ ግን ዋጋው 100 ብር ነው

CBE 1000649275062 Ze’Ab Zemichael

Contact me

E-mail nageszeab@gmail.com

Telegram @Nages_Desta